# በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ትንተና፣

በቀለ ቀነኒ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት

ከሚያስፈልጉ ነጥቦች መካከል ከፊሉን ለማሟላት

የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2009

ጅማ

# በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ

# የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ትንተና፡


በቀለ ቀነኒ

ጅማዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማካሪዎች፡ -

1. ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

2. መሀመድ አደም (MA)

ነሐሴ 2009

ጅማ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መረሀ ግብር

በቂልጡ ካራ'አገምሳበልአ እና ቡኬ አካቹ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ትንተና በሚልርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲው የጥራትና ወጥነት መስፈርት በማሟላት በአማካሪዎችና በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

### የፈታኝ ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ____________________________ ፊርማ _____________ ቀን _________

የውጭ ፈታኝ _______________________ ፊርማ _____________ ቀን _________

የውስጥ ፈታኝ _______________________ ፊርማ _____________ ቀን _________

*ማረጋገጫ*

*በቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ጥናት ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ፣ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መረሀ ግብር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈል ጉነጥቦች ከፊሉን ለሟሟላት ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህን በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና የጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ ባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡*

*ስም* ________________________

*ፊርማ* ______________________

*ቀን* ________________________

## *አጠቃሎ*

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቋንቋ ትምህርቱ*

*የተነቃቁ ለማድረግ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ምን እንደሚመስል ማጥናት ነው፡፡ ይህንን ለመተግበር ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ከተነሱ በኋላ ጥናቱን ለማካሄድ ናሙናዎች ተወስዶአል፡፡ በዚህ መሰረት በኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በቂልጡ ካራ ወረዳ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተወስዶአል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች ለመምረጥም በጠቅላይና በዕጣ የማውጣት ዘዴ ናሙናን ተጠቅሞአል፡፡ ከነዚህ ተተኳሪዎች  ረዳት መረጃ ሰብሳቢ በታዛና በተደራጀ ምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ አማካኝነት መረጃ ተሰብስቦአል፡፡ መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተማሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማነሳሻ ስልትን በምን አይነት ሁኔታ በመተግበር ላይ እንዳሉ በአይነታዊና ገላጭ የምርምር ዘዴ አማካይነት በገለፃተተንትነው የሚከተለው ውጤት ተመዝግቦአል፡፡ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ከክፍል ምልከታው፣ ከጽሑፍ መጠይቆቹና ከቃለ መጠይቆቹ ምላሽ ማረጋገጥ እንደተቻለው የማነሳሻ ስልቶችን በተሻለ ሁኔታ የሚተገብሩ የአገምሳ በልአና ቡኬ አከቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የማነሳሻ ስልቶችን ተግባራዊ ሲያደርጉ ተረጋግጦአል፡፡ ተማሪዎች ያላቸው ተነሳሶት ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት፡ - መምህራን መልካም የሆነ የመምህር ተማሪ ግንኙነት መፍጠር አለመቻላቸው' እንደ ቡድንና ጥንድ እያደራጁ በማሳተፍ በተስተምሮቱ አጋዥ ሁኔታ አለመመቻቸት' አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት' አዝናኝና አስደሳች የክፍል ሁኔታ አለመፍጠራቸው' የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ያልተመቻቸ በመሆኑ' መምህራኑ የማስተማር ዘዴ መምህር መር ማድረጋቸው ከዚህ በመነሳት የመፍትሄ ሀሳቦች የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለማነቃቃት እና የማነሳሻ ስልቶችን ለመተግበር በቅድሚያ ለማስተማር ፍላጎት እና ተነሳሶት ያላቸው ሊሆን ይገባል፡፡ በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር ወደ ሃምሳ ዝቅ ቢል ከዓሉታዊ ምጋቤ ምላሽ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት መልካም ነው፡፡ በአጠቃላይ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች የተሻለ የማነሳሻ ስልት ትግበራ ለማምጣት ያስችል ዘንድ ጥናቱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ጠቁሟል፡፡*                    /

## ምስጋና

ከሁሉም በላይ ግን አስጀምሮኝ እዚህ ደረጃ ላይ ለደረሰኝ ዕቅዱንና ዓላማዉን የፈፀመልኝ ልዑል እግዝአብሄር ስሙ የተመሰገነ ይሁን፡፡ በቅድሚያ "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ዉስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ጥናት ትንተና በቅልጡ ካራ' አገምሳ በልአና በቡኬ አካቼ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት" በሚል ርዕስ ጥናት እንድያካሄድ ዕድሉን ሰጥቶ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ጥናታዊ ጽሑፌን በመከታተልና አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማማከር እገዛቸዉ ላልተለየኝ ዶ/ር ለማ ንጋቱ እና አቶ መሀመድ አደም (MA) ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ መካሄድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ (የቀለም) ጽሑፎችን በማንበብ አስፈላጊ የሆኑ የጽሕፈት ሥራዎችን እና የእጅ ጽሑፍ በመገለበጥ ጊዜያቸዉንና ጉልበታቸዉን መስዋዕት በማድረግ እገዛ ላደረጉልኝ መ/ር መንግስቱ ባይሳ እና መ/ር ታምሩ ሆላኒ እንድሁም በኮምፒዉቴር ጽሑፍ እገዛ ላደረገልኝ መ/ር መልካሙ ዱፌራን የከበረ ምስጋናዬን አቀረባለሁ፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ አስተማማኝና ስኬታማ ለማድረግ በተደረገዉ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሂደት መረጃዎችን በመቀበል በክፍል ምልከታዉ ተሳታፊዎች በመሆን ቀና ትብብራቸዉ ላልተለዩኝ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሳነ መምህራን' የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ለረዳት ተመልካቾች የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸዉ፡፡ በዚህ ሁሉ የሥራ ሂደት ሀሳብና በፀሎት ከእኔ ጋር ለነበሩ ባለቤቴ ወ/ሮ አበባዬ ጉርሙ እና ልጆቼ ለሊሳ በቀለ፣ ቶሌራ በቀለ፣ ቆንዳሌ በቀለ፣ ዱሬቲ በቀለ እና መረርቱ በቀለ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡



ማውጫ ገፅ

አጠቃሎ ........................................................................................................ I

ምስጋና የይዘት ማውጫ ........................................................................................ II

የሰንጠረዥ ማውጫ ............................................................................................ VIII

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ ........................................................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ...................................................................................... 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ .................................................................................. 4

1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................ 5

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት ............................................................................................ 6

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት .............................................................................. 6

2.2 የተነሳሶት ምንነት .................................................................................. 6

2.3 የተነሳሶት አስፈላጊነት .......................................................................... 7

2.4 የተነሳሶት ዓይነቶች ............................................................................ 8

2.4.1 ዉስጣዊ ተነሳሶት ..................................................................... 9

2.4.2 ዉጫዊ ተነሳሶት ....................................................................... 11

2.4.3 ተነሳሶት በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ያለዉ ሚና ...................................... 13

2.5 የተነሳሶት ተለውጠዎች ........................................................................ 14

2.5.1 ማህበረሰቡ ለቋንቋ ያለዉ አመለካከት… ........................................ 14

III

2.5.2 ወላጆች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና ያላቸዉ አመለካከት ............... 15

2.5.3 ቢጤዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና ያላቸዉ አመለካከ............. 15

2.5.4 የቋንቋ መምህር……....................................................................................15

2.5.5 የማስተማሪያ ዘዴ ........................................................................................16

2.5.6 የቋንቋ ትምህርቱ ትግባራዎች.........................................................................16

2.6 የተነሳሶት ብልሃቶች በቋንቋ ትምህርት ክፍል ዉስጥ ስለመጠቀም ..........................17

2.6.1 መስረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን መፍጠር .........................................................18

2.6.1.1 ትክክለኛ የመምህር ባህሪይና ጥሩ የመምህር ተማሪ ግንኙነት............................18

2.6.1.2 አስደሳችና አጋዥ የክፍል ዉስጥ ሁኔታ...............................................................19

2.6.1.3 ጥሩ የቡድን ሥርዓትን የያዘ የተማሪ ቡድን ጥምርታ .........................................20

2.6.2 ተፈጊዉን ተነሳሶት ማንቀሳቀስ..........................................................................21

2.6.2.1ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸዉን መልካም አመለካከት ማሳደግ ........22

2.6.2.2 ዉጤት የመጠበቅ ተስፋን መጨመር ...................................................................23

2.6.2.3 አሰፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት .............................25

2.6.2.4 የተማሪዎች ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግ...........................................................25

2.6.2.5 የተማሪዎችን የአላማ አፈፃፀም ማሳደግ..............................................................26

2.6.3 የተማሪዎችን ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ .......................................................26

2.6.3.1 ተማሪዎች ያላቸዉን ለራስ የተለየ ግምት መስጠት በመንከባከብ በራስ የመተማመንን ብቃት ማሳዳግ...................................................................................27

2.6.3.2 በራስ መማር ....................................................................................................29

2.6.3.3 የተማሪዎች እርካታ መጨመር...........................................................................29

2.6.3.4 የትምህርት ትግበራዎችን በተነሳሶታዊ መንገድ ማቅረብ ....................................30

2.6.3.4.1 ትምህርቱን አነቃቂና አስደሳች ማድረግ ..........................................................31

IV

2.6.3.4.2 የሚያነቃቁ ምጋቤ-ምላሽና ሽልማት መስጠት ....................................................33

2.7 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት ...................................................................................34

ምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴና አካሄድ


3.1 የጥናቱ ዘዴ ........................................37

3.1.1 የጥናቱ አካላይ ........................................37

3.1.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................37

3.1.2.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ ........................................37

3.1.2.2 የትምህርት ቤቱ ናሙና አመራረጥ ........................................37

3.1.2.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........................................38

3.1.2.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ........................................38

3.1.2.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ........................................38

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች........................................39

3.2.1 የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ........................................39

3.2.2 የክፍል ዉሰጥ ምልከታ........................................39

3.2.3 የጽሁፍ መጠይቅ........................................40

3.2.4 ቃለ መጠይቅ........................................40

3.3 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት........................................41

3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ........................................42


ምዕራፍ አራት፡ የመረጃዎች ትንተናና ከጥናቱ የተገኙ ዉጤቶች


4.1 መምህሩ የሚጠቀምባቸዉ የማነሳሻ ስልትና አተገባበርበሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................44

4.1.1 መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት መፍጠር........................................45

4.1.2 የመማሪያ ክፍሉን አስደሳችና አጋዥ ስለማድረግ በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................48

4.1.3 ምጋቤ-ምላሽ መስጠትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................54





4.1.4 የመረጃ መሣሪያዎችን መጠቀም በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................56

4.2. የትምህርቱን ይዘት ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ በሚመለከት የቀረበ ትንተና ....58

4.3 የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሶት በሚመለከት የቀረበ ትንተና....60

4.4 በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተጽህኖ የሚያደርሱ ተለዉጦችበሚመለከት የቀረበ ትንተና....68

4.5 ከጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ አስተያየቶች....70

ምዕራፍ አምስት፡

5.1 ማጠቃለያ ....73

5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ....77

ዋቢ ጽሑፎች

አባሪዎች

ሠንጠረዥ ገጽ


1. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና አደረጃጀት ....................43
2. የመምህሩን አርአያነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታ የተገኘ ምላሾች....................44
3. የመምህር- ተማሪ ግንኙነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................45
4. የመምህር- ተማሪ ግንኙነት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች ...47
5. አስደሳች የመማሪያ ክፍል ሁኔታ መፍጠር በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች....................48
6. በቡድንና በጥንድ መደራጀትን በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች....................49
7. ተማሪ ተኮር እና መምህር-መሪ ዘዴን መጠቀም ማድረግ በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................51
8. ተማሪዎችን በተናጠል የመሳተፍ ተግባርን በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................52
9. ለተማሪዎች የተሰጡ ምጋቤ ምላሾችን በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................54
10. የመምህሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................57
11. የትምህርቱን አላማ ማሳወቅ በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ ምላሾች....................58
12. ስለ ትምህርቱ ይዘት ሳቢነት በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ ምላሾች....................59
13. የተማሪዎችን ፍላጎት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች....................60
14. ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸዉን ተነሳሽነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች....................62
15. ተማሪዎች ለመማር ያላቸዉን ፈቃደኝነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች ....................64
16 የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ብቃት በሚመለከት ከክፍል ምልከታዉ የተገኙ ምላሾች ....................66
17 ብጤዎቹ፣ወላጆችና ማህበረሰቡ ያላቸዉን አስተዋፅኦ በሚመለከት ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች ....................68




# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት መሠረታዊ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህም ተነሳሽነት የሰዎችን ፍላጎት፣ስሜት፣ጉጉት የሚያንፀባርቅ ከዉስጣዊ ወይም ከዉጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካካትን፣ አዎንታዊ ምላሽን፣ ጥሩ ዉጤትን የሚያስገኝ ፣አንድ ድርጊት እንዲፈፀም የማበረታታት ሂደት ነው (Gardner1985፣10)፡፡ በመሆኑም ተማሪዉ አንድ አቅጣጫ ይዞ በመጓዝ ወደ አንድ ግብ እንዲደርስ የሚያደርግ ጊዜያዊና ቀጣይነት ያለው የማነቃቂያ መንገድ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪው የግል ፍላጎቱንና ምርጫውን በሚተገብረው ሥራ ማጠናከር እንዲችል አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ከዚህም የተነሳ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነት አስፈላጊ ጉዳይ ይሆናል( Harmer 1991:3)፡፡

በትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለሚመጣው የባህሪይ ለዉጥ ተነሳሽነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመሆኑም አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት ካለው ሰፊ ግንዛቤና ትዉስታ ለመፍጠር አእምሯዊ ዕድገቱ የተፈጠነ ስለሚሆን ከትምህርቱ ግብ ይደርሳል፡፡(Noels 2003)፡፡ ሰዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ በተጨማሪ ቋንቋን ይለምዳሉ፤ይማራሉ፡፡ ይህም የሚሆነዉ ግለሰቡ በአከባቢዉ ከሚያገኘዉ ማህበረሰብ ጋር ከሚያደርገዉ መልካም ግንኙነት የተነሳ ለቋንቋዉ ሊጋለጥና በትምህርት ቤት ዉስጥ በመደበኛ ሁኔታ ቋንቋዉን ሲማር ነዉ፡፡ ቋንቋን መማር ሲባል ግለሰቡ በነቃ አእምሮ በመሆን በቋንቋዉ ቅርፅ ላይ በማተኮር፣በማደመጥ፣በማንበብ፣ስህተቶቹን ለይቶ በማዉጣት፣ ስዋስዋዊ ትክክለኝነቱን በማረጋገጥ፣የጽሑፍ ዉጤትን የበለጠ የሰላ ለማድረግ የሚካሄድ ሂደት ነዉ፡፡ ለዚህ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ደግሞ ተነሳሽነትን መፍጠር መሰረት ድንጋይ ነው (Alatis 1981፣98)፡፡

የተለያዩ አላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድን ነገር ለምንና እንዴት እንደሚተገብር የሚያሳይ፣ የባህሪይን ተጽዕኖ ሊያመጣ የሚችል ዉስጣዊ ግፊት ነዉ፣ተነሳሽነት የሰዎችን ስሜት ወይም ፍላጎት የተነቃቃ ማድረግ የሚችል ማነቃቃቱንም ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሀይል እንዳለዉ Rosser and N.Cholson (1984) ይገልፃሉ፡፡ ጠቅሶ እንደገለፁት ተነሳሽነት ወደ ግብ ሊያደርስ የሚችል ቀጥተኛ መስመር ነዉ፡፡

Guthrie. and Solomon (1997) ተማሪዎችን በውድድር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዉ በዉድድር ሁሉም ተማሪዎች ሊሳካላቸዉ አይችልም፡፡ በመሆኑም በተደጋጋም ሙከራ ስኬት ካላገኙ በራስ የመተማመን የስሜታቸዉን በማጣት ራሳቸዉን የማይሰራ ደካማ አደርገዉ ይቆጥራሉ፡፡ ሁለተኛዉ ከዉድድሩ አንጻ የሌላዉን የበላይ መሆን ግባቸዉን ለማሳካት በሌሎች ዘንድ አድናቆትን ለማቸርለበለጠ ዉስጣዊ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ ተማሪዉ ቋንቋዉን ስኬታማ እንዲሆን የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመፃፍ ክህሎትን በታላሚዉ ቋንቋ ሊያደብር ይገባል፡፡ ይህ እንዲሆንና ተማሪው በሙሉ ፈቃዳኝነት ቋንቋዉን እንዲማር ተነሳሽነት እንዲኖረዉ ያስፈልጋል፡፡

ቋንቋ ከመማር ከማህበራዊ ተግባቦት አንፃር ሲታይ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ከመማር ይለያል፡፡ ይህም ሲባል የግለሰቡን ማህበራዊ ማንነት፣ከሌላዉ ማህበረሰብ ጋር ያለዉን ተግባቦት በመመልከትና አመለካከቱን በማስተካካል ከታላሚዉ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል፣ ማህበራዊ ባህሪይ ጋር እራሱን የሚያስማማበት ሂደት ነዉ፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለዉ ግን፣ ግለሰቡ ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሽነት ሲኖረዉ ነዉ፡፡ Dorneyei (2001) እንደገለፁት ተነሳሽነት ረቂቅና ዉስብስብ ስለሆነ ለመተንተን ቢያስቸግርም የሚያስከትለዉ ዉጤት የተለየዩ ዓላማዎችን መነሻ አድርጎ አንድን ሁኔታ ለምንና እንዴት እንደሚከሰት ይገለፃል፡፡

በመሆኑም በንድፈ ሀሳቡ መሰረት የሚደረገው ጥናት የትኩረት አቅጣጫውም በማመላከቱ ባሻገር የማነሳሳት ስልትን የሚያዩበት ጎልቶ ለይቶ በማሳየት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር መመርመር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በተመረጡት ሦስት ትምህርት ቤቶች በተለይም በቂልጡ ካራ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያሉ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት አጥጋቢ ተሳትፎ ለማድረጋቸውንና ከትምህርት ገበታው ሲሸሹ አጥኚው በተከታታይ በማስተማር ስራ ላይ በነበረባቸው ቆይታዎች አስተውሏል፡፡ በመሆኑም የዚህ ችግር መንስኤ የመምህራን ተማሪዎቻቸውን መማር ፍላጎት ያለመጠበቅ ችግር ሊሆን ይችላል የሚል ሐሳብ አድሮበታል፡፡ከዚህ ጉዳይ የተነሳ የዚህን ችግር መንስኤ ለመለየት ጥናቱን አካሂዷል፡፡

- **የጥናቱ መሪ ጥያቄ**

በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው የማነሳሻ ስልት አተገባበር ምን ይመስላል; የሚለውን መሪ ጥያቄ ይዞ የተነሳ ሲሆን በሚከተሉት ንዑሳን ጥያቄዎች ዙሪያ ያጠነጠነ ምላሽ ለመሻት ጥናቱ ተካሄዷል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውስጣዊ ተነሳሽነት ለማጎልበት የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ምን ምን ናቸው;

2. መምህራኑ የተማሪዎቻቸውን ውጫዊ ተነሳሽነት ለማምጣት ምን ዓይነት ስልቶችን ይጠቀማሉ;

3. አሉታዊ ተፅዕኖን የሚያሳድሩ ተነሳሽነትን ይጠቀማሉ;

## -1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቂልጡ ካራ’ አገምሳ በልአ እና ቡኬ አከቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ዉስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ምን እንደሚመስል መመርመር ነዉ፡፡ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎችምይኖሩታል፡፡

1.መምህራን መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት በክፍል ዉስጥ መፍጠር መቻልና አለመቻላቸውን ይመረምራል፣

2.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ትምህርቱን ሲያቀረቡ የተማሪዎችን ተነሳሽነትን የሚያዳክሙ ጉዳዮችን ይለያል፣

3.ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋትምህርት ያላቸዉን ተነሳሶት በቢጤና በቡድን ተሳትፎ መጎልበት መቻልና አለመቻላቸዉን ይፈታሻል፣

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ስኬታማ የመሆንም ሆነ ያለመሆን ጉዳይ የሚፈጠረዉ ተማሪዉ ለቋንቋ ትምህርቱ በሚኖረዉ ወይም በሚያጣዉ ተነሳሽነት አማካይነት እንደሆነ Brown(1987)፤ Dorneyei(2001)፣Noels.eta (2003)ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ተጠንቶ ሲጠናቀቅ ለመምህራን የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል፡፡

- የቂልጡ ካራ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደቱ ስለሚጠቀሙበት የተነሳሽነት ስልት አተገባበር በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ፣ጠንካራና ደካማ ጎናቸዉን እንዲያዩ ሊያደርግ ይችላል፣

-የቋንቋ መምህራን ተነሳሽነትን ሲተገብሩ ለሚያገጥሟቸዉ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ሊጠቁም ይችላል፤

-የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚያደክሙ ሁኔታዎችና ተግባራት ምንምን እንደሆኑ ለቋንቋ መምህራን ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፤

-አማርኛን ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ተነሳሽነት ለተማሪዎቹ ዉጤማነት የሚኖረዉን ሚና ተገንዝበዉ በመማር-ማስተማሩ ሂደት በአግባቡ እንዲጠቀመበት ግንዛቤ ሊፈጥር ይችላል፡፡

-ለወደፊት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ለሚሹ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ተነሳሽነትን እንደ አንድ የማስተማሪያ ስልት በመቁጠር በቂ ግንዛቤን ጨብጠዉ ለራሳቸዉ እና ለተማሪዎቻቸዉ ተነሳሶትን በማጎልበት ዉጤታማ የሆነ የመማር-ማስተማር አተገባበርን እንዲፈጽሙ አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ወለጋ ዞን በርካታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት እነዚህን ትምህርት ቤቶች በሙሉ የሚያካትት አይደለም፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ትኩረት ያደረገዉ ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአገምሰ በልአ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነዉ፡፡ በተጠኚነት የተመረጡት በነዚህትምህርትቤቶች በ2009ዓመተ ምህረት በማስተማርላይ ያሉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸዉ፡፡የጥናቱ ትኩረት የመምህራን የተነሳሶት ስልት አተገባበር ላይ ሆኖ በዚህ ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ከመመርመር ዉጪ ሌሎች ከመማር- ማስተማር ጋር የተያየዙ ስነ ዘዴያዊ ጉዳዮችን ጥናቱ አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የቋንቋ፣የሥነ-ትምህርት፣የሥነ-ልቡና ምሁራንና አጥኚዎች ስለተነሳሽነት (Motivation) የፃፏቸዉ ፅሑፎች ይቃኛሉ፡፡ በመሆኑም የተነሳሽነት ምንነት፣የተነሳሽነት አስፈላጊነት፣ዓይነቶች፣ ተነሳሽነት በቋንቋ ትምህርትዉስጥ ያለዉ ሚና የተነሳሽነት አተገባበር፣ዉስጣዊ ተነሳሽነት፣ ዉጫዊ ተነሳሽነት ወዘተ ይዳሰሳሉ፡፡

### 2.2 የተነሳሶት ምንነት

ተነሳሶት የሚለዉ ቃል ከእንግልዘኛ ቃል ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ ነዉ፡፡ (Motivation) )ከሚለዉ ከእንግልዘኛ ቃል ደግሞ "Move" ከሚለዉ የላቲን ቃል የተገኘ መሆኑን Pirntrich and Schunk(2004፣4) ይገልፃሉ፡፡እያያዘዉ ምሁራኑ ተነሳሽነትን ሲገልፁ ወደ አንድ ግብ ለመድረስ የሚቀሰቅስ፣የሚገፋፋ፣የሚያነሳሳና የሚመራ ዉስጣዊ ስሜት ነዉ ብለዋል፡፡ William and Burden (1997፣120) ደግሞ ተነሳሽነትን "በነቃ አእምሮ አንድን ድርጊት ወደመፈፀም የሚያመራ ጥረትን የሚያበረታታ አእምሮታዊና ስሜታዊ ቅስቀሳ ነዉ"ይላሉ፡፡

Brown (1987፤114)በበኩላቸዉ ተነሳሶትን "በሰዉ ልጆች ላይ የሚታይ ተፈጥሮአዊ የሆነ፣አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ዉስጣዊ ፍላጎት ነዉ" ስሉ፤Oxford and Young (1993) ተነሳሶትን "(ሰዎች አንድን ነገር ለምን እንደሚተገብሩ፣ተግባሩ ለምን ያህል እንደተከናወነ እንደሚቆይና ለተግባሩ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠዉ የሚያመላክት ከዉስጥ የሚመነጭ ስሜት ነዉ" ይሉታል፡፡

እንደ Dornyei(2001፣7) አስተሳሰብ ደግሞ ተነሳሶት እንዳስበት ሃይል ዉስጣዊ ገፅታዉ ረቂቅና ዉስብስብ በመሆኑ ለመተማመን አስቸጋሪ ቢሆንም ላዕላይ ገፅታዉንና የሚያስከትለዉን ዉጤት መግለፅ ይቻላል፡፡ የተለያዩ አላማዎችን መሠረት ማድረግ አንድ ነገር ለምንና እንዴት እንደሚተገብር የሚያሳይ፣ የባህሪይን ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ዉስጣዊ ግፊት ነዉ፡፡

ተነሳሶት የሰዎችን ስሜት ወይም ፍላጎት የተነቃቃ ማድረግ የሚችል፣ማነቃቃቱንም ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሃይል እንዳለዉ Harmer (2001፣51) ጠቅሰዉ እንደገለፁት ተነሳሶት ወደ አንድ ግብ ሊያደርስ የሚችል ቀጥተኛ መስመር ነዉ፡፡

Ur (1996፣ 274) የተነሳሶትን ሚና ሲያብራሩ፣በመማር ማስተማሩ ሂደት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዉ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ተማሪዉ ለመማር በሚያደርገዉ ጥረት፣ ባለፈዉ ፈቃደኝነት እና የውስጥ ማሸት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ነዉ Gardner (1985፣10) ተነሳሶት የአንድን የቋንቋ ትምህርት የተስተምሮት ግብ ስኬታማ ወይም ስኬት አልባ ለማድረግ ወሳኝ የሆነ የፍላጎት፣የቀና አመለካከትና የጥረት ድምር ነዉ የሚሉት፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተሰጡትን የምሁራን ብያኔዎች ስንመለከት ተነሳሶት አንድን ድርጊት ለመፈፀም የሚቀሰቅስ፣የሚገፋፋ፣ዉስጣዊ ፍላጎት፣ስሜት ወይም ሀይል ነዉ፡፡ ተነሳሶት ቋንቋን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ስኬታማ ለማድረግ ና ከታለመው ግብ ለማድረስ እንደመነሻ የሚቆጠር መሠረታዊ ጉዳዩ ነው ። ይህ ከውስጥ በሚደረገወ ግፊትና ተማሪው በሚያደርገው ጥረት ይገልፃል። በመሆኑም አማርኛ ቋንቋን ለሚማሩም ሆነ ለሚያስተምሩ ተማሪዎችና መምህራን አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል።

## 2.3 የተነሳሶት አስፈላጊነት

ቋንቋን በማስተማር ሂደት ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ ተነሳሽነት ወሳኝና መሠረታዊ ጉደይ ነው፡፡Valier (1988) እንደገለፁት ተነሳሽነት በሌለበት ሁኔታ ተማሪዎች ከረጅም ግብ መድረስ ስለማይችሉ የተነሳሶትን መኖር ወሳኝ ይሆናል።Cunning Sworth (1984፣ 59-60) ደግሞ የተነሳሰትን አስፈላጊነትን እንደሚከተለው አብራርተውታል። በተደጋጋሚ እንደተረጋገጠው አንድን ተማሪ ከለመው ግብ የሚያደርሰው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቁ ችሎታ ያለው መምህርመኖር፣ አለመኖር ፣ መሠረታዊ እና ጥሩ የሆነ የመረጃ መሣሪያዎችና የመማሪያ መፃሕፍት ተሟልተው መቅረብ አለመቅረብ ብቻ ሳይሆን ተማሪው ያለው የግል ተነሳሶት ነው።

Keller(1983) ይህንን ሀሳብ ሲያብራሩ ብዙ ሞሁራን ማስተማሪያ መፃሕፍትን ያሙጥኝ ብሎ መያዝና ሥርዓት የጎዳላቸው (ረባሽ) ተማሪዎችን ሥርዓት በመስያዝ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እንደሚፈጠር ይቆጠራል ብሎ ያምናሉ፡፡እንደነዚህ ዓይነት መምህራን

ተማሪዎቻቸውን ተነሳሶት እንደሚፈጠር ማድረግአይችሉም። ስለዚህ ተማሪዎቹ ስኬታማ የመሆን ዕድላቸው እጅግ አነሰተኛ ይሆናል።

Bill (2001፣314) በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያገኘው የባህሪ ለውጥ በተነሳሽነት አማካይነት ይገልፃሉ። የቋንቋ ትምህርት በተነሳሶት የሚማር ተማሪው በተማሪው ትምህርት ዙሪያ ግንዘቤን፣ ትውሰታንና አእምሯዊ ዕድገትን ያገኛል። ይህም ሊሆን የሚችለው Harmer(2001 ፣ 52) እና Noels (2003፣ 38) እንደገለፁት ተነሳሶት ያለው ተማሪ በቋንቋትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ስለሚኖራው፣ አንድንድርጊት ለመፈፀም ይደፋፈራል ፤ አእምሯዊ፣ መንፈሳዊ እና አካላዊ ጥረት ያደርጋል ፤ ከዚህም የተነሳ ከለመው ግን ይደርሳል። በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ተነሳሽነት እንደ አንድ መሣሪያ የሚቆጠር፣ ለተማሪው እጅግ አሰፈላጊ የሆነ መሰረታዊ ጉደይ ነው ማለት ይቻላል።

## 2.4 የተነሳሶት ዓይነቶች

Ur (1996፣ 275) እንደገለፁት ተነሳሽነትን ውጫዊ እና ውሰጣዊ በማለት በሁለት ከፍላቸዋል ። እንደ ምሁራኑ ሀሰብ ውሰጣዊ ተነሳሶት የሚበለው ከግለሰቡ ግላዊ ፍላጎት የሚመነጭ ሲሆን ውጪያዊ ተነሳሶት ደግሞ በሌሎች አካላት አማካይነት ከሚደረጉ ግፊቶች የተነሳ የሚፈጠር ነው፡፡

Harmer(1991) እና Ur (1996) ውስጣዊ ተነሳሶት የቋንቋ ተማሪዎች በክፍል ውሰጥ የሚዩዋቸው ሁኔታዎች የሚመነጭ ሲሆን ውጪያዊ ተነሳሶት ግን የቋንቋ ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍሉ ውጪ በሚያጋጥሟቸው ተፅዕኖዎች አማካይነት የሚመጣ ነው ይላሉ። እዚህ የተነሳሶት ዓይነቶች በውስጣዊ ግፊት እና በውጫያዊ ግፊት አማካይነት ትምህርታቸውን የሚማሩ ሁለት ዓይነት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውሰጥ እንደሚኖሩ እንዲንገነዘብ ያደርጋል። እነዚህን የተነሳሶት ዓይነቶች በዝርዝር ከዚህ በታች ለማየት ይሞከራል፡፡

### 2.4.1 ውስጣዊ ተነሳሶት

ውስጣዊ ተነሳሶት ከሰው ልጅ ስሜት የሚመነጭ ተግባር መሆኑን ምሁራን ይስማማሉ። Pintrich and schunks (2002 ፣255) ፤ Deci (1980፣20)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት ውስጣዊ ተነሳሶት የሰዉ ልጅከአከባቢ ጋር በተለመደ መልኩ በራሱ መወሰን የሚያስችል ሰብአዊ ፍላጎት ነው ። ፍላጎቱ በፈቃዳኝነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ውስጣዊ ሀይሉን በመጠቀም ፍላጎቱን የሚያረካበት በፍላጎቱ መካከል ያሉትን ውጥረቶች የሚያረግብበትእንዲሁም ፍላጎቱን ይዞ የሚያቆይበት ነው።

ውስጣዊ ተነሳሶት በተማሪዎች ውስጥ ለሚኖረው ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥበት ተለውጦ ነው ይህም ተማሪዎች ለመማር በላቸው ጉጉት፣ ለማወቅ ባላቸው ፍላጎትና በታላሚው ቋንቋብቁ ለመሆን በሚያሳዩት ስሜት ጎልቶ እንደሚታይ Burden (2000)ን ጠቅሰው አብራርተዋል። ሰለዚህም ተነሳሶት አንድን ነገር ለመፈፀም የሚገፋፋ ክስተት ሆኖተግባሩም የሚከነወነው ከተማሪዎች በመነጨውስጣዊ ፈላጎትና መሻት በመሆኑ አስደሳችና መንፈስን የሚያረካ ሊሆን ይችላል Noels (2003፣ 38)። የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሶት ከራሳቸው የሚመነጭ በመሆኑ መምህሩ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን እንዲማሩና እንዲከታተሉ በማንኛውም መንገድ እንዲገፋፋቸውና እንዲጎተጉታቸው አይጠበቅበትም፡፡ተማሪዎች ፍላጎታቸውን ለመፈፀም በማንኛወም ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያገኘው ከአንድ አቅጣጫ ወይም ከራሳቸው ስለሚሆን መድረሻ ግቡ የተወሰነ ሊሆን ይችላል።

ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ተነሳሶት ከመደረሻ ግብ ጋር ቁርኝት አለው ማለት ይቻላል። ተማሪዎች የሚደርሱበትም ግብ እውነተኝነትና ዘላቂ ውጤት ይታይበታል። ምክንያቱም ተማሪዎች ከውጭ ከሚያገኟቸው ተነሳሶት ይልቅ በሚያስተውላቸው ነገሮች እና ከውስጣቸው ከሚወጣው የተነሳሶት ሂደት ላይ ስለሚሳተፉ ነው። ስለዚህ ውስጣዊ ተነሳሶት በመማር ማስተማር ሂደት ውጤት የሚያሰገኝ መሳሪያ ነው (Kosta 2006፣Elliot etal.2005) ማለት ይቻላል።

Harmer (1991፣ 4) እንደገለፁት፣ ቋንቋ በመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች የሚደረግ ውጫያዊ ተነሳሶት እምቢዛም ባለመታየቱ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ይታያል፤ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አሉታዊ

አመለካከት እንዲኖረቸው ውስጣዊ ተነሳሶት ያስፈልጋቸዋል። ይህም ለቋንቋ ትምህርቱ ስኬታማነት ስለሚያግዝ ለቋንቋ ትምህርቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ በሚችሉ ተለውጦች ማለትም በመምህሩ፣ በማስተማር ዘዴው እና ተማሪዎች በሚያገኙት ውጤት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

Noels (2003፣38) በመጥቀስ የሚከተለውን ሀሰብ አስፍረዋል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሶት ያላቸው ሰዎች አንድን ተግባር ለመምረጥም ሆነ ለማከነወን ነፃነት አላቸው። በተጫማሪም የችሎታ ብቃታቸውን ስለሚያ ጎለብቱ ፈታኝ የሆነ ጉዳዮችን ማንሳት እና ችግሮችን ማቃለል ይችላሉ። ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ተነሳሶት በሦስት ዓይነት አቅጣጫ ይከናወናል።

1. ዕውቀትን ለማግኘት፡- ግለሰቡ ከአዳዲስ ሀሰቦች ጋር ራሱን ለማስማማት እና ተግባሮችን ለመከናወን እንዲሁም ዕውቀትን ለማሳደግ ሲል ውስጣዊ ተነሳሶት ይኖረዋል።
2. ተግባርን ለመፈፀም፡- ግለሰቡ አንድን ነገር ለማማከር ወይም ለማከናወን እንዲሁም ውጤታማ የሆነ ግብ ላይ ለማድረስ ተነሳሶት ይኖረዋል።
3. ለማነቃቃት፡- ግለሰቡ አንድን ተግባር በሚያከነውንበትወቅት ደስታን፣ አድናቆትን፣ እርካታን ወዘተ ለማግኘት ውስጣዊ ተነሳሶት ይኖረዋል።

   እነዚህ የውስጣዊ ተነሳሶት ሂደቶች ግለሰቡ አንድን ተግባር በሚያከናወኑበት ጊዜ ከድርጊቱ ዕዉቀት ለማግኘት በተገኘዉ ዕውቀት ውጤታማ ለመሆን እና በዉጤቱ ለማርካት የሚያግዙ ናቸው። በአጠቃላይ ውስጣዊ ተነሳሶት ከሰው ልጅ ስሜት፣ ፍላጎት፣ አንድን ነገር የማድረግ ምኞት፣ በጉጉት ለይ ተመሠርቶ በሚከናወን የተግበር ሂደት ላይ ጎልቶ ሊታይ የሚችል ነው።

ይህም ሂደት ግለሰቡን ወደ አንድ የረጅም ጊዜ ግብ ያደርሳል ። ይህ ውስጣዊ ተነሳሶት በተማሪዎች ላይ ከታየ የመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማ እንዲሆን የሚያግዝ ቀና መንገድ ይሆናል፡፡

### 2.4.2 ውጫዊ ተነሳሶት

ውጫዊ ተነሳሶት የተነሳሶት  አንዱ አካል ሲሆን የሚፈጠርበት መንገድ እና የሚያገኘው ግብ ከውስጣዊ ተነሳሶት የተለየ ነው ። vanlier (1988 ፣1) “ውጫዊ ተነሳሶትንበሥራ ላይ ለመዋል እንደተበደሩት በኃላም እንደሚከፍሉት ገንዘብ ይቆጠራል” ማለትም ውጫዊ ተነሳሶት ከግለሰቡ ውጪ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን የትምህርት ተግበራት ለመከናወን  እና ለመማር ካለፍላጎት እና ጉጉት የሚመነጭ  ሳይሆን በተለየ ሁኔታ ከተለያዩ አካለትና ከአንደንድተፅዕኖዎች ማነቃቂያዎችን በመቀበል የሚመነጭነው። እነዚህም ማነቃቂያዎች ከመምህራን፣ ከወላጆች፣ ከጓደኞች፣ የሚገኙ ሽልማቶች ምስጋናዎች፣ ምጋቤምላሾች ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉBrown (1987፣ 115 )፤ Ur (1996 ፣ 275)፡፡

በውጫዊ ተነሳሶት አማካይነት የሚገኘው ግብ በውስጣዊ ተነሳሶት አማካይነት ከሚገኘው ግብ የተለየ ነው ። ተማሪዎች ውጫዊ ተነሳሶትን ያካበቱ ከሆኑ በፈተናዋሩ ውጤት ማግኘት፣ ጥፋትን በመቀነስ ቅጣትን ማስቀረትን የመሳሰሉትን የአጭር ጊዜ ግቦችን ያገኛሉEllott etal (2005 ፣14) ፣ Noels 2003፣39) ፡፡

Dournyei (1998 117-135) ትውረት መሠረት ውጫዊ ተነሳሶት ሦስት ደረጀዎች አሉት። እነሱም፡-

1. በውጫዊ ተፅዕኖ የሚፈጠር ተነሳሶት፡- ከግለሰብ ውጪ በሆኑ ምንጮች ላይ የተመሠረቱ ተግባራት ናቸው ። ይህም ማለት ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ሊታዩ የሚችሉት ጥቅማ ጥቅምን መሰረት ያደርጋሉ።ይህ ዓይነቱ ለጥቅማ ጥቅም ሲባል የሚፈጠር ተነሳሶት (Gadner and macitre (1993) ጥቅማዊ ተነሳሶት እንደሚባል ይገልፃሉ።
2. ከራስ  በሚመነጭ ጫና የሚፈጥር ተነሳሶት፡- ተማሪዎች  አንድን ተግባር ሲያከናውኑ ሲሉ ከራሳቸው ጋር የማይጣጣሙ ግለሰባዊ ግፊቶች እንዲኖራቸው ያደርጋል። ምንም እንኳን የግፊቱ ምንጮች አሰፈላጊ ቢሆኑም ተማሪዎች የራስ እድል በራስ የመወሰን ሁኔታ አይታይባቸውም። ተማሪዎች ከግፍቶች ጋር ይጋፈጣሉ እንጂ በራሳቸው ምርጫ ላይ ተመሰርተው ድርጊትን አይፈፅሙም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ተማሪዎች የሁለተኛውን ቋንቋቸውን ሲለምዱ ቋንቋውን  ለመናገር ስለሚያፍሩ ቋንቋውን በቶሎ

መልመድ አይችሉም፡፡ የተማሪዎች ሙከራ ሁልጊዜ ስህተት ወይም ጥፋት እንደይፈፅሙ ብቻ ነው፡፡

3. በተለየ ምክንያት የሚፈጠር ተነሳሶት፡- የራስ ዕድል በራስ የመወሰን የሚታይ በት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ተነሳሶት ተማሪዎች የሚሞክሩት የሚሰጠቸውን ተግባር ከፍ ለማድረግ ነው ምክንያቱም አንድን ነገር ለማድረግ ግላዊ የሆኑ አስፈላጊ ምክንያቶችን ለመፈፁም የራሳቸው ምርጫ አላቸው ይህም ከግብለማድረስለሚደረገው ክንውን አስፈላጊነው፡፡ ለምሳሌተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርታቸውን ለማሳደግ በቃላቸው በማደጋገም እና በማለማመድ ቋንቋዉን ያደብራሉWillian and Burden (1997፣123)፤ Noels (2005፣ 39)፡፡

በአጠቃላይ በውስጣዊ ተነሳሶት እና በውጫዊ ተነሳሶት መካከል ልዩነት እንደሚታዩ ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መረዳት ይቻላል፡፡ በተጫማሪም Hay wood (1971) እንደሚገልፀት ውጫዊ ተነሳሶት ምኞትን፣ደህንነትን፣የበላይ ሆኖመታየትን፣የሚያስገኝ ሲሆን ውስጣዊ ተነሳሶት ደግሞ ኃላፊነት፣ የፈጠራ ችሎታን ፣ ሥነ- ልቦናዊ እርካታን፣ በራስ ብቁ መሆንን ያስገኛል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሶትን በዝርዝር ለማየት ተሞክሯል። በዚህም መሠረት ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሶትን እንደሚከተለው ማነፃፀር ይቻላል፡፡

**የተማሪዎች ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሶት**

| ውስጣዊ ተነሳሶት | ውጪያዊ ተነሳሶት |
|---|---|
| ተነሳሶቱ ከውስጥ ፍላጎትና ጉጉት ይመነጫል | በሌላ አካል ከሚቀርብ ምስገና፣ ሽልማት ወዘተ ይመነጫል |
| የረጅም ጊዜ ግብ ወይም ዓላማ አለው | የአጭር ጊዜ ግብ ወይም አላማ አለው |
| በሚከናወነው ጉዳይ ላይ ስኬታማ ያደርጋል | የሚከናወነው ጉደይ ስኬታማነቱ እንደሚኖረው የግፊት መጠን ይለያያል |
| ደስታንና እርካታን ያስገኛል | ምኞትን፣ ደህንነትን ያስገኛል |

### 2.4.3 ተነሳሶት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና

ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ከዳር ለማድረስ የቋንቋ መምህሩ፣ የተማሪዎችና የሌሎች አጋዥ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው stren (1983፣18) እና Ur (1996፣ 276) እንደገለፁት በጥንት ጊዜ የቋንቋ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በመምህሩ አማከይነት ብቻ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ መምህር ተኮር የትምህርት አሠጣጥ ሂደት በአሁኑ ጊዜ በተማሪው ተሳትፎ ተተክቶ ይታያል፡፡ ተማሪው በቀጥታ ከመምህሩ ከሚማር ይልቅ በክፍል ውስጥ ለሚደርገው ተግባራዊ ተሳትፎ ትኩረትበመሰጠት የተስተምህሮቱ ሂደት ተጋሪ ሆኗል፡፡ በተጫማሪምተማሪው የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ሂደት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋ ተግባቦታዊ ሂደት ላይም ነው፡፡ በመሆኑም ቋንቋን መማር ለትምህርት ዓላማ ብቻ የሚካሄድ ሳይሆን አመለካከትን ለማሻሻል፣ ማህበራዊ እሴቶችንና ሥርዓቶችን ለማወቅ እንዲሁም ማንነትን ለመለወጥ ሰይቀር የሚተገብር ጉደይ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ተማሪው ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሶት ሲኖረውና በክፍል ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው፡፡ Narden and lin (2000)ን ጠቅሰው እንደብራሩት የተነቃቁና ተነሳሶት ያላቸው ተማሪዎች በቋንቋ ክንውን ላይ ሙሉ ለሙሉ ተሳትፎ ሰለሚያደርጉ ተነሳሶት ከሌላቸው ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ክሂላቸውን ለማሳደግ የተሻለ ዕድልና አጋጣሚ አላቸው፡፡ ተነሳሶት የሌላቸው ግን በቋንቋ ትምህርታቸው ዝቅተኛ ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል Gardener and Lambert (1972) እንደ ሚያመለክቱት በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ቋንቋን መልመድ ወይም መማር ማለት ከሰው ጠቃሚታ አንፃር ሲታዩ ማህበረሰባችን እንደሚያገናኝ ድልድይ ይቆጠራል፡፡ በተግባቦቱም ረገድ ግለሰቡ ያለው ተነሳሶት ለቋንቋው ማደግም ሆነ ውድቀት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ተመራማሪዎች ተለምዶአዊ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ በቋንቋ ውስጥ በግልፅ የሚታወቁ ሁለት ምዴሎች እንደሉ አስረድተዋል፡፡ እነሱም ውሕደታዊ ተነሳሶት እና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሶት የሚበሉናቸውእነዚህ የተነሳሶት ዓይነቶች Ellis (1994፣ 75)፤ Harmer(2001) Gardner (1985) Dornyei(2001) እና ሌሎች የሥነ ትምህርትና የሥነ-ልቦናባለሙያዎች በዝርዝር አብራርተዋል፡፡በውህደታዊ ተነሳሶት ግለሰቡ ከህብረተሰቡ ጋር ተግባቦት ማድረግ ሲፈልግወይም ግለሰቡ ከህብረተሰቡ ጋር በቋንቋ ተመሳስሎ መኖር ሲያስብ ራሱን ለቋንቋው በማጋለጥ ቋንቋውን ይለምዳል፤ ያውቃል፡፡

በአንፃሩም ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሳት ሲባል ግለሰቡ በታላሚው ቋንቋ አስፈላጊ ጽሑፎችን ለማንበብ፣ የሥራ ዕድገትና የመሳሰሉትን ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ሲባል ቋንቋውን የምለምድበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ተነሳሶት በብዙዎቹ ምሁራን ዘንድ እንደ ደካማ የተነሳሶት ዓይነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ምክንያቱም የረጅም ጊዜ ውጤትና ጥሩ ውጤት ማስገኘት ባለማስቻሉና የተማሪውን ስብዕና የመለወጥ አቅሙ ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋና የሰነ ልቦና የምሁራን እንደብራሩት አንደንድተማሪዎች የታላሚዉን ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል አኗኗር ይማርኳቸዉና በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ መቀላቀልና በቋንቋው ብቁ ችሎታ ያላቸው መሆን ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ፍላጎት ደግሞ ውሕደታዊ ተነሳሶትን ያስከትላል፡፡

በአጠቃላይ ተነሳሶት ተማሪዎች ቋንቋ ትምህርታቸውን ለመማርና በቋንቋው ብቁ ለመሆን በሚደረግ መልካም ግንኙነት ከመማሪያ ክፍልውጪ በሚደረግ ተግባቦታዊ ክንውን እንዲሳተፉ የሚያደርግ ኃይል ነው፡፡ተነሳሶት ያለው ተማሪ ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ውህደትን በመፍጠር የቋንቋው ተጠቃሚ በመሆን ወይም ደግሞ እንደሥራ ዕድል ማግኘት፣ሽልማት መቀበል፣ ወዘተ የመሰሰሉት ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ሲል ቋንቋውን ሊማር ይችላል፡፡ በመሆኑም በማንኛውም መንገድ ቢሆን ቋንቋን ለመማር ተነሳሶት ዋና ጉዳይ መሆኑ የማያጠራጥር ነው፡፡

## 2.5 የተነሳሶት ተለውጦዎች

ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ተነሳሶትን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ተለውጦዎች አሉ፡፡ ተለውጦዎቹ በተስተምህሮቱ ወቅት ወይም ከተስተምህሮቱ ውጪ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው፡፡ Pintrich and schunks (2002) የተነሳሶት ተለውጦዎችን እንደሚከተሉ በዝርዝር አስፍረዋቸዋል፡፡

### 2.5.1 ማህበረሰቡ ለቋንቋ ያለው አመለካከት

ማህበረሰቡ ምንም እንኳን በክፍል ውስጥ ተገኝተው የቋንቋ ትምህርቱን ባይከታተልም በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት የራሱ የሆነ አመለካከት ይኖረዋል፣ ማህበረሰቡ ለታላሚው ቋንቋ ምንያህል ግምት ይሰጠዋል?ተማሪዎችስ ቋንቋውን ለመማር ምን ያህል ፍላጎት አላቸው?

ለምን? የሚሉት ጥያቄዎች የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ዓይነት እንደሆነ ሊያንፀባርቁ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች በማህበረሰቡ ለቋንቋው የሚሰጡውን አመለካከት በመያዝ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸው ተነሳሶት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል፤ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ከማህበረሰቡ ጋር ለረጅም ጊዜ አብረው የኖሩ በመሆናቸው የማህበረሰቡ አመለካከት በእነሱ ሊንፀባረቅ ይችላል Harmer (2001'52) ፡፡

### 2.5.2 ወላጆች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና ያለቸው አመለካከት

ወላጆች በቤት ውስጥ ስለታላሚው የቋንቋ ትምህርት የሚሰጡት አስተያየት በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖንያሳድራል፡፡ ይህ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ተማሪዎቹ ቋንቋ ትምህርታቸውን ተነሳሶት እንዲጨምር ወይም እንዲዳከም ያደርጋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ጉዳይ በቋንቋ ተስተምህሮት ወቅት ጉልቶ ሊታይ ይችላል petty (2004) ፡፡

### 2.5.3 ቢጤዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና አመለካከት

በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርቱን የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ግምት የተለያየ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲከናወኑ የቢጤዎቻቸውን አመለካከት እየተለመዱ ይሄዳሉ፡፡ ይህም ማለት ቢጤዎቻቸው ትጉህና ታታሪ ከሆኑ ጓደኞቻቸውም ትጉህ ለመሆን በመሞከር ተነሳሶታቸውን ይቀሰቅሳሉ፡፡ የቢጤዎቻቸው ተነሳሶት የተደከመ ከሆነ የጓደኞቻቸውም ተነሳሶት እየተደከመ ሊሄድ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በተስተምህሮቱ ወቅት ተማሪዎች በብጤዎቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ግምትን ወይም ዋጋን ማግኘት ይሻሉ፡፡ ስለሆነም ቢጤዎቻቸው በነሱት ላይ የሚኖራቸው አመለካከት በተነሳሶታቸው ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል Harmer (2001፣ 53፤ Petty 2004፣ 45)፡፡

### 2.5.4 የቋንቋ መምህሩ

አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን የሚያስተምረው መምህር በተለየ መልኩ የተማሪዎቹን ተነሳሶት ሊያጠናክር ወይም ሊያዳክም ይችላል፡፡ ይኸውም የቋንቋ መምህሩ ትጋት፣ ድክመት ስብዕና፣የትምህርት አቀራረብ ስልቱ ወዘተተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ትልቅ ወይም

ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ትልቅ ሚና አለው ማለት ይችላል UR (1996፣ Pintrich and schunk 2002)፡፡

በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተፅዕኖ ሊያስከተሉ የሚችሉ የመምህር ባህሪያት መኖራቸውን Parrott (1993) ያስረዳሉ እነዚህ በህርያት የሚከተሉ ናቸው፡፡

1. ትጉህነት ወይም ቆራጥነት የሚታይበት፣
2. ከተማሪዎች ጋር በጎ የሆነ ግንኙነትን የሚፈጥር፣
3. ከተማሪ ወላጆች ጋር በጎ የሆነ ግንኙነት የሚያደርግ መምህር ሊሆን ይችላል፡፡

ምሁሩ አክለው እንዳብራሩት የቋንቋ መምህር ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት ለተማሪዎቹ በማለየት ተማሪዎቹ የሱን ፍላጎትና ተነሳሶት በመመልከት እንዲነቃቁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ለትምህርቱ ውስጣዊ ተነሳሶት ለማይታይባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ስልቶችን በመለዋወጥ መሠረታዊ ውስጣዊ ተነሳሶት እንዲኖራቸው በትጋት ማስተማር ይጠበቅበታል፡፡ የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎችን ስነልቦና በመረዳት ከምን ዓይነት ቤተሰብ መሀል እንደመጡ ክትትል በማድረግ ከተማሪዎች ወላጆች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ለትምህርቱ ፍላጎት እንዲያድርባቸውና ተነሳሶት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን መምህር ጠቀስ በህሪዎች በተማሪው የቋንቋ ተነሳሶት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

### 2.5.5 የማስተማሪያ ዘዴ

በመማር-ማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ እነዚህ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከተማሪዎቹ ስሜት እና ችሎታ ጋር ሊጣጣሙ ወይም ደግም ላይጣጣሙ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ተነሳሶት ለማስተማሪያው ዘዴው እንደሚስጡት ግምት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል Harmer (2001)፡፡

### 2.5.6 የቋንቋ ትምህርቱ ትግበራዎች

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለየዩ የተግባር ክንውኖችን እና መልመጃዎችን እንደተገብሩ ይደርጋል ለዚህ ትግበራዎች የተሰጣቸውን ርዕስ የሚያነሱት ርዕስ ጉደይ የላቸዉ ርዝማኔና አቀራረብ ስልቶቻቸው መስብህነት ያላቸው ወይም የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ከነዚህም የተነሳ በትግበራዎቹ አማካይነት የተማሪዎቹ ተነሳሶት ሊጠናከር ወይም ሊደክም ይችለል ማለት ነው Petty (2004፣Ur 1996 Pintrich and schunk 2002)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ማህበረሰቡ፣ ወለጆቹ፣ ቢጤዎቹ፣ የቋንቋ መምህሩና በክፍል ውስጥ የመኖሩ ሁኔታዎች ማለትም መምህሩ የሚጠቀምበት ማስተማሪያ ዘዴና ትምህርቱን ለማስፈፀም ተዘጋጅተው የቀርቡት የተግባር ክንውኖችና መልመጃዎች መምህሩ የማነሳሻትምህርቱን ያላቸውን ተነሳሶት ደረጃ ሊያጎለብቱና ሊያደክም፣ ተማሪዎቹን ውጤት ሊያሰገኙ ወይም ውጤት ሊያሰጡ የሚችል ተለውጦዎችማለት ይቻላል፡፡

## 2.6 የተነሳሶት ብልሃቶችን በአማርኛቋንቋ ትምህርት ክፍል ውጥ ስለመጠቀም

ቋንቋን በመማር ማስተማሩ ሂደት ሰፊድርሻ የሚሰጠው ተነሳሶት ከትምህርት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው መሆኑን አጥኚዎች ያስረዳሉ፡፡ Dornyie(2001) እና Young(1999) እንደሚያብራሩት፡- ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ ለማድረግ በመጀመሪያ ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው የቋንቋ መምህሩ የተለያዩ ብልሃቶችንና ስልቶችን መጠቀም ሲችል ነው፡፡ የሚጠቀምባቸው የተነሳሶት ብልሃቶች ከቋንቋ ትምህርቱ፣ ከተማሪዎች አከባቢና የአኗኗር ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ ቢሆኑ ውጤትና ለውጥን ለማምጣት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

Ur (1996)፣ Gardener (1977)ን ጠቅሰው እንደገለፁት በአሁኑ ጊዜ መምህራን ተማሪዎችን ተነሳሶት ለመፍጠር እንደ ዋነኛው መሣሪያ የሚጠቀሙበት ስልት ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ይሁንና ተማሪዎቹ የተነሳሱ የሚሆኑት መምህራኑ ተግበራቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያበረታቱበትን መንገድ የቀየሱ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም የቋንቋ መምህራኑ ኃላፍነትን መውሰድ ይኖርባቸዋል Pintrich and schunk(2004፡ 4) እንዳመለከቱት፡- መምህራን መጨነቅ ያለባቸው ‘ ተነሳሶት ምንድን ነው” በሚል ጉዳዩ ላይ ሳይሆን ‘ ምን፣ መቼና እንዴት አስተምረንየተማሪዎችን ተነሳሶት መምጣት እንችላል” በሚል ሀሰብ ላይ ነው፡፡ ይህ እንደሆን ደግሞ Dornyei (2001) እና Petty (2004) ሀሳቡን እንደብራሩት መምህራን “ carrot and stick” ሽልማትና ቅጣትና” የሚለውን የማበረታቻ ስልት በመቀነስ በቂና ምቹ በሆኑ የማነቃቂያ ወይም ማበረታቻ

ስልቶቹን ቢጠቀሙ ወደሚፈልገው ወጤት መምራት ይችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚከተሉትን ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተግባራዊ ያስፈልጋቸዋል፡፡

1.መሰረታዊ የተነሳሶት ጉዳዮችን መፍጠር

2. ተፈላጊውን ተነሳሶት ማንቀሳቀስ

3. የተማሪዎችን ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ ናቸው፡፡ እነዚህን ዋና

ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ይሞከራል፡፡

### 2.6.1 መሠረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን መፍጠር

Dornyei (2001) መሠረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች አስፍረዋል፡፡ የተነሳሶት ብልሃቶችን ሁሉንም በአንድ ጊዜ መጠቀም አይቻልም፡፡ ተነሰሶትን ከፍ ለማድረግና ከውጤት ለማድረስ በቅድሚያ የሚከተሉ ቅድመ ሁኔታዎችን መሟላት ያስፈልጋል፡፡ እነሱም፡-

- ትክክለኛ የመምህር በህሪይና ጥሩ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት፣
- አስደሳችና አጋዥ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ፣
- ጥሩ የቡድን ሥርዓት የያዝ የተማሪ ቡድን ጥምርታ ናቸው፡፡

#### 2.6.1.1 ትክክለኛው የመምህር ባህሪይና ጥሩየመምህር ተማሪ ግንኙነት

የመምህር በህሪይ ጉልህ የሆነ የተነሳሶት ማሰሪያ ነው፡፡ በመምህራኑ የሚደረግ ማንኛውም ነገር በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተፅዕኖ ያሰድራል የተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚያሳየውን በባህሪይ በመከተል የሚመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ Dornyei (2001) ተጨማሪ በተስተምሮቱ የሚያድረጉት ጥረት የላቀ የሚሆነው በመምህሩ አማካይነት ነው፡፡ይኸውም መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር የሚያደርገው መልካም የሆነ ግንኙነትና 'ተማሪ ተኮር" በሆነ የትምህርት አስጣጥ ሂደት ውስጥ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር በሚያሳየው ቀረበታ ነው Rodyers (1991)፡፡

Alison (1993) መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚደርጉት የእርስ በእርስ መተማመንና መከባበር በክፍል ውስጥበሚከሄደው የተግባር ክንውን ላይ ወሰኝነት እንዳለው ይገልፃሉ፡፡

በተጫማሪም የመተማመንና በመከባበር ሁኔታ ትጋትንና የትምህርት ጉጉትን በመምህሩ ላይ ይፈጥራል ለማስተማር የሚታጋው መምህር ራሱን መስዋዕት በማድረግ በቃልና ቃል-አልባ በሆኑ ስልቶች አማካይነት ትምህርቱን ያቀርባል፡፡ ይህንንም በማድረጉ መምህሩ በተማሪዎቹ ዘንድ እንዲጥሩ አርአያሊወስድ ይችላል፡፡በአንፃሩ Wright (1987) ከተማሪዎቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌላቸውን መምህራን እንዲህ በ ማለት ይገልጿቸዋል፡፡ መምህራን እንደ አለቃና መሪ ብቻ ሆነዉ የመማር ማስተማሩ ሂደቱን ከሚያከናወኑ ከሆነ አቃባይና መጋቢ ብቻ ስለሚሆኑ የተማሪዎቹ ተሳትፎና ለትምህርቱ ያላቸው ጉጉት ጎልቶ ሊታይ አይችልም፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች የመምህር-ተማሪ መልካም ግንኙነት መገለጫ መንገድ እንደሆኑ Dornyei (2001) ያስረደሉ፡፡

- ተማሪዎች የመምህሩን እርዳታ ሲጠይቁ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣
- ተማሪዎችን እንደረዳት ሆኖ መቅረብ፣
- ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን በግል ለመወያየት መፍቀድ፣

### 2.6.1.2 አስደሳችና አጋዥ የክፍል ዉስጥ ሁኔታ

የክፍል ውስጥ ሁኔታማለት Pintrich and shunk (2002-322) ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ማህበራዊ ሥነልቦናዊና ስሜታዊ ባህሪይን የተላበሰ የመማሪያ ክፍል ማለት ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ወይም ፈዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚፈጥረው ደግሞ አብዘኛውን ጊዜ በመምህር-ተማሪ መልካም ግንኙነት አማካይነት ነው፡፡ የመምህር ተማሪው መልካም ግንኙነት የሚካሄደው ተማሪዎቹ ነፃነት እንደሚሰማቸው በሚያስችል መልኩ ከሆነ በክፍል ውስጥ ንቁ ትሰተፎ ይኖራል፡፡ የንቁ ተሳትፎ መኖርደግሞ ተነሳሶት እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን የመምህር ተማሪ መልካም ግንኙነት ነፃነትን የሚያስጠና መምህሩን በበላይነት የሚመራው ከሆነ የክፍሉ ተሳትፎ ፌዝ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎቹ ተነሳሶት እየተዳከመ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡

Young (1999) የክፍል ውስጥ ሁኔታን በተመለከቱ የሚከተለውንሀሰብ ሰንዝርዋል፡፡ የክፍል ውስጥ ሁኔታ በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ያሰድራል፡፡ ይህም ማለት ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ ከለተማሪዎቹ በተስተምህርቱ ወቅት ሃሰባቸውን አመለካከታቸውን እምነታቸውን ለመግለፅ አይቸገሩም፡፡ ተማሪዎች አመለካከታቸውን በነፃነት መግለፅ መቻላቸውን የቋንቋችሎታ የማሻሻል ጥረታቸውን ከፍ

እንደል ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ሊያውኩና የመማር- ማስተማር ሂደቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተለውጦዎችን መቆጠጠርና ምቹ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ለመፍጠር መጣር ይኖርባቸዋል፡፡

ያልተመቻቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁኔታ ማለትም የቋንቋ ትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎች የእርስ በእርስ አለማደማመጥ መምህር-ተማሪ መልካም-ግንኙነት አለ-ታዊነት ተማሪዎችን ጭንቀትና ብቸነት እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለሆነም በተማሪዎች ላይ የሚፈጠሩ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን አዝናኝና የሚያነቃቁ ማድረግ ይጠበቅበታልUr (1996፡ 277) Good and Brophy (1994፣ 215)፡፡

### 2.6.1.3 ጥሩ የቡድን ሥነ-ሥርዓትን የያዘ የተማሪ ቡድን ጥምርታ

Pintirich and Schunk (2002’ 309) በክፍል ውስጥ የሚደረግ የተማሪዎችን አደረጃጀት የቡድን አወቃቀርን በተመለከተ ሦስት ዓይነት አደረጃጀት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ እነሱም ትብብራዊ፣ ውድድራዊ ና ግለሰባዊ ናቸዉ፡፡በነዚህ ተሳትፎዎች ዉስጥ ተማሪዎች አንዱ ከአንዱ የመማማርና የመተጋጋዝ አዎንታዊ ገፅታ ያለው የፉክክር ና የተወዳደሪነት መንፈስ በግል የመጣርን ልምድ ተማሪዎች ያካብታል፡፡ እነዚህ አወቃቀር ስልቶች ለተማሪዎች ተነሳሶት ጠቃሚታ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል Dornyei (2001) የቡድን ሥራን በተመለከተ የሚከተለውን ሀሰብ ሰንዝርዋል፡፡ በማንኛውም የቡድን አደረጃጀት ውስጥ ተነሳሶት ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁለት ጉደዮች አሉ፡፡

እነዚህም ጉዳዮች የቡድን ጥምርታና የቡድን ሥነ ሥርዓት ናቸው፡፡ የቡድን ጥምርታ የእኛነት ስሜት የሚታይበትና አካላቱ ለቡድናቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳይበት ነው፡፡ በአንፃሩ ይህ ካልሆነ ግን የትብብር መንፈስ እጦትን ከማለየቱም በላይ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ቁርጠኝነት እንዲቀንስ በማድረግ ውጤትን ወደ ማጣት ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ያደርጋል፡፡

የቡድን ጥምርታን የሚያደርጉ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች መኖራቸውን Dornyei (1998) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

1. የቡድኑ አበላት እርስ በርሳቸው ይማማራሉ; መምህሩም ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲለዋወጡና ዕውቀት እንዲያገኙ እገዛ ያደርጋሉ።
2. መደበኛ የሆነ የክፍል ውስጥ የመቀመጫ ቦታ ሥርዓትን በማስቀረት ተማሪዎች በቢጤ ውይይት በአነስተኛ ቡድን ምሥረታ; በሚና ጫወታ ወዘተ በማደራጀት እርስ በርሳቸው መልካም ግንኙነትእንዲያደርጉ ያግዛል፡፡
3. ተማሪዎች ለጋራ ዓላማቸው እርስበርስ በመተባበር ችግሮችን በማቃለል መፍትሄዎችን ይፈልጋሉ፡፡
4. በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ አባላት እርስ በርሳቸው እየተወዳደሩ በመካከላቸው መልካም የሆነ ግንኙትን ይፈጥራሉ፡፡

የቡድን ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ Dornyei (1998፡142) ሀሰብ አስፍረዋል፡፡ የቡድን ሥርዓት ሲወጣ የቡድኑ አባላት የተሰማሙበትን ሃሳብ ማፅደቅ ይሆናል፡፡ ሥርዓቱም ተማሪዎቹ በእርስ በርስ ተራክቦ ወቅት ተግበራዊ የሚደርጉት ነው፡፡ ባጭሩ መምህራን መልካም ግንኙነት ያለው ቡድን እንዲመሠረት በማድረግ የተማሪዎችን ተሳትፎ ቢያጎለብቱ ተነሳሶታቸው እየጨመረ ይሄዳል ማለት ይቻላል፡፡

### 2.6.2 ተፈላጊውን ተነሳሶት ማንቀሰቀስ

Roders (1991), Rosser and N,cholson (1984) እና Brophy (1998) እንደገለፁት ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ አንድን ነገር የማወቅ ጉጉትና አከባቢውን የመመርመር ፍላጎት አለው፡፡ ተማሪዎችም ከሚመሩት ትምህርት ውስጥ የሚያስደስታቸውን ነገር ስለሚፈልጉ ለትምህርት ጉጉት ያላቸው ይመስላል፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች አንድን ነገር የማወቅ ፈላጎት ለውጥን በማያሰዩ አንዳንድ የትምህርት ቤት ተፅዕኖዎች ምክንያት ሊዳከም ይችላል፡፡ ለምሳሌ የትምህርት ቤት ተማሪውን መከታታያ ቅፆች (የስም መጥሪያ ቅፆች) ለዚህ ተጠቃሽ ማስረጃ ይሆናል።

Brophy (1998) አያይዘው እንዳብራሩት ምንም እንኳን ሌሎች አማራጮች ቢኖሩም ብዙ መምህራን ትክክለኛ ተነሳሶትን ከፍ የማድረጊያ መንገድ ብለው የሚያምኑት በክፍል ውስጥ የተሰጡትን ክንውኖች ለማሳካት የሚያደርጉትን ጥረት ነው። ይሁንና እነዚህ የክፍል ውስጥ ክንውኖች ምናልባት ላይመርጧቸው ወይም ደግሞ ላይደሰቱባቸው ይችላሉ፡፡መምህራን አነቃቂ የሆኑ ሁኔቶችን በክፍል ውስጥ ካላመቻቹ ተማሪዎች ለቋንቋ

ትምህርቱ ያላቸው በጎ አመለካከት ከፍ እንዲያደርጉ የተለያዩ መንገዶችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረቡ ጉደዮች መሆናቸውን ምሁራኑ ጠቁመዋል፡፧

### 2.6.2.1 ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ላይ ያላቸውን መልካም አመለካካት ማሳደግ

Dornyei (2001) እንደገለፁት፣ ቋንቋን ለረጅም ጊዜ በፍላጎት መከታተል መልካም ወደ ሆነ አመለካከት ለማሻገር ተማሪዎችን ውጤታማ ሊያደርጓቸው ይችላል። ለዚህም ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ቋንቋ ጋር ትስስሮሽ ያላቸው ሦስት ጉደዩች መኖራቸውን ምሁሩ ገልጸዋል፡፡እነዚህን ጉዳዩች ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ይሞከራል።

1. ከታላሚው ቋንቋ የትምህርት ሂደት ጋር አዎንታዊ ትስስርነት ያለው አመለካከት የተማሪዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስና ከፍ ለማድረግ ዋናው ጉዳዩ ትኩረታቸውንና መሻታቸውን በማነቃቃት ጥሩ ምስልን በአእምሯቸው ውስጥ መፍጠር ነው፡፡ ይህም ተነሳሶት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው መሆን ያሳያል፡፡
2. ለአመለካከትና ለተነሳሶት የሚሰጠው ዋጋ ከታላሚው ቋንቋና ከተናጋሪዎቹ ጋር ያለው ተዛምዶ ይህ ዓይነቱ ሂደት በማህበራዊና በባህላዊ ጉዳዩች ላይ የሚያኩተሩ ሲሆን ውህደታዊነትን ያሚያመለክት ነው። ይህም ከባህሉ ከተናጋሪዎችና ከሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች ጋር ትስስሮሽ ያለው ነው። የሚከተሉትን ሀሳቦች ባህላዊ ዕውቀትን ለማግኘትና ውህደታዊነትን ከፍ ለማድረግ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡
    - አስፈላጊ ከሆኑ ቋንቋ ባህል ፍላጎቶች ጋር ተማሪዎችን ማስተሳሰር፣
    - በባህል ተመስሰሎዎች ላይ በማተኮር የባህል እውቀትን ማሳደግና ትስስርን መፍጠር፧
    - ቋንቋ በክፍል ውስጥ ያለውን አዎንታዊ ተግባር ለተማሪዎች ማካፈል፧
    - ስለ ቋንቋ ትምህርት አስፈላጊነት የተነገሩ፣ በህዝብ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸውን አባባሎችንና ጥቅሶችን በመሰበሰብ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ማካፈል፧
    - ስለ ሀገሪቱ ጥሩመረጃ የያዙ በቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን እንዲፈለጉ በማበረታታት ያገኟቸውን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ከታላሚው ቋንቋ ባህል ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በማወቅ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሳደግ መጣር ተገቢ ይሆናል

3. ታላሚው ቋንቋ ለተማሪዎች ያለው ጠቃሜታና ውጤት ይህ ቋንቋን ማወቅ ሊስገኝ ከሚችለው ማህበራዊ ጥቅምና ተግባራዊ ክንውን ጋር ትስስርነት አለው። ይህ ለጥቅማ ጥቅም ዋጋን የመስጠት ሂደት፡- የገንዘብ ክፍያን፣ የሥራ ዕድገትን አጋጣሚ ወዘተ የመሳሰሉ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡

Alison (1993) ይህንን ሀሳብ ሲያብራሩ፣ ጥቅምን የሚስገኙ ብልሃቶች የተነሳሰቱን ዋጋ የተነሳሶቱን ዋጋ የሚያመላክቱ ዘዴዎች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ እነዚህንም ዘዴዎች ተማሪዎቹ ለሚጠቀሙባቸውና ውጤታማ ለመሆን የሚፈፅሟቸው ተግባራት አስቀድመው ዋጋ የከፈሉባቸው በመሆናቸው ብቃት ላይና በሚፈለገው ውጤት መካከል ትስስሮሽ ለመፍጠር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ጠቃሚ የሆነ ውጤትና ስኬታማየሆኑ ብልሃቶች ይኖራሉ። መምህራንም ተማሪዎቹን በቋንቋው እንዴት እንደሚጠቀሙበትና ቋንቋው የመጠቀም ብቃታቸው እስከምን ድረስ እንደሆነ መቃኘት ነው።

በአጠቃላይ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት በማሳደግና ለቋንቋው የሚስጡትን ዋጋ ከፍ በማድረግ ተፈላጊውን ተነሳሰት ካለበት ደረጃ በማንቀስቀሰ ወደ ውጤት እንዲደርስ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል።

### 2.6.2.2 ውጤት የመጠበቅ ተሰፋን መጨመር

ውጤትን የመጠበቅ የሚለው ሀሰብ ላለፉት አርባ ዓመታት ያህል ጥናት ከተደረገባቸው የተነሳሶት ስነ ልቦናዊ ተፅእኖዎች መካከል አንዱ ነው። Bronphy (1998) ይህን ሀሰብ በተመለከተ የሚከተለውን አስፍረዋል ስዎች በአንድ ነገር ላይ ስኬታማ እንደሚሆኑ ተስፋ ካደረጉ ድርጊቱን ለመፈፀም ወደ በኃላ እንደማይሉ የማይካድ ሀቅ ነው። በተመሳሳይ መልኩ በጥሩሁኔታ ከተማሩውጤትን  መጠበቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይሁንና ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ብቻውን በራሱ በቂ በለመሆኑ በመልካም እሴቶች መታገዝ እንደሚገባው አጥኚዎቹ ይስማማሉ በመሆኑም ውጤትን የመጠበቅ ተስፋና ለአንድ ነገር የምንሰጠው  ዋጋ ወይም ግምት በአንድነት የሚሄዱ ጉደዮች ናቸው ምሁሩ አያይዘው፣ አንድን ነገር የመጠበቅ ሂደት የሚከናወነው በአእምሮ ውስጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚነሳሱ ተማሪዎች አንድን ነገር የመጠበቅ ተስፋቸውን የሚያሳድጉት፣ በነቃ አእምሮ ሁኔቶችን በትክክለኛው መንገድ ሲያስተከሉና

በአዎንታዊ ሁኔታ ሲተገበሩ ነው በተጫማሪም ለተማሪዎች ከባድና አስቸጋሪ የሆኑ ትግበራዎችን መስጠት ተገቢ አይሆንም።

Dornyei (2001) ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ከፍ እንዲል የሚከተሉትን ዘዴዎች ይፋ አድርገዋል፣

1. አስቸጋሪ ለሆኑ ትግበራዎች ብቻ ሳይሆን ትግበራዎቹን ማከናወን እንደሚገባቸው ለተማሪዎች በቂ ግንዘቤ መስጠት፣
2. መምህራን የክፉሉን ሁኔታ በመምራት ላይ ላሉ፣ ተማሪዎቹ ወደተግባር ክንውኑ በቀጥታ እንዲገቡና አስቸጋሪ ትግበራዎችን መከናወን እንዲችሉ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው እርዳታ ማድረግ፣
3. በትብብራዊ እና በአነስተኛ ቡድን ተደራጅተው ትግበራን በሚከናውኑበት ወቅት ተማሪዎች የሚያውቁትን ነገር ለተመሳሳይ አላማ ከቢጤዎቻቸው ጋር አብሮ በመስራት እርስ በራሳቸው እንዲተጋገዙ ማድረግ፣
4. በትምህርት ክንውን ወቅት የሚጠብቁ የሌሎች ተማሪዎችን ስኬታማ ክዋኔዎች በምሳሌነት /በምዴልነት/ ማቅረብ፣ ይህ ተግባር ሞዴል በጥራት የተሰራው በቢጤዎቻቸው ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም በነበሩ ተማሪዎች ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ ከውጤቱ ምን እንደሚጠብቁ ለማሳየት ሲባል የምስልና የድምፅ መቅረጫዎችን በመጠቀም የውጤት ምዴሎችን ማቅርብ ያስፈልጋል። በጭሩ ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ምሁሩ እንደገለፁት በአእምሮ ውስጥ የሚከናወን ሂደት ሆኖ፣ ተማሪዎች ከሚያዩዋቸው የክንውን ውጤቶች የተነሳ ሊፈጠር የሚችል መሆኑን መንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ለመጠናከር ተማሪዎችን በበቂ ሁኔታ ለትግበራው ማዘጋጀት፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን መርዳት፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲተጋገዙ ማድረግና የተለያዩ ስኬቶችን በምዴልነት ወስዶ ማየት ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ እንዲጨምርና ተነሳሶት ከፍ እንዲል እገዛ እንደሚያደርግ መገንዘብ ይቻላል።

#### 2.6.2.3 አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መርጃመሳሪያዎችን መዘጋጀት

wodowsky (1996)ን ጠቅሰው እንደገለፁት፣ ተማሪዎች ትምህርቱ ሳቢና ማራኪ ቢሆንም ባይሆንም የተለያዩ የክፍል ውስጥ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን መሥራታቸው ያስፈልጋል። ይሁንና ከተማሪዎች ፍላጎትና መምህራን ካካበቱት ልምድ በመነሳት ተማሪዎች ምን ዓይነት ፍላጎትና ዝንባሌ እንደላቸው መረጃ በመሰብሰብ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ። መምህራን የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግም ከተማሪዎቹ ልምድና ሕይወት ጋር የተዛመዱ ርዕሶችንና ትግበራዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ማራኪና ሳቢ ሆነው የማዘጋጀት ማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን ተነሳሶትን ከፍየሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ይቻላል።

#### 2.6.2.4 የተማሪዎች ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግ

Gardner and Macintyre (1993) እና Petty (2004) ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ከፍ ብሎ ተነሳሶታቸው እንዲጨምር ለማድረግ መምህሩ የሚከተሉትን ሐሰቦች ተግበራዊ ቢያደርግ የተሻለ እንደሆነ ያስረዳሉ፣

-መምህሩ በሚያበረታታ መልኩ የራሱን የትምህርት ፍላጎት ለተማሪዎቹ ማሳየት፣

-መምህሩ አንጓጊና ጥያቄ ሊፈጥሩ በሚችሉ ነጥቦች ላይ በማተኮር ተማሪዎቹ እንዲሰተፉ ማድረግ፣ ተጨባጭ በሆነ መንገድ መምህሩ የሚያስተምረው ትምህርት ጠቃሚ መሆኑን ለተማሪዎቹ ማሳወቅ፣

-ተማሪዎቹ የራሳቸውን ፈጠራና ገለፃ እንደሚጠ ቀሙበት ዕድል መስጠት፣

-የተማሪዎቹን የትምህርትክንውኖች መደበኛ በሆነ መንገድ እየለዋወጡ እንዲሠሩ ማመቻቸት

-የሚያስደንቁና የሚያስገርሙ ሃሳቦችን በትምህርቱ መሃል ጣልቃ በማሰገባት ተማሪዎችን ማነቃቃት

-በክፍል ውስጥ በትምህርት ክንውን ወቅት በቡድን ሆነው ሲሠሩ የተወዳዳሪነት መንፈስን በመከካላቸው መፍጠር፣

-በተስተምሮቱ ወቅት የሚቀርቡ ምሳሌዎችን ከኑሮአቸውና ከሕይወት ልምዳቸው ጋር በማያያዝ ማቅረብ፣ መምህሩ እነዚህን ሀሳቦችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በአግባቡ ከተጠቀመ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ፍላጎት አድሮባቸው ወደ ውጤት ሊያመሩ ይችላሉ፡፡

### 2.6.2.5 የተማሪዎችን የዓላማ አፈፃፀም ማሳደግ

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ጥሩ ዓላማን ይዘውለመማር ከተነሱ ለትምህርቱ ያላቸው የተነሳሶት ደረጃ ከፍ ያለ እንደሚሆን Gardner and Macintyre (1993፣ 133)፤ ያስረዳሉ። ይሁንና በተሰትምህርሮቱ ተግባር ውስጥ  ለምን እንደተላለፉ በውል የማይገነዘቡ አንዳንድ  ተማሪዎች ይኖራሉ ።

ስለሆነም መምህራኑ ተማሪዎች በቋንቋ  ትምህርቱ  የተነሳሱ እንድሆኑ  ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው  የክፍል ውስጥ ተግብራትተማሪዎች ስያውቋቸውና  ሊቀበሏቸው የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል። በተጨማሪም ትግባራዎቻቸው ከሚያውቁትን  ከአከባቢያቸው ሁኔታ ጋር እያጣጣሙ የሚተግበሩን  ከልሆኑ መምህሩ ተነሳሶትን  ለመፍጠር የሚደርገው ሙከራ ከንቱ ልፋት  ይሆናል።

በሌላ በኩል Janet (1997) ተነሳሶትን በተመለከተ ጠቅሰው ተማሪዎች ውጤታማ መሆን እንዲችሉ የራሳቸውን እቅድና ዓላማ መንደፍ ይኖረባቸዋል፡፡ መምህሩም የቋንቋ ትምህርቱን ከተማሪዎች ግላዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ የሚጠቀመባቸውን የማስተማሪያ ስልቶች ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል።

William and Burden (1997) እንደመለከቱት የክፍል ውስጥ ትግባራዎችን መርጦ በሰፈለገው ጊዜና ሁኔታ መጠቀም ተማሪዎችን ወደ አንድ የትምህርት ዓላማ እንዲያመሩ ይገባል፡፡

### 2.6.3 የተማሪዎች ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ

Dornyei (2001፣ 71) የተማሪዎች ተነሳሶት በጥንቃቄ ሊያዝ እንደሚገባ በዝርዝር አስፈረዋል። ተነሳሶት ጥንቃቄ ካልተያዘና ካልተጠበቀ ድርጊቱ በሚከናወንበት ጊዜ የተማሪዎች ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ እየተዳከመና በተግባር ክንውኑ ላይ መሰላቸት ይታይባቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው ተነሳሶት እየቀነሰ ይሄዳል። ስለዚህ

የቋንቋ መምህሩ በርካታ የተነሳሶት እንክብካቤ ብልሃቶችን መጠቀም ይገባዋል ። ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸው ዝንባሌ እየተዳከመ ሲሄድ የትምህርት ዓላማውን አቅጣጫ ይስታሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ተፈላጊው የተማሪዎች ተነሳሶት ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል ።በተጨማሪም አዎንታዊና አሉታዊ ጎን ያላቸው ተፅዕኖች በትምህርት ላይ ይከሰታሉ ፡፡ ስለዚህ ያላቸውን ተነሳሶት በጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልጋል። Raymond (1986፤144) በበኩላቸው የሚከተለውን ሀሳብ ስንዝረዋል።

በማንኛውም ሰው ውስጥ አንዳንድ ፍላጎት የማሟላት ምኞት ይንፀባረቃል። በተነሳሶት ጥበቃና አፈፃፀም ዙሪያ የተለያዩ ብልሃቶች አሉ። እነዚህም ብልሃቶች ሰው ልጅ በባህሪዩ በሂደት ላይ እያለ በተለያዩ መንገዶች እንዲሻሻልና እንዲለዋወጥ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል የትምህርት ትግበራዎችን በማስተማር ሂደት ወቅት የተማሪዎችን ተነሳሶት እንዴት ከፍ ማድረግ እንደሚቻል እናያለን፣

### 2.6.3.1 ተማሪዎች ያላቸውን በራስ የተለየ ግምት መስጠት በመንከባከብ በራስ የመተማመን ብቃት ማሰደግ

በራስ መተማመን የሚለው ሀሳብ ለራስ የተለየ ግምት መስጠት የራስ ብቃት፣ ራስን ማስጨነቅ በሚሉት ፅንሰ ሀሳቦች ጋር ተዛምዶ አለው ፅንሰ ሀሳቦቹ በራሳቸው ውስብስብነት ቢኖራቸውም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተነሳሶታቸው አመካኝነት ወደ ትምህርት እንዲያተኩሩና ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ እንድችሉ ያደርጋል። ይህ እንድሆን ግን በራስ መተማመንና ለራስ የተለየ ግምት መስጠት የሚሉት ፅንሰ ሀሳቦች ጤናማ ሆነ የእርስ በርስ መደጋገፍ ሊያሳዩም ይገባል Raymod (1986)። ይሁን እንጂ Hedge (2000) እንደሚጠቁሙት እነዚህ ፅንስ ሀሳቦች ምንም ዓይነት እንክብካቤ ቢደረግላቸው አስተማመኝ የሆነ መረጋገት አይታይባቸውም። ምክንያቱም ምንም እንኳን መምህሩ ፈጠራዊ የተነሰሶት ሀሰቦች ቢያክሉባቸውም ተማሪዎች የጥርጣሬ መንፈስ ካላቸው በራስ መተማመናቸው ከፍ ሊል የማይቻል በመሆኑ ነው።

Scheidecker and William (1999፤122) እንዳሚያብራሩት ተማሪዎች የራስ ብቃታቸው የራስን አነስተኛ ሆኖ አስቸጋሪ ክንውኖች በስኬታማነት እንዴት መተግበር እንደሚገባቸው ከማተኮር ይልቅ ከችግራቸውና ከብቃት ማነሳቸው ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ ከዚህም

የተነሳ ተማሪዎቹ ችሎታቸው እየቀነሰ ሲሄድና ከራስ አለመተማመን ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ በራስ የመተማመን ብቃታቸው ከውስጣቸው ይጠፋል። በአንፃሩ ጠንካራ የሆነ የራስ ብቃት፡- የተማሪዎችን የሥራ ክንውን ማለትም ከክንውን ተሳትፎ ወቅት ስለ ራስ ማንነት ከሚሳብ ይልቅ ስለክንውኑ የማሰብ፣ በራስ ተማምኖ ተስማሚ ሁኔታዎችን የማቅረብ፡፣ ውድቀት በሚያጋጥምበት ጊዜ ጥረትን የማጎልበት ችሎታን ያሳድጋል ፣ከፍ ያደርጋል።

Dornyei (2001፣87) ታደጊ ወጣቶችን አስመልክተው የራስ መተማመን ብቃታቸውምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ታደጊ ወጣቶች በአከባቢያቸው በሚደርሱባቸው ግጭቶች አማካይነት ለተለያዩ ጥቃቶች ይጋለጣሉ። ከዚህም የተነሳ ስለ እፅኝነት፣ ስለቡድናዊነት፣ ስለዘር፣ ስለ አለባበስ፣ እንዲሁም ስለ ትምህርት ውጤታቸው ሊያስቡና ሊጫነቁ ይችላለ። ይህ ሲሆን ደግሞ የራስ መተማመን ብቃታቸው ዝቅተኛ ይሆናል Scheidcher and William (1999) ይህን ሀሳብ አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውሰጥ ስለተማሪዎች ለራስ የተለያየ ግምት መስጠት በራስ መተማመንን በራሰ ብቃት መጨነቅ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው ምክንያቱም ተማሪዎቹ ታዳጊ ወጣቶች በመሆናቸው አንድ ነገር ሲያገጥ ማቸው በራሳቸው ከመተማመናቸው ይልቅ የስሜት ተለዋዋጭነት፣ ጥርጣሬ እና ጭንቀት ስለሚታይባቸው ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ ጥረታቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙበትና ቋንቋቸውን ለማሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አምስት መርሆችን Dornyei (2001፡130) ይፋ አድርጓል።

- የተማሪዎች በራስ የመተማመን ብቃት ለውጥን እያየ እንዲሄድ እምነታቸውን ማበረታታት ይቻላል፣
- መምህራን ንቁ የሚያደርግ መደበኛ ልምምድን በመስጠት ለቋንቋ ትምህርቱ ብቃት ምቹ የሆነ አመላከከትን መፍጠር ይችላል፣
- ተማሪዎች ለትምህርቱ ጥሩ ስሜት ከኖራቸውና አስተዋጽኦ ከበረከቱ የሚሰጠው የትግበራ ክንውን ለመስራት ፍላጎት ያድርባቸዋል፣
- ተማሪዎችን ለማበረታታት ከግለሰቦች የሚወጡ ጥቂት ቃላት በቂ ናቸው፣
- መምህራን የትምህርቱን አውድ አዝናኝ በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚታየውን የተማሪዎች ጭንቀትና ተስፋ ማጣት መቀነስ ይችላሉ። በአጭሩ መምህራን

ለተማሪዎቻቸው በሚያደርጉት እንክብካቤና ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር በሚያደርጉት ጥረት አማካይነት በራስ የመተማመን ብቃታቸው ከፍ ሊል ይችላል።

### 2.6.3.2 በራስ መማር

እንደ Benson (2000) አመለካከት፣ ትምህርት በሰዎች ባህሪይ ተፅዕኖን ሊያስከትል የሚችል ጉዳይ ነው። ምሁሩ በራስ ላይ ዕድገትን ለማምጣት የሚያለማምዱና የሚያበረታቱ አምስት ነጥቦችን ለይተው አሰይተዋል፡፡

1. ተማሪ- ተኮር አቀራረብ፡- ይህ ግልፅ የሆነ ሰነልቦናዊና የባህሪ ለውጥ በተማሪው ላይ ያመጣል።
2. የመረጃ ምንጭ-ተኮር አቀራረብ፡- ይህ ደግሞ በትምህርቱ የመረጀ ምንጮች ላይ ነፃ የሆነ ተረክቦ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
3. ቴክኖሎጂ-ተኮር አቀራረብ፡- ተማሪዎች ቴክኖሎጅን በመጠቀም ከትምህርቱ ጋር ነፃ የሆነ ተረክቦን ያደርጋሉ።
4. የክፍል ውስጥ-ተኮር አቀራረብ፡- ይህ የሚያመለክተው በመምህሩና በተማሪው መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ እያመጣ ሲሄድ ነው።
5. መረሀ ትምርት-ተኮር አቀራረብ፡- ይህ የተማሪውን ሀሳብ ከመረሀ ትምህርቱ ጋር በማገናዘብ ትምህርቱ እንዲካሄድ ያደርጋል።

Ushioda (1997፣ 41) በራስ መተማመን ማለት እንዲጠበቁት በራስ የሚደረግ ተነሳሶት ሰለ ትምህርቱ ልምዶች ስለ ትምህርቱ ዓላማ ምንነት መመርመር የሚያስችል ነው። በመሆኑም ተነሳሶት የአዎንታዊ ሀሰብ ተግባርና የእምነት መዋቅር ነው። በተጨማሪም ከትምህርቱ ውስጥ ጉልቶየሚታይ ዘለቂነት ያለው አዎንታዊ ሀሰብ ነው።

### 2.6.3.3 የተማሪዎችን እርካታ መጨመር

Covington (1999፣127) ስለ እርካታ ሲገልፁ፣ የእርካታ ስሜት የተነሳሶት ዋነኛ አካል አስፈላጊና የሚያበረታታ የሥራ ክንውን በሕርይ ነው፡፡

የመምህራን የተነሳሶት ብልሀቶችአላማቸው የተማሪዎችን እርካታ በመጨመር ስራቸውን በፈቃደኝነት በመተግበር ላይ ያተኮረ ነው። ማበረታታት ልክ እንደ ሽልማት የሚያኮራና የሚያስከብር ውጤትን ያስገኛል፡፡ተማሪዎች በትክክልና እና በስርዓቱ ባይሠሩም እንኳን

የመጨረሻ የሆነውን የመውደቅ ወይም የማለፍ ግብ ውጤታቸው እርካታቸው የተለያየ እንዲሆን ያደርጋል። አንድ ውጤት የሚያተኩረው ከመማር ሂደት ይልቅ በክዋኔ ብቃት ላይ ነው። በርካታ ተማሪዎች አሁን ያሉበት ደረጃ ያደረሳቸው በመጀመሪያ ያገኙት ውጤት ነው።

በሌላ በኩል Haris (1991) ውጫዊ ተነሳሶት በውስጣዊ ተነሳሶት አመካኝነት ኃይል አገኝተው መነቃቃት ስላልቻሉ ተማሪዎች እንደ ሽልማት ሊረዱ የሚችል ጉዳይ እንደሚሆን ገልጸዋል። ለመጥፎ ባህሪያት የሚሰጡ ትችቶችና ለጥሩ ባህሪያት የሚቀርቡ ምስጋናዎች እንደ ሽልማት ይቆጠራል። Hair(1991) አክለው እንደብራሩት፣ በትምህርት ቤቶችም ሆነ በኮሌጆች ውስጥ ለጥሩ የክዋኔ ብቃቶች ምሳሌ የሚሆኑ ስርተፍኬቶች፣ መጽሔቶች፣ ቃላዊ ምስጋናዎች ይሰጣሉ። ዋናው ነገር ውጫዊ ተነሳሶት በትክክለኛው ጊዜው ከተሰጠ ውስጣዊ ተነሳሶትን ማስገኘት ይቻላል።ባጭሩ ለጥሩ ሥራ የሚሰጥ ሽልማት ጥሩ ስሜትንና አመለካከትን አስገኝተው ለእርካታ ያበቃል ማለት ይቻላል።

### 2.6.3.4 የትምህርት ትግበራዎችን በተነሳሶታዊ መንገድ ማቅረብ

Good and Brophy (1994) ለትግበራዎች የሚደረግ ተነሳሶት ውጫዊና ውስጣዊ ባህሪይ ያሏቸው በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። ከተማሪዎች ተነሳሶት ጋር ግንኙነት ያለው ትግበራ እውነተኛ ተግባቦትን የሚያሰድግ ነው። Nunan (1989) በበኩላቸው ደግሞ ጥሩ ትግበራዎች የሚያከትቷቸው ክንውኖች በተማሪዎች መካከል የሚከሂደውን እውተኛ ተግበቦታዊ ተራክቦ በሚያሰድግና በሐሳቦች ላይ ለማስማማት ተማሪዎችን የሚያበረታታ ነው ሲሉ፣ Parrott (1993) ዳግሞ የሚከተለውን ሀሰብ ሰንዝረዋል፣ ክንውኖችን መምረጥ የሚገባን የቋንቋ ትምህርቱን ለማካሄድ ብቻ ሳይሆን አዎንታዊ የጋራ ስሜቶችንና አመለካከቶችን ለመደገፍ ጭምርነው፡፡ Hutchinson (1988) ደግሞ በበኩላቸው የቢጤና የቡድን ስራዎች አሉታዊነት የማይታይባቸው የተማሪዎችን ውስጣዊ ስሜቶችን ለማነሳሳት እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል። በተጨማሪም ክንውኖቹ ዓላማዎችን ግልፅ ለማድረግ ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የትምህርት ትግበራዎችን ግብ ከተረዱ ከውስጥ በመነጨ እና ባጠናከረ ፍላጎት ክንውኑን ይፈፅማሉ፡፡

Good and Brophy (1994) እንደገለፀት፣ ጥሩ ትግበራዎች ለዕውቀት ዋጋን ይሰጣሉ። በተጨማሪም በክንውኖቹ ወቅት ክሂሎች እንዲዳብሩ ይረዳሉ። ይህም ማለት ትግበራዎቹ ለተማሪዎቹ ጊዜያዊና ቀጣይ ሕይወታቸውን የሚሆኑ ዕውቀቶችን ያስጨብጣሉ።

Harmer (1991) እንዳገለፁት፣ ትግበራዎች ውጤታማ መሆን አለባቸው፡፡ መምህራን በጣም ከፍተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ የሆኑ ትግባራዎችን መቅርፅ የለባቸውም። ምክንያቱም ሙሉ ለሙሉ ውጤት አልባ መሆን ተነሳሶትን ሊያደክም ይችላል። Conning swoth (1984) የተለምዷዊ ትግበራ መመሪያ ዓላማዎችን እንሚከተለው በዝርዝር አስፍረዋል፡፡

1. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚፈፅሙት ተግባር ምንድን ነው?
2. ትግበራዎቹስ መቼ ይጨርሳሉ?
3. እነዚህን አፈፃፀሞች እንዴት ይገመግማሉ?

በሌላ በኩል ወደ ተነሳሶት የሚያስገቡ ክንውኖች ቢያንስ ሦስት ተግባራት ይኖራቸዋል፣

1. የትግበራዎችን ዓላማና አጠቃቀም ይገልፃሉ።
2. ተማሪዎቹ በትግበራው ላይ ያላቸውንና የሚኖራቸውን ተሳትፎ ያሳያሉ።
3. ትግበራዎችን ለመሥራት የሚበጅ ትክክለኛው ብልሃቶችን ይጠቀማሉ።

በአጠቃላይ በተነሳሶታዊ መንገድ ትግበራዎችንና ክንውኖችን ማቅረብ ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግ፣ እንዲሁም አመቺ የሆኑ መመሪያዎችን መቅረፅ የተማሪዎቹ ፍላጎት ሙሉ እንዲሆንና ክንውን እንዲሠሩ ያደርጋል።

### 2.6.3.4.1 ትምህርቱን አነቃቂና አስደሳች ማድረግ

Killer (1983) እንደገለፁት፣ ሰዎች የወደዱትን ሥራ ኃይላቸውንና ጊዜያቸውን ተጠቅመው ለመሥራት ፈቀደኞች ናቸው።ተማሪዎችም የሚወዱትን ትምህርት በክፍል ውስጥ ለመማርና ትግበራዎችንም ለመከናወን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። Dormye (2001) የትምህርት ክንውኑን የተዋጣለት ለማድረግ ሦስት ዓይነት ብልሃቶች እንዳሉ ይጠቁማሉ፡፡

1. የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመርና ክንውንን የበለጠ አስደሳች ለማድረግ የተናጠል ሥራን አለማዘውተር። መምህራን የትምህርት ክንውኖችን ከመለያየት ተማሪዎችን ማስተማር ይችላሉ። ለምሳሌ የቋንቋ ክሂልን በተመለከተ ሲያስተምሩ የፅሕፈትን ከንግግር ክሂልን በመለየት፣ ታግባቦታዊ ክንውንን ሲያከሄዱ የማደመጥን፣ የመመልከትንና የመደሰስን መግባቢያዎች በመለያየት ከቢጤ ስራ ለይተው ያቀርባሉ፡፡
2. ለትግበራው የሚሆኑ አስፈላጊ ሂደቶችን በየዓይነቱ አቀናጅቶ የማቅረብ መምህሩ ትምህርቱን የሚያቀራርብበት ስልት፣ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያ፣ የተማሪዎች በተሳትፎ ወቅት ያላቸው ቆይታ፣ የመማሪያ ክፍሉ፣ የወንበርና የጠረጴዛ አቀማመጥ ወዘተ… ትምህርቱ አሰልቺ እንዳይሆን እርስ በርስ ተቀናጅተውና የመማሪያ ክፍሉ ተደራጅቶ የሚሰጠውን ትግበራ ውጤታማ ሊያደርግ ይችለል።
3. የተመረጡ ይዘቶችን ለትግበራው ክንውን መጠቀም Good and Brophy (1994) እንዳመለከቱት የትምህርት ትግበራው ማራኪና አነቃቂ ሊሆን የሚችለው ትግበራው የያዘው ይዘት የተመረጠ ሲሆን ነው። ሳቢና የተነሳሶት ባህሪያት የሚታይባቸው የትግበራ ይዘቶች የሚከተሉ ናቸው፡፡

ሀ. ተማሪዎቹ ችግርን እንዲያቃልሉ፣ አዳዲስ ግኝቶችን እንዲያገኙ፣ የተሸሸጉ መረጃዎችን እንዲያወጡ የሚያደርጉ የትግበራ ይዘቶች፣

ለ. ተማሪዎች በርዕሱ አማካኝነት ተገፋፍተው መልመጃዎችን እንዲሠሩ የሚያደርጉ ተወዳጅ ይዘቶች፣

ሐ. አሰልቺነትን የሚያስወግዱ አዳዲስ ወይም ያልተጠበቁ እንግዳ የሆኑ ይዘቶች

መ. እያንዳንዱን ተማሪ የግል ሕይወቱን እየነካ ሊያነቃቃ የሚችል ግለሰባዊነት የሚታይ ይዘቶች

በአጭሩ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የትግበራ ይዘቶች ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ትምህርቱን አስደሳች ለማድረግ ጉልህ ሚና አላቸው።

2.6.3.4.2 የሚያነቃቁ ምጋቤ-ምላሽ ሽልማት መስጠት

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ የመምህር-ተማሪ መልካም ግንኙነት ምጋቤ-ምላሽ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ Harmer (2001)፣ Pintriin and schunk (2002) ምጋቤ-ምላሽን እንደሚከተለው ገልፀውታል፣ ምጋቤ-ምላሽ ከአንድ ድርጊት ወይም መልስ በኃላ ተከትሎ የሚሰጥ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ሊያመጣ የሚችል ምላሽ ነው።

በተጨማሪም በተስተምህሮተ ወቅት ዓይነተኛ የማስተማሪያ ተግባር Pintriich and schunk (2002፣322) መምህሩ ምጋቤ-ምላሽን ለተማሪዎች ሊሰጡ ለተለየ ዓላማና ተግባር ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ለምሰሌ፡- በሚያግባባ መልኩ ተማሪውን ለማበረታታት አንድን ስህተት ለይቶ ለማሳየት ወይም እንዲያሻሽል ለማድረግ ወዘተ ሊሆን ይችላል። Rosenshine and stevens (1986) ምጋ ቤ-ምላሽን በተመለከተ የሚከተለውን ሀሰብ ሠንዝረዋል። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አንድን ተግባር ሲፈፀሙ ትክክለኛመረጃን የሚሰጥ ወይም ስህተቶችንየሚያስተካክል ነው። ትክክለኛ መረጃን ሊሰጥ የሚችል ፈጣን ምጋቤ-ምላሽ የተማሪዎችን ተነሳሶት ከፍ ከማድረጉም በላይ የተወዳዳሪነትን መንፈስ እያዳበሩ እንዲሄዱ ያደርጋል። ለምሰሌ" ይህንን ስራህን (ሽን) በጥንቃቄ አስቀምጠው (ጥው) " ወይም ይህን መስራት እንደምትችልአውቃለሁ የሚሉ ምጋቤ ምላሾችን መምህሩ ቢሰጡ ተማሪው የበለጠ እንዲነሳሳና የተሻለ ነገር እንዲሰራ የሚገፋፉ ሊሆን ይችላል።

Brophy (1998) ምጋቤ-ምላሽ በምስጋና ሊቀርብ እንዲሚችል አመልክተዋል። ምስጋና አዎንታዊ ምላሻን የሚያንፀባርቅ ሲሆን የተሰራውን ሥራ ትክክለኘነት ማረጋገጫ መንገድ ነው። Wittrack (1986) ምስጋናን በተመለከተ ሲያበራሩ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ተደጋጋሚ ምስጋና ተማሪዎች ትክክለኛ ባህሪይን እንዲያመጡ ከማድረግ ይልቅ የመምህሩን ምስጋና ጠባቂ እንዲሆኑ ያደርጋል ሲሉ Brophy (1998) ይህን ሀሰብ በመቃወም ምስጋና ማለት መምህሩ ያለውን እምነት የሚያመለክትበት መረጃ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪው ስህተት ሲሰራ አንተ(ቺ) በደንብ እንደምትሰራ(ሪ) አውቃለው፣ ምነው ዛሬ የሚል ምጋቤ-ምላሽ መምህሩ ቢሰጥ ተማሪው፣ ከስህተቱ ታርሞ እንደገና እንዲሰራ የሚገፋፉ ይሆናል።

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ምጋቤ ምላሽ በተማሪው እምነት፣ ጥረትና ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል፣ መምህሩንም በአግባቡ ሊጠቀምበት የሚገባ በመማር-ማስተማር ወቅት የተማሪው ተነሳሶት እየጨመረ እንዲሄድ የሚያደርግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

## 2.7 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት

በመማር መስተማሩ ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበትን የተነሳሶትን ስልት በሚመለከት ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎች እጥኚው መግኘት አልቻለም፡፡ ይሁንና እንግሊዝኛን ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን ዙሪያ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበትን የተነሳሶት ስልት አተግባበርምን እንደሚመስል የሚሳይ ጥናቶችን ማግኘት ተችሏል ጥናቶቹም ከዚህ ጥናት ጋር የይዘት ዝምድና የሚታይባቸው በመሆኑ አንድነታቸውና ልዩነታቸው ከዚህ በታች ለመቃኘት ተመክሯል።

Mulgeta (1997) በማደመጥ ክሂል ጊዜ የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሶት ምን ያህል እንደሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአንደኛ ዓመት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ አካሂዷል፡፡ በጥናቱም ለተማሪዎችና ለመምህራን በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት የመረጃ መሰባሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ተግባር ላይ አውሏል፡፡ የጥናቱም ውጤት በተመለከተ ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ በመሆኑ ግንዛቤያቸውን እንዲጨምር መምህራንም ተማሪዎቸን ለማነሳሳት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው የመፍትሄ ሃሳብ ጠቁመዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሙሉጌታ ጥናት በማዳመጥ ክሂል ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ከአጥኚው ጥናት ይለያል፡፡ ሌላው በመረጃ ማሰባሰቢያነት የወሰደው በዋናነት የጽሁፍ መጠይቆች ሲሆን የአጥኚው በዋናነት የተወሰደው ምልከታ በመሆኑ ይለያል፡፡ የክፍል ደረጃን በተመለከተ የሙሉጌታ በከፍተኛ ተቋማት ላይ ሲሆን የአጥኚው በሁለተኛ ደረጃ ላይ ስለሆነ ይለያል፡፡ የሙሉጌታ ጥናት ዓመተ ምህረቱ 1997 ሲሆን የአጥኚው 2009 ዓመተ ምህረት ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ጥናት ከአጥኚው ጋር በመረጃ ማሰባሰቢያነት የተጠቀመው የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ያመሳስላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ በተነሳሶት ላይ በማተኮሩ ከዚሁ ስራ ጋር ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ የሙሉጌታ የጥናት ትኩረት በማዳመጥ ክሂል ተማሪዎች ምን ያህል

መሆኑን የመረመረ ሲሆን አጥኚው ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ጥናት ስለሆነ ይለያያል፡፡

Bayoush (2007) የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን የተነሳሶት ስልትን እንዴት እንደሚተገብሩ ጥናት አካሂዳለች፡፡ በጥናቷም ለመምህራንና ለተማሪዎች ያዘጋጀችው የጽሁፍ መጠይቅ በቀዳሚ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን በአጋዥነት ደግሞ ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ተግባር ላይ አውላለች፡፡ የጥናቱ ውጤት መምህራን መልካም የሆነ የመምህር ተማሪ ግንኙነት በመፍጠር' ተማሪዎች ያለፉትን የክፍል ተሳትፎ በመገፋፋት አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች መስጠት ተነሳሽነትን ስልቶች ለመተግበር ቢሞክሩም በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ችግሮች በትምህርት ቤቶቹ ተከስተዋል፡፡ የእነዚህ ችግሮች ምክንያት በአንድ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የማስማሪያ እጥረቶች ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመቆጣጠር እና የሁሉንም ተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ የባዩሽ የጥናት ትኩረት በእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን የማነሳሳት ስልቶችን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩ ሲሆን የአጥኚው ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማነሳሻ ስልት አተገባበር እንዴት እንደሚተገብሩ ያጠና ስለሆነ ይለያያል፡፡ በባዩሽ የመረጃ መሰብሰቢያ በዋናነት የተጠቀመችው የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆን የአጥኚው በዋናነት የተጠቀመው ምልከታ በአጋዥነት የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ በመሆኑ ከባዩሽ ይለያል፡፡ ጥናቱን ያካሄደችው በ2007 ዓመተ ምህረት ሲሆን የአጥኚው ግን በ2009 ዓመተ ምህረት ስለሆነ ይለያል፡፡ ሁለቱም ጥናቶች በቋንቋ ላይ የተጠኑ በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

Seblawangle (2007) በነቀምቴና በአዳማ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና መምህራን ማሰልጠኛዎች የሚያስተምሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን የተነሳሶት ስልቶችን እንዴት ተግባራዊ እንዲሚያደርጉ አጥንተዋል፡፡ በጥናቱም ለመምህራኑ የተዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ሲሆን ቃለ መጠየቅና የክፍል ምልከታ በደጋፊነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ግልጋሎት ላይ ውለዋል፡፡ የጥናቱም ውጤት ምቹ እና አስደሳች የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታን መፍጠር' በራስ መተማመንን ማጎልበት ወዘተ የመሳሰሉ የተነሳሽነት ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ባለመሆኑ ስርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው

ባህልና ከኢትዮጲያ የቋንቋ ስነ ልሳናዊ አውድ ጋር ተዋህዶ የመማሪያ መጽሀፉ እንዲዘጋጁ' መምህራኑም ተማሪዎቻቸውን ማነቃቃት እንዲችሉ ስልጠና እንዲሰጣቸው የመፍትሄ ሀሳብ ጠቁመዋል፡፡ የሰብለ ወንጌል የጥናት ትኩረት በእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን የማነሳሳት ስልቶች በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩ ሲሆን የአጥኚው ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩ ስለሆነ ይለያል፡፡ ለጥናቱ ለመምህራን በዋናነት የተዘጋጀው መረጃ መሰብሰቢያ የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን የአጥኚው በዋናነት ምልከታ በመሆኑ ይለያል፡፡ የጥናቱ ቦታና ዓመተ ምህረት በከፍተኛ ተቋማት በ2007 ሲሆን የአጥኚው በሁለተኛ ደረጃ በ2009 ዓመተ ምህረት በማስተማር ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ስለሆነ ይለያያል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች በተነሳሶት ላይ በማተኮራቸው ከዚህ ስራ ጋር በተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ በተለይ Bayush and seblewengele ላይ የተጠቀሱት ስራዎች የተነሳሶት ስልቶችን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩ ያጠኑ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ናቸው፡፡ Mulugeta ላይ የተጠቀሰው ስራ በተናጠል በአንድ ክሂል ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ሊለያዩ ችሏል፡፡ከዚህ ሌላ Bayush (2007) የተጠቀሰው ስራ በአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን ትምህርት ላይ የተካሄደ ጥናት ሲሆን seblewongele (2007) ላይ የተጠቀሰው ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚያስተምሩ በእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረገው የክፍል ደረጃ ከቀደምቶቹ ስራዎች የተለየ ሆኗል፡፡

እነዚህ አጥኚዎች ጥናታቸውን ያካሄዱት በዩኒቨርሲቲ፣ በኮሌጅና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጥኚው ስላላጋጠመው ይህንን ክፍተት ለመሙላት ጥናቱ አስፈልጓል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴና አካሄድ

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ ምርምር መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አቀራረቡም ዓይነታዊ በመሆን ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በርዕሱ ጉዳይ ዙሪያ በቀረቡት የፅንሰ ሃሳብ መነሻዎች መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበራቸውን ይፈትሻል፡፡ ቀጥሎ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የኒሞና ስልቶችና የመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች ቀርበዋል፡፡

#### 3.1.1. የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የሚካሄደው በቂልጡ ካራ ወረዳ ትምህርት ቤቶች፡- ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወንድ 820 ሴት 660 በጠቅላላ 1480 ተማሪዎች ሲኖሩ ከአገምሰ በልአ ወንድ 90 ሴት 130 በጠቅላላ 220 ተማሪዎች እና ከቡኬ አካቼ ወንድ 120 ሴት 96 ጠቅላላ 216 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ወንድ 1030 ሴት 886 በጠቅላላ 1916 ተማሪዎች በመማር ማስተማር ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡

#### 3.1.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.1.2.1የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ወለጋ ዞን ነው፡፡ ምርጫው የተካሄደው አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ዞኑ የተመረጠበት ምክንያት ለጥናቱ የሚሆን መረጃ በዓይነትና በመጠን ናሙና ለመሰብሰብ ያስችለኛል የሚል እምነት አጥኚው በማሳደሩ ነው፡፡

#### 3.1.2.2 የትምህርት ቤቱ የናሙና አመራረጥ

በምዕራብ ወለጋ ዞን በቂልጡ ካራ ወረዳ ውስጥ ያሉትን ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በዚህ የንሞና ዘዴ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት በቂ መረጃዎችን ማግኘት ስለሚችል ነው፡፡

#### 3.1.2.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በቂልጡ ካራ ወረዳ ትምህርት ቤቶች ሥር ከሚገኙት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መንገድ በጥናቱ እንዲካተቱ የተመረጡት ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አገምሳ በልአ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው። በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ከዘጠነኛ እስከ አሥረኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለሀገር አቀፍ ፈተና የሚዘጋጁ በመሆኑ በጥናቱ የሚገኘውን ውጤት በተሻለ መጠን አስተማማኝ ለማድረግ አጥኚው በተጠኚዎች ላይ ረዘም ላለጊዜ ምልከታ ለማድረግ በመሆኑ ዘጠነኛክፍል በአመቺ የናሙና አመራሪጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከፍ ሲል እንደተጠቆመው የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ምክንያት ከትምህርት ቤቶቹ የሚለዩበት ጊዜያት አጭር በመሆናቸው ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለማያስችሉ ነው።

#### 3.1.2.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለጥናቱ የተመረጡት በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስት' ከአገምሳ በልአ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት መምህራንና ከቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ መምህር በድምሩ 6 ተጠኚ መምህራን በጠቅላይናሙና (Compessive Sampling) ዘዴ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

#### 3.1.2.5 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2009 ዓመተምህረት ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ጥናቱ አካቷል፡፡በመሆኑም በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙት በቂልጡ ካራ ወንድ 820 ሴት 660 ድምር 1480 ፣አገምሳ በልኣ ወንድ 90 ሴት 130 ድምር 220 እና ቡኬ አካቼ ወንድ 120 ሴት 96 ድምር 216 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ወንድ 1030 ሴት 886 ድምር 1916 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከላይ አጠቃላይ ከተገለጹት ተማሪዎች 15 ፐርሰንት በመውሰድ ያገኘሁትን እንደገና በዕጣ የመውጣት ዘዴ (Lottery system) በመጠቀም ወንድ 78 ሴት 52 በድምሩ 130 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ዕጣው የመውጣት ዘዴ ክፍል ውስጥ

ያሉትን የወንድ ብዛትና ሴት ለይተው በማውጣት ለእያንዳንዳቸው ለየብቻ ከየክፍሉ ወንድ ሶስት ሴት ሁለት በመምረጥ የዕጣ ናሙና ተካሂዷል፡፡ይህ የናሙና መምረጫ እኩል መጠንና አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸውን ወረቀት አዘጋጅተው በእያንዳንዱ አባል ስም አንፃር የተመለከቱትን ቁጥር በማዘጋጀት በወረቀቶች ላይ በመጻፍና በመጠቅለል የተፈለገውን የናሙና ቁጥር እስከሚገኝ ድርስ አንድ በአንድ የተጠቀለለውን ወረቀቶች በማውጣት በመመዝገብ ናሙና ተመርጧል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.2.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ጥናቱን ለማካሄድ ምልከታ የቃለመጠይቅና የጽሑፍመጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎችተደጋጋፊነት ያላቸው በመሆናቸው ለጥናቱም ተፈጊላውን አስተማማኝ መረጃ ያስገኛል ተብሎ ይታመናል።

### 3.2.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በዚህ ጥናት የክፍል ውስጥ ምልከታ እንደዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተደርጎ የተወሰደ ሲሆን የእያንዳንዱን ተጠኚ መምህር ለመመልከት ሲባል በሁለት ዙሮች ተከናውኗል። የክፍል ምልከታው በዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት ሊመርጥ የቻለውበመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በቀጥታ የሚያሳይ በመሆኑ ነው። የምልከታ መቆጣጠርያ ቅጹም Dornyei (2001) በቀረበው Cheeklist መሠረት የተነሳሶት ስልትን የሚያመለክቱ ነጥቦች በዝርዝር ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህምበምልከታው የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታና አደረጃጀት፣መምህሩ ከተማሪዎችጋር ያለውን ግንኙነት፣ የመምህሩ የተነሳሶት(የማነሳሻ) ስልት አተገባበር በመቆጣጠሪያ ቅፁ ላይ ሰፍረዋል። ጥያቄዎቹም “አዎ” ወይም “አይደለም” የሚሉ አማራጭ መልሶችን ይዘዋል፡፡ በተጨማሪም ተመልካቾቹ አስተያየቶችን እንዲያሰፍሩ ዕድል የሚሰጡ ጥያቄዎች በምልከታ ቅጹ ላይ ተካተዋል፡፡ የመቆጣጠሪያ ቅጹ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ከታየ በኃላ በአጥኚው አማካሪ ተገምግሞና አስተያየት ተሰጥቶበት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ከምልከታው የሚገኘውን የመረጃ አስተማማኝ ለማድረግ አጥኚው በተጨማሪ አንድ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህርና አንድ በእንግሊዘኛ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህር ምልከታው

በሚካሄድባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተገኝተው የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅጹን በመሙላት በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። አጥኚው በክፍል ምልከታ ወቅት መረጃው አስተማማኝ እንዲሆን በማሰብ ምልከታውንም ተከታትለዋል።

### 3.2.3. የጽሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት የጽሑፍ መጠይቅ ከምልከታው የተገኘውን ውጤት ለማጠናከር በአጋዥነት የቀረበ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን የተመረጠበት ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ለመሰብሰብ የሚያስችል በመሆኑና መምህራኑ በጊዜው የሚጠቀምባቸው የማነሳሻ ስልቶች ምንምን እንደሆኑ ሊጠቁም የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ መጠይቁ ተዘጋጅቶ የቀረበው በናሙናነት በተመረጡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ነው። አዘገጃጀቱም Dornyei (2001) ሀሳብን መሠረት ያደረገ ሲሆን በመጠይቁ የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታን የመምህሩ የክፍል ውስጥ የማነሳሻ ስልት አተገባበርን የሚያውሱ ሠላሳአንድ ዝግ ጥያቄዎች የሊከርት እስኬል መሠረት አድርገው ቀርበዋል፡፡አቀራረቡም በጣምእስማማለሁ፣ መወሰን ያስቸግረኛል፣ አልስማማም እና በጣም አልስማማም የሚሉ አማራጮች በማስፈር ነው። ከዚህ በተጨማሪም የናሙና ተማሪዎቹ አስተያየታቸውን የሚሰጡበት ሦስት ክፍት ጥያቄዎች በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ተካተዋል። የፅሑፍ መጠይቁ በሁለት የአማርኛ መምህራን ዲግሪባላቸው መምህራን ታይቶ በአጥኚው አማካሪ አስተያየት ተስጥቶበት ከተስተከካለ በኃላ በሥራ ላይ ውሏል።

### 3.2.4. ቃለ መጠይቅ

ቃለመጠይቁ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት በሦስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀርበ ነው። አላማውም መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በቋንቋ ትምህርቱ ለማነቃቃት የሚጠቃሙባቸው ስልቶች ለማየትና ስልቶቹን እዲተገብሩ እንቅፋት የሆኑባቸውን በመለየት መረጃ ለመስብሰብነው፡፡ በቃለ መጠይቁም የመምራኑዳራዊ መግለጫ፣ መምህራን ምንም ዓይነት የማነሳሻ ስልቶችን በምን አይነት መንገድ እንደሚተገብሯቸው እንዲሁም የተማሪዎቻቸው የተነሳሶት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ የሚያወሱ ጥያቄዎች በዝርዝር ተካተዋል። ከቃለ-መጠይቁ የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ መረጃዎችን የመሰብሰቡ ሂደት

ተከናውኗል። አማርኛን የሚያስተምሩ ዲግሪባላቸው መምህራን ታይቶ በአጥኚው  አማካሪ ከተገመገመ በኃላ ተግባር ላይ ውሏል።

## 3.3. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ለጥናቱ የዋሉትመረጃዎች የተሰበሰቡበት በቂልጡካሩ ወረዳ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሦስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በናሙና ከተመረጡ ተማሪዎችነው። የመረጃ  አሰባሰቡም ሂደት ለሁለት ወራት ያህል የተካሄደ ነው። በዚህ መሠረት በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚያስተምሩበትን የክፍል ምድብና የክፍለ ጊዜ ድልድልን በመመዝገብ፤ የተደራረቡ ክፍለ ጊዜያትን ለይቶ በማወቅ፤ የክፍል ምልከታውን ለማካሄድ አመቺ የሆኑት ክፍለ ጊዜያት ተመርጠዋል። በዚህም መሠረት በክፍል ምልከታው የመቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ የሠፈሩት የመገምገሚያ ነጥቦች ለሁለት ረዳት ተመልካቾች በአጥኚው አማካይነት ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ በተመረጡት ምድቦች የመማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታው ለሁለት ዙር ተከናውኗል። በዚህም ተጠኚው መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ለማነቃቃት የተጠቀሙበትን የማነሳሻ ስልትና አተገባበሩን ለማየት ተሞክሯል።  ከዚህም ሌላ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀው የጽሑፍ  መጠይቅ ከየትምህርት ቤቱ ለተመረጡት ተተኳሪ ተማሪዎች ተበትኖ እንዲሞላ ተደርጓል የአሞላሉም ሂደት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚማሩት ተተኳሪዎች የትምህርት ሰዓታቸውን በማይነካ ሁኔታ በየትምህርት ቤታቸው እንዲሰበሰቡ በማድረግ የመጠይቁ አሞላል ተገልፆላቸው መጠይቁን  ሞልተዋል፡፡ በተጨማሪም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል  መምህራን ቃለ-መጠይቅ  በማድረግ ወደ ጽሑፍ ተቀይሯል።

ከክፍል ምልከታው የተገኙት ውጤቶችም በአጠኚው በረዳት ተመልካቾች ከታዩበኃላ ልዩነትየተፈጠሩባቸውነጥቦች ተለይተው ከሦስት ተመልካቾች ሁለቱ የተስማሙባቸው ነጥቦች በውጤትነት ተይዘው ለትንታኔ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከየትምህርት ቤቶቹ መረጃየመሰብሰቡ ሂደት ተከናውኗል።

### 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከክፍል ምልከታው፣ ከጽሑፍ መጠይቁናከቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በማጠናከር ተተንትኗል። በምልከታው መቆጣጠሪያቅፅና በመጠይቆቹ የቀረቡትን የጥያቄ ይዘቶች ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንፃር በማደራጀት የተገኙ ውጤቶች ለትንተና ቀርበዋል፡፡ ትንተናውም ዓይነታዊና ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ቀርቧል፡፡ ከሁሉም የመረጃ ምንጮች የተገኙት መረጃ በመማር ማስተማር ሂደትመምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን የማነሳሻ ስልቶች በዝርዝር የሚያሳዩና አተገባበራቸውን የሚመለከቱ በመሆናቸው የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሞክረዋል፡፡

አተናተናቸውም በክፍል ምልከታ የተገኙት ውጤቶችበድግግሞሽ መጠናቸውን ሲገልፁ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኙትን ውጤቶች ደግም "በጣም እስማማለሁ" የሚሉ አዎንታዊ ምላሾች በአንድነት በማጣመር እንዲሁም "አልስማማም፣ በጣም አልስማማም" የሚሉትን አሉታዊ ምላሾች በአንድነት በማቀናጀት በመቶኛ ተሠርቶ ቀርቧል።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤቶች

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጡትመሳሪያዎች አማካይነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን ለጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችን መልስ መስጠት ነው፡፡ በዚህመሠረት ከየትምህርት ቤቶቹ የተገኙ ውጤቶች በመቶኛ ተሰልተውና የተግባር ድግግሞሽ መጠናቸው በቁጥር እየተገለፀ በገላጭ የምርምር ዘዴ አማካይነት በገለፃ ቀርቧል።

**ሠንጠርዥ አንድ ፡የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና አደረጃጀት**

| ተ.ቁ | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ | አማራጭ መልሶች | ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂ/ካ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት |
| 1.1 | የመማሪያ ክፍሉ በቂ ስፋት አለው | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 1.2 | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ መቀመጫዎች ለተማሪዎች በቂ ናቸው | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 13 | የመማሪያ ክፍሉ ንጽሕና የተጠበቀ ነው | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 1.4 | ንጹሕ አየር በመማሪያ ክፍል መስኮት ይገባል | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |
| 1.5 | በመማሪያ ክፍሉየሚገኘው ጥቁር ሰሌዳ ለሁሉም በሚታይ መልኩ ተቀምጧል ? | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |

Young (1999) የክፍል ውስጥ ሁኔታን በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ይህም ማለት ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ ከተማሪዎች በተስተምሮት ወቅት ሀሳባቸውን' አመለካከታቸውን' እምነታቸውን ለመግለጽ አይቸገሩም፡፡

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መመለከት እንደተቻለው በሦስቱ ተጠኚ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በቂ ስፋት የሌላቸው መሆኑ ተርጋግጧል። ይህ ሊሆን የቻለው በክፍል ምልከታው እንደተረጋገጠው በሦስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች የመማሪያ ክፍል ውስጥ እስከ ሰባ ስድስት የሚደርሱ ተማሪዎች በመገኘታቸው ነው። በዚህ የተነሳ በየትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መቀመጫዎች አነስተኛ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም የመማሪያ ክፍሎቹ ንፅህና ያልተጠበቀ መሆኑ በምልከታው ተረጋግጧል። ይሁን እንጂ በመማሪያ ክፍሎቹ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ያላቸው በመሆኑ መተፋፈንና መጨናነቅ መኖሩ በክፍል ምልከታ ወቅት ሊረጋገጥ ችሏል። በአንጻሩም በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ጥቁር ሠሌዳዎች ለተማሪዎች በሚታይ መልኩ በተገቢ ስፍራ ተቀምጦ ይታያል።

### 4.1. መምህሩ የሚጠቀምባቸውን የማነሳሻ ስልቶችና አተገባበር በሚመለከት የቀረበ ትንተና

**ሠንጠረዥ ሁለት፡- የመምህሩ አርአያነት በሚመለከት ከክፊል ምልከታ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂ/ካራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች |
| | | | በቁጥር | በቁጥር |
| 2.1 | መምህሩ በሰዓት ወደ መማሪያ ክፍሉ ገብተዋል? | አዎ | 4 | 5 |
| | | አይደለም | 2 | 1 |
| 2.2 | መምህሩ ደንብ ልብሳቸውን ለብሰዋል? | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው ከየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ ተጠኚዎች መምህራን የደንብ ልብሳቸውን ለብሰው በሰዓት በማስተማሪያ ክፍላቸው የተገኙ ሲሆኑ የተወሰኑ ተጠኚ መምህራን በሰዓት ወደ ክፍላቸው አለመግባታቸውም ይታያል፡፡

አንድ መምህር የመማር-ማስተማር ሂደቱ የተቃና እንዲሆንለት ጥሩ የመምህር ባሕሪይን ሲላበስ ነው። መምህሩ በሰዓቱ በማስተማሪያ ክፍሉ ተገኝቶ ሥራውን በትጋት እያከናወነ ለተማሪዎቹ አርአያ ከሆነ የተማሪዎቹ የመማር ፍላጎት እየጨመረ ሊሄድ ይችላል። ይህም በክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪው መካከል መልካም የሆነ ግኑኝነት ለመፍጠር አመቺ መንገድ ይሆናል።

### 4.1.1. መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪ ግኑኝነት መፍጠር

በክፍል ውስጥ በሚደረገው በመምህር ተማሪ ተረክቦ መልካም የሆነ ግኑኝነት እንዲኖር ያስፈልጋል። ለዚህም walodkowski (1986) ጠቅሰው እንደገለጹት፤ መምህር ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ማሳየት ከተማሪዎቻቸው ለሚነሱ ጥያቄዎች በትህትና መልስ መስጠት የተማሪዎቻቸውን ስም ለይተው በመጥራት ማሳተፍና ስራቸውን መከታተል በመምህር ተማሪ መካከል ያለውን ግንኙነት አዎንታዊ ጎን እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በአንፃሩም Good and Brophy (1994፤ 215) እንደገለፁት የመምህር-ተማሪ መልካም ግንኙነት አሉታዊ ከሆነ ተማሪዎቹ ለጭንቀትና የትምህርት ፍላጎት ማጣት ስለሚያደርጉ መሠረታዊ ተነሳሽነትን መፍጠር አዳጋች ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ከተካሄደው የክፍል ምልከታ የሚከተለውን ምላሽ ተገኝቷል፡፡

**ሠንጠረዥ ሶስት፡- የመምህር ተማሪ ግንኙነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂ/ካራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች |
| 3.1 | የአማርኛ መምህር ለተማሪዎቻቸው ትህትናን ያሳያሉ | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3.2 | የአማርኛ መምህር ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ያሳያሉ | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | - |
| 3.3 | የአማር ኛመምህር ለተማሪዎቻቸው የቁጡነት ባህሪ ይታይባቸዎል? | አዎ | 1 | - |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 3.4 | የአማርኛ መምህር በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን ይከታተላሉ | አዎ | 2 | 5 |
| | | አይደለም | 4 | 1 |
| 3.5 | የአማርኛ መምህር ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ ሲጠይቋቸው ለመመለስ ፈቃደኛ ናቸው | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተገለፀው በአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መምህራን ፈገግታን፤ ፈቃደኝነትን ለተማሪዎቻቸው በማሳየት መልካም መምህር ተማሪ ግንኙነት ሲፈጥሩ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን ምልከታው በተካሄደባቸው ቀናት ተግባራቱን በአብዛኛው ሲፈጽሙ አልታዩም። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን የመከታተል ተግባር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለስድስት ጊዜ ድግግሞሽ ታይቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቸ ውስጥ ጥሩ የሆነ የመምህር ተማሪ ግንኙነት መኖሩ በቅልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን የመምህር-ተማሪ ግንኙነት ፈገግታን ለማሳየት አሉታዊ ጎን እንደሚታይበት ነው። ይህ የመምህር ተማሪ ግንኙነት ለተማሪዎች በቀረበ የፅሑፍ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ አራት፡- የመምህር -ተማሪ ግንኙነት የሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማም | | መልስ ያልሰጡ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 4.1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በስሜ ጠርቶ መልስ እንዲመልስ ያደርጉኛል | 29 | 23.3 | 41 | 31.5 | 21 | 16.1 | 26 | 20 | 13 | 10 | - | - |
| 4.2 | ለአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በፈገግታ ጥያቄዎችን ይመልሱልኛል | 24 | 18.4 | 49 | 37.6 | 22 | 16.9 | 25 | 19.2 | 10 | 7.6 | - | - |
| 4.3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የክፍል ሁኔታ እንደአስፈላጊነቱ ይቆጣጠራሉ | 36 | 27.6 | 51 | 39.2 | 16 | 12.3 | 14 | 10.7 | 8 | 6.1 | 5 | 3.8 |
| 4.4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የተሳሳተ መልስ ሲመልስ በትህትና እርማትይሰጡኛል | 29 | 22.3 | 56 | 43 | 17 | 13 | 18 | 13.8 | 9 | 6.9 | 1 | 0.7 |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው በመምህር-ተማሪ መካከል መልካም ግንኙነት ለመፍጠር በቂልጡ ካራ ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን የተማሪዎችን ስም በመጥራት መልስ እንዲሰጡ በተመለከተ 53.84 ፐርሰንት ያህሉ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 46.15 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን ፈገግታን

የሚያሳዩ 56.15 ፐርሰት ያህሉ አዎንታዊ መልስ ሲመልሱ 43.84 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ መልስ መልሰዋል፡፡ በሌላ በኩል መምህሩ በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን ይቆጣጠራሉ የሚለው ጥያቄ 66.92 ፐርሰንት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 33 ፐርሰንት አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በትህትና እርማት የሰጡ መምህራን 65.38 ፐርሰንት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 34.61 ፐርሰንት አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከጽሑፉ መጠይቁ ምላሽ ለማወቅ የሚቻለው ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ትህትናን ለማሳየት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንደሚያከናውኑ ነው፡፡ ይሁንና በክፍል ምልከታ ወቅት በትህትና ለተማሪዎቻቸው መልሶችን የመስጠት ተግባር በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በከፊል ሲጓደል ታይቷል፡፡ በመሆኑም በምልከታው ውጤትና በመጠይቁ ውጤት መካከል ተቃርኖ አሳይቷል፡፡

#### 4.1.2 የመማሪያ ክፍሉን አስደሳችና አጋዥ ስለማድረግ በሚመለከት የቀረበ ትንተና

**ሠንጠረዥ አምስት፡- አስደሳች የመማሪያ ክፍል ሁኔታን መፍጠርን በሚመለከት በክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | የቀረበጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የተጠኚመምህራንትምህርትቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡካራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት |
| 5.1 | የአማርኛ መምህሩ በየ ትምህርቱ ጣልቃ ቀልዶችን ያቀርባሉ? | አዎ | 2 | 4 |
| | | አይደለም | 4 | 2 |

የክፍል ውስጥ ሁኔታ ማለት Pintrich and shuunk (2002: 322) ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ማህበራዊ' ስነ ልቦናዊ እና ስሜታዊ ባህሪይን የተላበሰ የመማሪያ ክፍል ማለት ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ወይም ፌዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው በአብዛኛው ጊዜ በመምህር ተማሪ መልካም ግንኙነት አማካኝነት ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደተቻለው በትምህርቱ ጣልቃ ቀልድን እያስገቡ ትምህርቱን አዝናኝ በማድረግ ሂደት የተከናወነው በአገምሳ በልአ ሁለተኛ ደረጃ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አራት ጊዜ ሲሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ከላይ በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው ተማሪዎች ተነሳሽነታቸውን ከፍ እያለ እንዲሄድ ማነቃቂያና ወደ ትምህርቱ ይዘት በሚያደርሱና በሚያዝናኑ ቀልዶች መምህሩ መጠቀም ይጠበቅበታል፡፡ይህንን ተግባር ለማረጋገጥ በፅሑፍ መጠይቁ የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው 33 ፐርሰንት ያህሉ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 66.7 ፐርሰንት የሚሆኑ የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ የሚገኙ መምህራን ትምህርቱን አዝናኝ ለማድረግ በተቻለ ሁኔታ ጥረት የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው፡፡

**ሠንጠረዥ ስድስት፡- በቡድን በጥንድ መደራጀትን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭመልሶች | የተጠኚ መምህራን ት/ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተ ኛደረጃ ትምህርት ቤት |
| 6.1 | የአማርኛ መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን እንዲደራጁ አድርገዋል? | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |
| 6.2 | የአማርኛ መምህሩ ተማሪዎችን በጥንድ እንዲደራጁ አድርገዋል? | አዎ | 1 | 3 |
| | | አይደለም | 5 | 3 |
| 6.3 | በቡድን ሥራ ወቅት የቡድን መሪነ በር? | አዎ | _ | _ |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 6.4 | በቡድን ሥራ ወቅት የሚሳተፉት ሁሉም ናቸው? | አዎ | _ | 1 |
| | | አይደለም | 6 | 5 |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸውን በቡድንና በጥንድ ሲያደራጁ ታይተዋል፡፡ በመማር-ማስተማሩም ሂደት አጋዥ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ለመፍጠር የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እርስ በርስ እንዲረዳዱ እንዲተጋገዙ በማድረግ ንቁ የሆነ የተማሪ ለተማሪ መልካም ግንኙነት መፍጠር ይቻላል፡፡ Dornyei (2001)። ይሁንና ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የታየው በቡድንና በጥንድ ተማሪዎችን የማደራጀት ተግባር ከአገምሳ በልአ እና ከቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በቂል ጡካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቡድን የማደራጀት ተግባር አንድ ጊዜ ሲፈፀም በቡኬ አካቼ እና በአገምሳ በልአ ሁለተኛ ደረጃት ትምህርት ቤቶች ሁለት ጊዜ ድግግምሽ መተግበሩን በክፍል ምልከታው ተረጋግጠዋል፡፡

የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጥንድ በማደራጀት የእርስ በርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ የማድረግ ተግባር ምልከታው በተከሄደባቸው ቀናት አንድ ጊዜ ብቻ ሲተገበር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ሦስት ጊዜ ተግባራዊ ሲሆን ታይቷል፡፡ በመሆኑም የአገምሳ በልአ እና የቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸውን በቡድንና በጥንድ እያደራጁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በቡድን ሥራ ወቅት የቡድን መሪ መርጦ በራስ የመተማመንን ብቃት ለማጎልበት በሦስቱም ትምህርት ቤቶች አልተሞከረም።

በቡድንና በጥንድ ማደራጀትን በሚመለከት ከተማሪዎች የተገኘው የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ እንደሚያስረዳው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቡድን የሚያሳትፉ 16.7 ፐርሰንት ያህል ሲሆን በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 33.3 ፐርሰንት ያህል ናቸው፡፡በተጨማሪም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን16.7 ፐርሰንት ያህል በጥንድ አደራጅተው እንዲሳተፉ ሲያደርጉ በቡኬ አካቼ እና በአገምሳ በልአ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ደግሞ 50 ፐርሰንት ያህል ተማሪዎቻቸውን በጥንድ አደራጅተው እንንደሚያሳትፉ ከተማሪዎች የተገኘው የመጠይቅ ምላሽ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች በሰጡት ምላሽ ለማረጋገጥ እንደተቻለው፤

የቡድን መሪ ወይም ፀሐፊ ለመሆን ተነሳሽነትን ከፍ የሚያደርግ ተግባር በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የማይተገበር መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በሦስቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ምስስሎሽ ይታያል፡፡

በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የቡድን ሥራን ለማከናወን የሚቸገሩባቸውን ነጥቦች በቃለ መጠይቁ ሲያስረዱ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ወንበሮች ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ መሆኑን የተማሪዎቹም ቁጥር መብዛት በክፍል ውስጥ ጫጫታ እንዳይፈጠር በመስጋት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የቡድን ሥራን በሚመለከት ምሁራን እንዳብራሩት ጥሩ የሆነ የቡድን ጥምርታ መኖር በተማሪዎች መካከል እርስ በርስ የመተጋገዝና የመተባበር መንፈስ በማምጣት እያንዳንዱ በቡድኑ በቁርጠኝነት እንዲሰራና የትምህርት ፍላጎቱን እያጎለበተ እንዲሄድ ይረዳል፡፡ ይሁንና የቡድን ሥራ ክንውን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዝቅተኛ መሆኑ ከምልከታውና ከመጠይቆቹ ውጤቶች ተረጋግጧል፡፡

**ሠንጠረዥ ሰባት፡- ተማሪ-ተኮር እና መምህር-መር ዘዴን መጠቀም በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ. ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 7.1 | የአማርኛ መምህሩ በክፍል ውስጥ የውይይት መንፈስ እንዲኖር አድርገዋል; | አዎ | 1 | 5 |
| | | አይደለም | 5 | 1 |
| 7.2 | የአማርኛ መምህሩ በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ እንዲኖር አድርገዋል? | አዎ | 1 | 3 |
| | | አይደለም | 5 | 3 |
| 7.3 | የአማርኛ መምህሩ ተማሪ ተኮር ዘዴን ተጠቅመዋል? | አዎ | 2 | 5 |
| | | አይደለም | 4 | 1 |
| 7.4 | የአማርኛ መምህሩ መምህር-መር ዘዴን ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምረዋል? | አዎ | 4 | 1 |
| | | አይደለም | 2 | 5 |

Stren (1983:18) እና Ur (1996:276) እንደገለፁት በጥንት ጊዜ የቋንቋ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በመምህሩ አማካይነት ብቻ ነበረ፡፡ ይህ ዓይነቱ መምህር ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአሁኑ ጊዜ በተማሪ ተሳትፎ ተተክተው ይታያል፡፡

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው፡- በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቡድንና በጥንድ በማሳተፍ አምስት ጊዜ በድግግሞሽ እንዲወያዩና በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ በመካከላቸው የእርስ በርስ የውድድር መንፈስ እንዲኖር በማመቻቸት ትምህርቱን ተማሪ-ተኮር ሲያደርጉ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን ተግባሩን ሁለት ጊዜ ማከነወናቸው በምልከታው ተረጋግጧል፡፡

የተማሪዎች መጠይቅ ምላሹም ይህንን አጠናክሯል፡፡ በሌላ በኩል ከክፍል ምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በአራት ጊዜ ድግግሞሽ መምህር-መር ዘዴን ተጠቅመው የቋንቋ ትምህርቱን የሚያስተምሩ ሲሆን በቡኬ አካቼ እና በአገምሳ በልአ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ የመምህር-መር ዘዴን ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምረዋል፡፡ በመሆኑም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባራዊ የሆነው የማስተማር ዘዴ መምህር- መር መሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ፡-ስምንት ተማሪዎችን በተናጠል የማሳተፍ ተግባርን በሚመለከት በክፍል ምልከታ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 8.1 | የአማርኛ መምህሩ በጥቁር ሳሌዳ ላይ እንዲፅፉ ተማሪዎች አደርገዋል? | አዎ | 2 | 3 |
| | | አይደለም | 4 | 3 |
| 8.2 | የአማርኛ መምህሩ ተማሪዎችን ተራ በተራ ጥያቄ በመመለስ እንዲሳተፉ እድል ሰተዋል? | አዎ | 3 | 6 |
| | | አይደለም | 3 | 0 |

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተገለፀው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን ይልቅ በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸውን ከመቀመጫው እየተነሱ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መልሶቻቸውን እንዲፅፉ አድርገዋል ፡፡ ይህም ተግባር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሦስት ጊዜ ድግግሞሽ መጠን ሲታይ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን ሁለት ጊዜ ብቻ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ እንዲሳተፉ እድሉን የመስጠት ተግባር በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኩል በከፊል የተፈጸመ ሲሆን በአገምሰ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ይህንን ተግባር በተመለከተ የአገምሳ በልአ እና የቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች መምህራን ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸው ምላሻቸውን ሲሰጡ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

በመማሪያ ክፍሎች ውሰጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸው ከ70-75 ቢደርሱም ተራ በተራ ለማሳተፍ አመቺ ሁኔታ እየፈጠርን እንጠቀማለን ሲሉ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማሳተፍ ፍቃደኝነት የሚታይባቸው ተማሪዎች ጥቂት በመሆናቸው ተሰትፎ ዝቅተኛ መሆኑን ከቃለ -መጠይቁ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህር የፈጠራ ችሎታቸውን እንደሚያበረታቱላቸው አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት የገለፁ ከቂል ጡካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከአገምሳ በልአ፤ ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 51.51 ፐርሰት የሚሆን ሲሆኑ አሉታዊ ምላሻቸውን የሰጡት18.3 ፐርሰንት የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን 21 ፐርሰንት አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለዚህሀሳብ 23.8 ፐርሰንት የሚሆኑ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና 18.61 ፐርሰንት የሚሆኑ የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል አማካይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች ያላቸውን የፈጠራ ችሎታ የቋንቋ መምህራኑ በከፊል እንደሚያበረታቱላቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት ሆነ በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ መሆኑ ከመጠይቁ ውጤት ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

### 4.1.3 ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና

**ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡-ለተማሪዎች የተሰጡ-ምጋቤ ምላሾችን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 9.1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ የመብረታቻ ቃላትን ይጠቀማሉ? | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |
| 9.2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ስመልሱ የምስጋና ቃላትን ይመልሳሉ? | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | -- |
| 9.3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ስመልሱ የነቀፊታ ቃላትን ይጠቀማሉ? | አዎ | - | -- |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 9.4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ጥያቄ ጠይቀው ከተማሪዎቻቸው መልስ ሲያጡ የነቀፌታ ቃላትን ይጠቀማሉ? | አዎ | 1 | -- |
| | | አይደለም | 5 | 6 |

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን የትምህርት ተግባራት ለማከናወን እና ለመማር ካለፍላጎት እና ጉጉት የሚመነጭ ሳይሆን በተለየ ሁኔታ ከተለያዩ አካላት ተፅዕኖችን ማነቃቂያዎችን በመቀበል የሚመነጭ ነው Ur (1996: 275)፡ ፡

ከላይ በሠንጠረገፑ ለማየት እንደተቻለው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ም ሆነ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥያቄ ሲጠይቋቸው የማበረታቻ ቃላት በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ በመጠቀማቸው ምስስሎሽ ታይቶባቸዋል፡፡

ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ እና በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን የምስጋና ቃላት ተጠቅመዋል፡፡ ይሁንና በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምስጋና ቃላትን የመጠቀም ተግባር በአንድ የክፍል ምልከታ ወቅት ሳይታይ በመቅረቱ መምህራኑ ተግባሩን ሲያጓድሉ ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራንም ሆነ በአገምሳ በልአ ና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን በነቀፌታ ቃላት እንደማይጠቀሙ በክፍል ምልከታው ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራኑ ጥያቄ ጠይቀው ለጥያቄዎቻቸው መልስ ሲያጡ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን በአንድ የክፍል ምልከታ ወቅት“ የዚህ ክፍል ተማሪዎች ሰነፎች ናቸው” የሚል የነቀፌታ ቃል መጠቀማቸውን ከምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን የማስጨብጨብና የሽልማት ምጋቤ- ምላሾችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረቡት የፅሑፍ መጠይቆች የሚከተሉትን ምላሾች ተገኝተዋል፡፡ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 23.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ እንደሚጨበጨብላቸው በመግለፅ አዎንታዊ ምላሻቸውን ሲሰጡ 56.1 ፐርሰንት የሚሆኑ ደግሞ ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ የማይጨበጨብላቸው መሆኑን በመግለፅ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ 31 ፐርሰንት ያህሉ እንደሚጨበጨብላቸው በመግለፅ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 50.1 ፐርሰንት የሚሆኑ ደግሞ እንደማይጨበጨብላቸው በመግለፅ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በሌላ በኩል 28 ፐርሰንት የሚሆኑት በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሚሠጡት ሙከራዎች ጥሩ ውጤት ስናመጣ ከመምህሮቻችን ሽልማት እናገኛለን በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 51 ፐርሰንት የሚሆኑ ደግሞ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተወል፡፡ በተጨማሪም በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ተማሪዎች 11.5 ፐርሰንት የሚሆኑት ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ከመምህሮቻቸው ሽልማት እንደሚሰጣቸው ሲገልፁ 67 ፐርሰንት የሚሆኑ መላሾች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ይሁንና በክፍል ምልከታ ወቅት ለማየት እንደተቻለው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ትክክለኛ መልስ ለሚመልሱ ተማሪዎች ሲያስጨበጭቡም ሆነ ሲሸልሙ አልታዩም፡፡ ለመምህራን በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃት ምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን የክፍሉ ፀጥታ እንዳታይታወክ በመስጋት ትክክለኛ መልስ ለሚመልሱ ተማሪዎች እንደማያስጨበጭቡ ሲገልፁ ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎችም ሽልመው እንደማያወቁ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ከፅሑፍ መጠይቁ ምላሽ ላይ የተገኘው አዎንታዊ ውጤት ከመምህሩ የቃለ መጠይቅ ተቃርኖ እንደሚያሳይ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከተገኘው ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በተማሪዎቻቸው የሥነ-ሥርዓት መጓደል የተነሳ አንዳንድ የነቀፌታ ቃላትን እንደሚጠቀሙ ሲረጋገጥ በአንፃሩም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን እንደ “በጣም ጥሩ”፣ ጎበዝ፣ በርታ አመሰግናለሁ፣ አግኝተሃል (ሻል)፣ አንበሳ ፣የመሳሰሉ የማበረታቻና የምስጋና ቃላትን በተስተምህሮቱ ወቅት እንደተጠቀሙ ከምልከታውና ከቃለ መጠይቁ ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 4.1.4 የመርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም በሚመለከት የቀረበ ትንተና

የመማር-ማስተማሩ ሂደት ተፈላጊ የሆነው ተነሳሽነትን ለማሳደግ ከሚያስችሉ አንዱ በመርጃ መሣሪያዎች ተጠቅሞ ማስተማር ነው፡፡የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሲባል፣ በመቅርፀ-ድምፅ የተቀረፁ ንግግሮች ፤የተለያዩ መጽሐፍት ፤መጽሔቶችንና ጋዜጦችን መጠቀም ያካትታል፡፡ በዚህም መሠረት በክፍል ምልከታውንና በጽሑፍ መጠይቁ አማካይነት የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ታይቷል፡፡

**ሠንጠረዥ አስር የመምህሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 10.1 | የአማርኛ መምህሩ ከማስተማሪያ መጽሐፍ ሌላ በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ መረጃ መሣሪያ ተጠቅመው አስተምሯል? | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |
| 10.2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ መቅረፀ ድምፅ ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምሯል? | አዎ | -- | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 10.3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ሌሎች ፅሑፎችን በመረጃነት ተጠቅመው አስተምሯል? | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |

ከላይ በሠንጠረዥ ለማየት እንደተቻለው በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃም ሆነ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን መቅረፀ ድምፅ ተጠቅመው እንዳላስተማሩ ከክፍል ምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁንና ሌሎች ስዋሰውን፣ ድርሰትን፣ አንቀጽን ፣ቅኔን፣ ልቦለድን የሚያወሱ ፅሑሮች በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በክፍል ተጠቅመው ሲያስተምሩ ታይቷል፡፡በመሆኑም በሦስቱም ትምህርት ቤቶች መካከል ተመሳሳይ የሆነ የመርጃ መሣሪያ አጠቃቀም መኖሩን በምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስቸጋሪ የሆኑ ትግበራዎችን በግልፅና በቀላል ፣ሳቢ እና ተወዳጅ ለማድረግ እንደሚያግዙ Sebele wangle (2007)፣ walodk Awski (1986)ን ጠቅሰው ገልፀዋል፡፡ ይህንን ተግባር ከተማሪዎች ከተገኘው የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ለማረጋገጥ እንደተቻለው መምህራኑ መቅርፀ ድምፅ ተጠቅመው እንደማያስተምሩ 54% ያህሉ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትተማሪዎች ሲገልፁ በተመሳሳይ መልኩ 57.6% የሚሆኑ በአገምሳ በልአ እና

በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መምህራኖቻችው መቅረፀ ድምፅን ተጠቅመው እንደሚያስተምሯቸው በምላሻቸው አረጋግጠዋል፡፡ የቀሩ 16% የሚሆኑ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች 14% የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መቅረፀ ድምፅን በትምህርት መርጃ መሣሪያነት ተጠቅመው እንደሚያስተምሯቸው ገልፀዋል፡፡ ተጠኚ መምህራን እንደገለፀት ካለው የክፍለ ጊዜ ማነስ አኳያ መቅርፀ ድምፅን በትምህርት መርጃ መሣሪያነት ተጠቅመው እንደማያውቁ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል “ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ሌላ የተዘጋጁ ጽሑፎችን በትምህርት መርጃነት መምህሮቻቸው ይጠቀማሉ” በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች 60% ያህሉ ሲሆኑ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ደግሞ 72.2% ናቸው፡፡ ከዚህ ውጤት እና ከክፍል ምልከታው መረዳት የሚቻለው በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ጽሁፎችን በትምህርት መርጃ መሣሪያነት መምህራኑ እንደሚጠቀሙ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው ምላሽም አጠናክሮታል፡፡

## 4.2. የትምህርቱን ይዘት ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ በሚመለከት የቀረበ ትንተና

የመማር-ማስተማሩ ሂደት አንዳንድ ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችንና ትግበራዎች ለምን ዓላማ እንደተዘጋጁ ግልፅ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ የትምህርቱን ይዘቶችንና ክንውኖችን ዓላማ ለተማሪዎቹ ማሳወቅ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የማነሳሻ ስልት ከፍ እንዲል የትምህርቱን ይዘቶች ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የትምህርቱን ይዘቶች ምን ያህል ተስማሚ እንደሚያደርግና አላማውንም ለተማሪዎቹ ምን ያህል እንደሚያሳውቁ ለተማሪዎች በቀርበ የፅሑፍ መጠይቅ ለማየት ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥአ ሥራ አንድ፡-የትምህርቱን አላማ ማሳወቅ በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | መልስ ያልሰጡ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህር እያንዳንዱን ክንውን ዓላማ ያሳውቁኛል | 42 | 32.3 | 27 | 20.7 | 19 | 14.6 | 15 | 11.5 | 20 | 15.3 | 7 | 5.3 |

በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ጥሩ ዓላማን ይዘው ለመማር ከተነሱ ለትምህርቱ ያላቸው የተነሳሶት ደረጃ ከፍ ያለ እንደሚሄድ Gardner and Mscintyre (1993:133) ያስረዳሉ፡፡ ከዚሁ ሠንጠረዥ ማየት እንደሚቻለው የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የትምህርቱን ክንውን ዓላማ ያሳውቃሉ በማለት ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች 53.07 ፐርሰንት ተማሪዎች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በአንፃሩ 46.92 ፐርሰንት ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው በሶስቱም ትምህርት ቤቶች መምህራን የትምህርቱን ክንውን ዓላማ ለተማሪዎቻቸው እንደሚያሳውቁና ግልጽ እንደሚያደርጉ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ አሥራ ሁለት፡-የትምህርቱን ይዘት ሳቢነት በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | መልስ ያልሰጡ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 12.1 | በአማርኛ ቋንቋትምህርት ወቅት የሚቀርቡ ይዘቶች በህይወት ልምዴ ከማውቃቸው ዝምድና አላቸው | 33 | 25.3 | 51 | 39.2 | 13 | 10 | 16 | 12.3 | 12 | 9.2 | 5 | 3.8 |
| 12.2 | በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉ ምንባቦች | 32 | 24.6 | 50 | 38.4 | 18 | 13.8 | 14 | 10.7 | 14 | 10.7 | 2 | 1.5 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ያስደስቱኛል | | | | | | | | | | | | |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው የትምህርቱ ይዘቶች በህይወት ልምዴ ከማውቃቸው ጋር ዝምድና አላቸው በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች 64.61 ፐርሰንት ያህል ናቸው፡፡ ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ የሆኑ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ የትምህርት ይዘቶቹ ከተማሪዎች ባህል፣ አካባቢና ከህይወት ልምዳቸው ጋር እየተዛመዱ አዝናኝና ቀላል በሆነ መንገድ ማቅረብ ከቻሉ ተማሪዎቹ ለትምህርት ያላቸው ፍላጎትና ተነሳሶት እየጨመረ እንደሚሄድ Gardner and Mancityre (1993)፣ William and Burden (1997) ገልፀዋል፡፡ የቋንቋ መምህራን ይህንን ተግባር እንዳስፈላጊነቱ እንደሚያከናውኑ እንደመሆናቸው በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ ይሁንና በክፍል ምልከታ ወቅት የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ከሚያውቃቸው ከአካባቢያቸው ከሚያዩዋቸው ነገሮች ጋር እያዛመዱ ለማስተማር የተገበሩ የአገምሳ በልአና ቡኬ አከቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁለት መምህራንና በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ አንድ መምህር ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ በክፍል ምልከታው ከታየው እውነታ ጋር ተዛምዶ ሊታይበት አልቻለም፡፡

### 4.3 የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሶትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና

ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተነሳሶት እንዲኖራቸው በቅድሚያ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎቹ ፍላጎት ተነሳሽነትን፤ በራ ስመተማመንን ፤ድፍረትን ሊያስገኝ ወይም ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ይህንንም ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆችና ምልከታዎች ለማየት ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥአስራ ሶስት፡-የተማሪዎች ፍላጎት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች**

| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | በጣም አልስማማም | መልስ ያልሰጡ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በቁ ጥር | በመ ቶኛ | በቁ ጥር | በመቶ ኛ | በቁ ጥር | በመቶ ኛ | በቁ ጥር | በመቶ ኛ | በቁ ጥር | በመ ቶኛ | በቁ ጥር | በመ ቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13.1 | ለአማርኛ ቋንቋትምህርት ፍላጎት አለኝ | 52 | 40 | 47 | 36.1 | 13 | 10 | 11 | 8.4 | 5 | 3.8 | 2 | 1.5 |
| 132 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ይቀለኛል | 19 | 14.6 | 38 | 29.2 | 38 | 29.2 | 18 | 13.8 | 9 | 6.9 | 8 | 6.1 |
| 13.3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ሲያስተማሩ ትምህርቱ ይገባኛል | 33 | 25.3 | 50 | 38.4 | 16 | 12.3 | 18 | 13.8 | 13 | 10 | - | - |

Gardner and Mscintyre (1993) እና Petty (2004) ተማሪዎች ለሚማሩ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ከፍ ብሎ ተነሳሶታቸው እንደሚጨምር መምህሩ በሚያበረታታ መልኩ የራሱን የትምህርት ፍላጎት ለተማሪዎች ማሳየት የሚያስደንቁና የሚያስገርሙ ሃሳቦችን በትምህርቱ መሃል ጠልቃ በማስገባት ተማሪዎችን መነቃቃት አለበት፡፡

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው 76.15 ፐርሰንት የሚሆን በቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለቋንቋ ፍላጎት እንዳላቸው በማመልከታቸው ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ ምላሽና 23.84 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ለትምህርቱ ፍላጎት እንደለላቸው የሚያመለክት አሉታዊ ምላሽ ተገኝተዋል፡፡ የአማርኛ ትምህርት ይቀለኛል በማለት አዎንታዊ ምላሻቸውን የሰጡ 43.84 ፐርሰንት የሚሆኑ ቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ለዚህ ሀሳብ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ከሶስቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች 56.15 ፐርሰንት የሚሆኑ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ትምህርት ሲንማር ይገባናል በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት 63.84 ፐርሰንት ሲሆኑ በአንፃሩም ሶስቱም ትምህርት ቤቶች 36.15 ፐርሰንት አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው በቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አብዛኛዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የቋንቋ ትምህርቱ እንደሚቀላቸው የገለጹት ተማሪዎች ቂልጡ ካራ ሁለተኛ

ደረጃ ትምህርት ቤት ጥቂቶች ናቸው፡፡በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚመለከት የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፡፡ አብዛኛው ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ምክንያት የተገለጸው አማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ከ5ኛ ክፍል ስለሚጀምሩ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ የሆኑና አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው የሆኑ እኩል ሊወዳደሩ አለመቻላቸው ነው፡ የሚል ግምታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽና ግምገማ ሊቃረን ችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ አሥራ አራት፡- ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት በሚመለከ ት ምልከታ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የተጠኚ መምህራን ትምህት ቤቶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አማራጭ መልሶች | ቂልጡ ከራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | አገምሰ በልአ እና ቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 14.1 | ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸው ውሰጥ በሰዓት ተገኝተዋል? | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | _ |
| 14.2 | ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ሲያስተምሩ በፀጥታ ያዳምጣሉ? | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | _ |
| 14.3 | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ወቅት እርስ በርሳቸው በሹክሹክታ ይነጋገራሉ? | አዎ | 1 | _ |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 14.4 | ተማሪዎች መምህራቸው ሲያስተምሯቸው የግል ሥራቸውን የሚሠሩ አሉ? | አዎ | 1 | _ |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 14.5 | መምህሩ ሲያስተምሩ ማስታወሻ የሚይዙ ተማሪዎች ብዙ ነበሩ? | አዎ | 3 | 5 |
| | | አይደለም | 3 | 1 |
| 14.6 | ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቻቸው መልስ ሲመልሱ በጥንቃቄ ይከታተላሉ? | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | _ |

Dornyei (2001) እንገለፁት ቋንቋን ለረጅም ጊዜ በፍላጎት መከታተል መልካም ወደ ሆነ አመለካከት ለማሻገር ተማሪዎችን ውጤታማ ልያደርጓቸው ይችላል፡፡ስለዚህ ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው፡- የመማር-ማስተማር ክንውን ሂደት በተወሰነለት ጊዜ እንዲጠናቀቅና ተማሪዎች ተገቢውን ዕውቀት እንዲያገኙ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸው በሰዓቱ መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡በዚህም መሠረት ይህ ተግባር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ሲያገኝ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን ሁለት ጊዜ ድግግሞሽ ተግባራዊ ሳይሆኑ ቀርቷል፡፡በተስተምህሮቱም ወቅትም ተማሪዎች እርስበርሳቸው ሲያንሾካሽኩ በፀጥታ የማዳመጥ ተግባር ሙሉ በሙሉ በአገምሰ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተተገበረ ሲሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባሩ አንድ አንድ ጊዜ ተጓድሎታይቷል፡፡

በተጨማሪም በነበሩት የምልከታ ጊዜያት በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች መምህሮቻቸው ሲያስተምሩ በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ ማስታወሻ ሲይዙ ታይቷል፡፡በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግን ማስታወሻ የመያዝ ተግባርን አንድ ጊዜ ብቻ ተጓድሎ ታይቷል፡፡በተጨማሪም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንድ የምልከታ ጊዜ የግል ሥራቸውን የሚሠሩ ተማሪዎች እንደነበሩ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ተማሪዎች ከመምህራቸው በተጨማሪ የክፍል ጓደኞቻቸው የሚያቀርቡትን ሃሳብ በመከታተል ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ማየት ይኖርባቸዋል፡፡ይሁንና ይህ ተግባር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ ሲተገበር ቢታይም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሁለት ጊዜ ድግግሞሽ ሳይተገበር ቀርቷል፡፡

ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው የመማር-ማስተማሩ ሂደት በአትኩሮት የመከታታል ተግባር በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ በአብዛኛው ሲከናወን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃትምርት ቤት ግን አልፎ አልፎ መተግበሩን ነው፡፡ስለሆነም በአገምሳ በልአ እናበቡ ኬአካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትየሚገኙ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ትምህርቱን መከታተላቸው ተረጋግጧል፡፡

ሠንጠረዥአሥራ አምስት፡- ተማሪዎች ለመማር ያላቸው ፈቃደኝነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አማራጭ መልሶች | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 15.1 | በፈቃደኝነት እጃቸውን በማውጣት መልስ የሚመልሱ ተማሪዎች አሉ; | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |
| 15.2 | በፈቃደኝነት ጥያቄ የሚመልሱ ተማሪዎች ጥቂት ናቸው; | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 15.3 | ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች አሉ; | አዎ | 3 | 6 |
| | | አይደለም | 3 | - |
| 15.4 | ተማሪዎች በቡድን ለመሳተፍ ፈቃደኝነት ይታይባቸዋል; | አዎ | 2 | 3 |
| | | አይደለም | 4 | 3 |
| 15.5 | የቤት ስራቸውን ሰርተው የመጡ ሁሉም ተማሪዎች ናቸው; | አዎ | 2 | 3 |
| | | አይደለም | 4 | 3 |
| 15.6 | የቤት ሥራቸውን ሰርተው የመጡ ተማሪዎች ጥቂቶች ናቸው | አዎ | 3 | 1 |
| | | አይደለም | 3 | 5 |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ለመግለፅ እንደተሞከረው በቋንቋ ትምህርት ወቅት በሦስቱም ትምህርት ቤቶች እጃቸውን በማውጣት በፈቃደኝነት ጥያቄዎችን የሚመልሱ ተማሪዎች መኖራቸውን ከምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይሁንና እጃቸውን በማውጣት መልሶች የሚመልሱ ተማሪዎች በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተካሄደው ምልከታ ጥቂቶች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግን በሁለት ጊዜ ድግግሞሽ በክፍል ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥያቄ ለመመለስ በፈቃደኝነት ሲሳተፉ ታይተዋል፡፡ በተጨማሪም ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ

ተግባሩን ሲፈፅሙ በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረጋቸው በምልከታው ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

በአንፃሩ የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በቡድን ያደራጁበት ጊዜ ውስን ስለነበረ ምልከታዎቹ በተከሄዱባቸው ቀናት በተሟላ ሁኔታ የተማሪዎቹን የቡድን ተሳትፎ ፈቃደኝነት ለማየት አልተቻለም፡፡ነገር ግን በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የቡድን ሥራ በነበረበት ወቅት ለማሳተፍ ያሳዩት ፈቃደኝነት ጠንካራ እንደነበረ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተማሪዎች ተነሳሽነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ አንድን ነገር ለማወቅ ለመተግበርና በነገሩ እርካታን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት እንደሚገለፁ Brown (1987፤14-16)፤ Noels (2003) ገልፀዋል፡፡ ይህም ጥያቄ በመጠየቅ፣በመመለስ የቤት ሥራዎችን በመሥራት፣በቡድን ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተነሳሽነትን ማሳየት ይቻላል Petty (2004፣50-55)፡፡ በመሆኑም የተገኙ የቃል መጠይቅ ምላሽ እንደሚያመለክተው ተማሪዎችበፈቃደኝነት ለመጠየቅ እና ለመመለስ የቃላት አጥረት ስለሚያጋጥሟቸው አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው አመልክተዋል፡፡ ይህንንም በምልከታው ወቅት በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ቃላት እያጠራቸው ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቃላትን እያቀላቀሉ ሲጠቀሙ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቁ አስተያየት መስጫ ክፍል ላይ መጠይቁ ከተፃፈበት ቋንቋ ውጪ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችና በፈቃደኝነት የመሳተፍ ተግባር በተገቢ ውሁኔታ ሊከናወን አልቻለም፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን የቤት ሥራዎችን በተደጋጋሚ ባለመስጠታቸው ምልከታው በተካሄደባቸው ቀናት ተማሪዎቹ ተግባሩን ሲፈፅሙ አልታዩም፡፡የቤት ሥራ በተሰጠባቸው ቀናትም ቢሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ደብተር በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ስላልተቆጣጠሩ የቤት ሥራቸውን ሰርተው የተገኙ ተማሪዎች ጥቂት ነበሩ፡፡

ይህንን ማረጋገጥ የተቻለው የቤት ሥራ ሳይሠሩ የመጡ ተማሪዎች አጠገባቸው ካለው ተማሪ መልሶችን ሲገለብጡ በመታየታቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታውና ከመጠይቁ ወጤቶች መገንዘብ የሚቻለው በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በፈቃደኝነት የሚመልሱና የተሰጧቸውን የቤት ሥራዎች ሰርተው

የሚመጡ ተማሪዎች በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቁጥራቸው ብዛት ያላቸው ሲሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን አነስተኛ ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቹ ትምህርት ቤቶች የተሻለ ተነሳሽነት አሳይተዋል ማለት ይቻላል፡፡

***ሠንጠረዥ አሥራ ስድስት፡-የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ብቃት በሚመለከት በክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አማራጭ መልሶች | ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት | አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 16.1 | ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ፍርሃት ይታይባቸዋል? | አዎ | 3 | 1 |
| | | አይደለም | 3 | 5 |
| 16.2 | ተማሪዎች ጥያቄ በሚመልሱበት ጊዜ ስህተት ሲፈፅሙ የመደናገጥ ስሜት ይታይባዋል? | አዎ | 1 | 1 |
| | | አይደለም | 5 | 5 |
| 16.3 | ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠየቁ የመረጋጋ ስሜት ይታይባቸዋል ? | አዎ | 2 | 4 |
| | | አይደለም | 4 | 2 |
| 164 | ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው የተሳሳተ መልስ ሲሰነዘር ይስቃሉ? | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |
| 16.5 | በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎች ከከፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሳይፈሩ ሲወያዩ ታየቷል? | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |

ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው፡-በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ሲመልሱ ሦስት የክፍል ምልከታ ጊዜ ያለፍርሃት የታየባቸውን ተማሪዎች ማየት ሲቻል በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ግን አንድ ጊዜ በክፍል ምልካታ ወቅት ብቻ የሚፈሩ ተማሪዎች ማየት ተችሏል፡፡

በአንፃሩም ጥያቄ ሲጠየቁ የመረጋጋት ስሜት የሚታይባቸው የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥቂት ሲሆኑ የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በነበራቸው የቡድን ሥራ ወቅት ሳይፈሩ እርስ በርሳቸው ሲወያዩ ታይቷል፡፡ በአንጻሩ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ የመሳቅ ተግባር ከቂልጡ ካራ ትምህርት ቤት ይልቅ በአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፈጸሙን በምልከታው ሂደት ተስተውሏል፡፡ከላይ በሠንጠረዥ 17 ላይ እንደታየው በፊቃደኝነት የማሳተፍ ተግባርን አብዛኛዎች በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ስላልተገበሩት የተሳሳተ መልስ ሰጥተው ሲደናገጡ ከአንድ ጊዜ በላይ አልታየም፡፡ ይህንን ሐሳብ ከተማሪዎች መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ 60 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ጥያቄ ለመጠየቅ የማይፈሩ መሆናቸውን ሲያመለክቱ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ 43 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች እንደማይፈሩ አመልክተዋል፡፡በ ክፍል ተሳትፎ ወቅት በራስ መተማመን የሚታይባቸው መሆናቸውን የገለፁት ደግሞ ከአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 72 ፐርሰንት የሚሆኑት ሲሆን ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ 57.3 ፐርሰንት የሚሆኑ ናቸው፡፡

በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ቋንቋውን ሲነገሩ እንደማይጨነቁ 70 ፐርሰንት የሚሆኑት የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲገልፁ ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 57.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ቋንቋውን ያለጭንቀት መናገርና በክፍል ውስጥ መሳተፍ እነደሚችሉ ገልፀዋል፡፡ ይሁንና ከትምህርት በኃላ እርካታ እንደሚያገኙ አዎንታዊ ምላሻቸውን በመስጠት የገለፁት ከአገምሰ በልአ እና ከቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች 66.6 ፐርሰንት ሲሆኑ ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግም 41 ፐርሰንት የሚሆኑ ናቸው፡፡

Hedge(2000) እንደገለፁት ተማሪዎች "እሳሳት ይሁን ፣ይሳቅብኝ ይሁን" የሚል የጥርጣሬ መንፈስ በውስጣቸው ይዘው የሚማሩ ከሆነ በራስ የመተማመን ብቃታቸው እየቀነሰ የመጨነቅና እርካታን የማጣት ስሜት ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት እያደከመ ይሄዳል፡፡በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን በቃለ መጠየቁ ላይ ስለ ተማሪዎቻቸው በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለመናገር ድፍረትና በራስ መተማመን ስለሚያጡ ጥያቄ ከመጠየቅና ከመመለስ ይቆጠባሉ፡፡ ስለሆነም እናስጨንቃቸዋለን በሚል ስሜት ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ እንደማያስገድዷቸው ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል፡፡

## 4.4 በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ተለውጦች በሚመለከት የቀረበ ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በተለያዩ ምሁራን በተገለጸው ሀሳብ ለማብራራት እንደተሞከረው የተማሪዎች ተነሳሶት ከፍ ወይም ዝቅ እንዲል ከሚያደርጉት ተለውጦች መካከል በቢጤዎች፣ወላጆችና የአከባቢው ማህበረሰብ ይገኙበታል፡፡ እነዚህም የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎችን ለማነቃቃት አጋዥ ወይም እንቅፋት ሊሆኑበት ይችላሉ፡፡በመሆኑም ይህንን ተግባር በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ቀጥሎ ለማየት ይሞከራል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፡- ቢጤዎች ወላጆችና ማህበረሰቡ ያላቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት ከፅሁፍ መጠይቁ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | መልስ ያልሰጡ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 17.1 | የክፍል ጓደኞቼ ጥያቄ እንዲመልስ ያበረታቱኛል | 37 | 28.4 | 47 | 36.1 | 17 | 13 | 22 | 16.9 | 6 | 4.6 | 1 | 0.7 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17.2 | የክፍል ጓደኞቼ በቋንቋ ትምህርት ወቅት በሚፈጠረው ስህተት አይስቁብኝም | 24 | 18.4 | 50 | 38.4 | 16 | 12.3 | 23 | 17.6 | 17 | 13 | - | - |
| 17.3 | ወላጆች ስለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | 25 | 19.2 | 38 | 29.2 | 29 | 22.3 | 14 | 10.7 | 17 | 13 | 7 | 5.3 |
| 17.4 | ወላጆች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ እንዳጠና ያበረታቱኛል | 26 | 20 | 48 | 36.9 | 22 | 16.9 | 19 | 14.6 | 15 | 11.5 | - | - |
| 17.5 | በአካባቢዬ ያሉ ሰዎች ስለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | 19 | 14.6 | 42 | 32.3 | 23 | 17.6 | 18 | 13.8 | 18 | 13.8 | 10 | 7.6 |

ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ተነሳሶትን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ተለውጦች አሉ፡፡ተለውጦቹ በተስተምሮት ወቅት ወይም ከተስተምሮቱ ውጭ ሊሆን ይችላሉ (Pintrich and Schunks (2002) :: ስለዚህ ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የክፍል ጓደኞቻቸው ግፊት ተጽእኖ እንደማያደርስባቸው 64.61 ፐርሰንት የሚሆኑ የቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና በኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በሶስቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡት 35.38 ፐርሰንት ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ተሳትፎኣቸው ስህተት ቢፈጥረሩም ጓደኞቻችወ እንደማይስቁባቸው ከቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ 56.92 ፐርሰንት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 43.07 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው ከቂልጡ ካራ ትምህርት ቤትም ሆነ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ እንደሚደርስባቸውና በአንፃሩ የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኘው ተማሪዎች ይልቅ የአገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ የሚገኙ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲሰሙ እንደሚስቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች ወላጆቻቸው ለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አለለካከት እንዳላቸው 48.46

ፐርሰንት የሚሆኑ የቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 51.53 ፐርሰንት ደግሞ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ውስጥ በአገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት እንደተቸገሩ ከምላሻቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁንና 56.92 ፐርሰንት ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ትምህርት ቤት 56.6 ፐርሰንት ከአገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆቻቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን እንዲያጠኑ እንደሚገፏፏቸው በምላሻቸው አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ወላጆች በቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አዎንታዊ ተጽእኖ 50 ፐርሰንት ያልሞላ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ለቋንቋ ያላቸው አመለካከት 46.92 ፐርሰንት የሚሆኑ ከቂልጡ ካራ፣ አገምሳ በልአና ቡኬ አካቼ ተማሪዎች ጥሩ እንደሆነ ሲያመላክቱ ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች 53.07 ፐርሰንት አሉታዊና ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

### 4.5 ከጽሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ አስተያየቶች

ለተማሪዎች የቀረበ የፅሑፍ መጠይቅና ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ከነዚህ አስተያየቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን ፍላጎት ለምን እንደሚማሩት በማስመልከት ተጠይቀው ሲመልሱ የሚከተሉትን ሀሳቦች ዘርዝረዋል፡፡

- ❖ ቋንቋው የመግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ ወደፊት ከሰዎች ጋር የመግባባት ችግር እንዳያጋጥመኝ እማራለሁ፣
- ❖ በአማርኛ ትምህርት ውስጥ የሚገኙትን ዘይቤዎችና ቅኔዎች ማወቅ ስለምንፈልግና የቋንቋውን ስዋሰው አጠቃቀም መገንዘብ ስለሚፈልግ እማራለሁ፣
- ❖ ከሚሰጡት ትምህርቶች አንዱ በመሆኑ የሚሉ አዎንታዊ ምላሾች የአገምሳ በልአ እና ከቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲገልፁ፡-

ከቂልጡ ካራ ት/ትቤት ደግሞ

- ❖ ቋንቋውን የምንማረው የመማር ግዴታ ስላለብኝ፡-ፈተና ለማለፍ እማራለሁ፣
- ❖ ቋንቋውን ለመልመድ ስለምፈልግ፣የሥራ ቋንቋ ስለሆነ፡-የሚሉት ምላሾች ተገኝተዋል፡፡

ከዚህ ምላሽ ለመረዳት የሚቻለው የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከውስጣዊ ተነሳሶት ይልቅ በውጫዊ ግፊት ለማለፍ ሲሉ እንደሚማሩ ሲሆን የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ በቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ሥርዓትንና  የቋንቋ አጠቃቀምን ለማወቅ ተግባቦትን ለማሳደግ ሲሉ በፍላጎት እንደሚማሩ ነው፡፡ተጠኚ መምህራኑም ምን ዓይነት የመማሪያ ስልትን ተጠቅመው ተማሪዎችን ለማነሳሳት ጥረት እንደሚያደርጉ ተጠይቀው ሲገልፁ፡-

- በአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን በቡድንና በጥንድ በማሳተፍ ተማሪዎች እንዲወያዩ በማድረግ፡-
- ለሌሎች አጋዥ መጽሐፍትን በሚጠቅስ አዝናኝ በሆነ መንገድ እንደሚያስተምሩ ሲገልፁ
- የቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ደግሞ፡-
- የክፍል ፀጥታ እንዳይጓደል እና ተማሪዎቹ ብዛት ስላላቸውና፡-በአብዛኛው በግል አልፎ አልፎ በጥንድ ተማሪዎችን በማሳተፍ ቋንቋውን እንዲማሩ ማድረግ፡-
- በሚገባቸው መልክ ምሳሌዎችን በመጥቀስ እያበረታቱ እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል፡፡

ተማሪዎች የመምህሮቻቸውን የማስተማሪያ ስልቶችእ ንደሚስማማቸው ተጠይቀው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

- የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች
- ለተማሪዎች ጥሩ አመለካከት ስላላቸው፣
- በቀላል ቋንቋ በምሳሌና በቀልድ እያዋዙ ስለሚያስተምሩ፣
- በቡድን በማደረጀት ድራማስ ለሚያሰሩና ስለሚያወያዩ፣
- በፈገግታ ሳይቆጡ ጥያቄዎችን ስለሚመልሱ የማስተማሪያ ስልታቸው ደስ ይለናል ሲሉ ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ፡-
- በትህትና ትምህርቱን ስለሚያስረዱኝ፣
- ማስታወሻ ስለሚሰጡ፣
- የክፌሉን ጸጥታ ስለሚያከብሩ የማስተማር ስልታቸው ይስማማናል የሚሉ አዎንታዊ ምላሾች ተገኝተዋል፡፡

የመምህራን የማስተማር ስልት እንደማይስማማቸው የገለፁት የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ የሚከተለውን ብለዋል፡-

- ፊትለፊት ወጥተን እንዲንናገር ስለሚያስገድዱን፣
- የቤት ሥራ ስለሚሰጡን የማስተማር ስልታቸው አይስማማንም ሲሉ ፤ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ፡-
- የማያዝናኑ ቀልዶችን ስለማይጠቀሙ፣
- የክፍል ሥራ የሚሰጡት ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ በመሆኑ እና የሰራነውን ስለማያርሙልን፡-
- ከፊት የሚቀመጡትን ብቻ ስለሚያሳትፏቸው የማስተማር ስልታቸው አይስማማንም የሚሉ አሉታዊ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡

ከተማሪዎች የተገኙ አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት በአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ የሚገኙ መምህራን ትምህርቱን በተሻለ ሁኔታ አዝናኝና አስደሳች ለማድረግ የተማሪዎችን ተነሳሽነትን ከፍ ለማድረግ ጥረት የሚያደርጉ ሲሆን በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ይህንን ተግባር ከመፈፀም ይልቅ በክፈሉ ፀጥታ መጠበቅ እና በገለፃ ላይ እንደሚያተኩሩ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዓላማ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ለየትኞቹ የማነሳሻ ስልቶች እንደሚጠቀሙበትና እንዴት እንደሚተገብሯቸው ማጥናት ነው፡፡

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የማነሳሻ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በርካታ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው አዳዲስ ዕውቀቶችን እንዲያኙና በተግባር እንዲተረጉሟቸው የማሳሻ ስልቶችን ተጠቅሞ የቋንቋ መምህሩ ማስተማር እንደሚገባቸው Brown (1987) ገልፀዋል፡፡ በተመሳሰይ መልኩ Dornyel (2001) የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች በተስተምህሮቱ ወቅት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹና አጋዥ የክፍል ሁኔታዎችን በመፍጠር ወደ ታላሚው ግብ እንዲደርሱ ማበረታታት እንደሚጠቀምባቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራን የማነሳሻ ስልቶቹን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማቸዋል ፡፡ከእነዚህ መካካል የተማሪዎች ዳራ፤ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና አደረጃጀት የቋንቋ መምህሩ የራሱ ዳራና የማስተማር ፍላጎቱ ጥቂቶች ናቸው፡፡በዚህ መሠረት በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትኞቹ ተማሪዎቻቸውን ለትምህርቱ የተነሳሱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ በገለፃ ለማየት ተሞክሯል፡፡

በዚህ መሠረት በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካይነት ከመምህራኑና ከተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተንትነው የተደረሰበት ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመማር- ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮች መኖራቸውን ከመረጃ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል፡፡በዚህም መሠረት በቂልጡ ካራ

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከአገምሳ በልአ እና ከቡኬ አካቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ ተማሪዎች ዝቅ ያለ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች ያላቸውን ተነሳሶት ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች አማካይነት መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

- መምህራን መልካም የሆነ የመምህር- ተማሪ ግንኙነት በክፍል ውስጥ መፍጠር አለመቻላቸው፣
- እንደ ቡድንና ጥንድ እያደራጁ በማሳተፍ በተስተምህሮቱ አጋዥ ሁኔታን አለማመቻቸታቸው፣
- አሉታዊ ምጋቤ- ምላሽ መጠቀማቸው፣
- መምህራኑ በአብዛኛው መምህር-መር የማስተማር ዘዴን መርጠው መጠቀማቻውና ተማሪ- ተኮር ዘዴን አለመጠቀማቸው፡፡

አዝናኝና አስደሳች የክፍል ሁኔታ ለመፍጠር አለመጣራቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቹ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሳሶት የተሻለ በመሆኑ ያላቸው ተፅዕኖ ውስን እንደሆነ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል መምህራን የተነሳሶት ስልት አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ካስከተሉት አንዱ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ነው፡፡ በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች ንፅሕናቸው ያልተጠበቁ፣ መቀመጫዎቹ ያልተሟሉና በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እስከ ሰባ ስድስት የሚደርሱ ተማሪዎች የሚገኙ በመሆናቸው ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እና በክፍል ውስጥ ተንቀሳቅሶ የተማሪዎችን ሥራ ለመከታተል አለመቻላቸው የመሳሰሉት በመምህራን የማነሳሻ ስልት አተገባበር ተፅዕኖ ማሳደራቸው ተረጋግጧል፡፡

በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቹ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ንፅሕናቸው የተጠበቀና በአንድ ክፍል ውስጥ

የሚማሩ የተማሪዎች ብዛት ተመሳሳይ ቢሆንም በመጠኑ ከተፅዕኖ ነፃ መሆናቸው በክፍል ምልከታውና ከመጠይቁ ውጤቶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው በጥናቱ ለማረጋገጥ የተሞከረው ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በአገምሳ በልአና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትኞቹ ተማሪዎቻቸውን በተሻለ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርቱ ለማነቃቃትና ለማነሳሳት ይሞክራሉ የሚለው ነው፡፡በመሆኑም ከክፍል ምልከታውና ከመጠይቆቹ ምላሽ ማረጋገጥ እንደተቻለው የማነሳሻ ስልቶችን በተሻለ ሁኔታ የሚተገብሩት የአገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይልቅ በማነሳሻ ስልታቸው የተሻሉ ሊሆኑ የቻሉት፡፡

- ❖ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው ትህትናን ፤ፈገግታንና ፈቃደኛነትን በማሳየት ስማቸውን እየጠሩ በማሳተፍ መልካም የሆነ የመምህር- ተማሪ ግንኙነት በመፍጠራቸው፤
- ❖ አዝናኝ ቀልዶችን በትምህርቱ ጣልቃ በማስገባትና የትምህርቱን ይዘት ከተማሪዎቻቸው ልምድ ጋር አዛምደው በማቅረባቸው፤
- ❖ ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት የውይይትና የመተጋገዝ መንፈስን በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ በመፍጠር ተማሪ-ተኮር ዘዴን መከተላቸው፤
- ❖ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታታት አዎንታዊ ምጋቤ ምላሾችን ከመስጠታቸው የተማሪዎችን ተነሳሶት ለመቀስቀስም ሆነ ያላቸው ተነሳሶት ከፍ ለማድረግ የተሻሉ መሆናቸው ከመረጃዎቹ ውጤቶች ለማረጋገጥ ተችላል፡፡

በአንጻሩም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት የማነሳሻ ስልቶች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ሲቸገሩ ታይቷል፡፡ በመሆኑም መምህራኑ በክፍል ውስጥ የቁጡነት ባህሪ በማሳየታቸው የክፍሉ ፀጥታ እንዳይታወክ በሚል ስጋት በትምህርቱ ጣልቃ ቀልዶችን የመጠቀም ብልሃታቸው ዝቅተኛ መሆኑንና ፣ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ አደራጅቶ ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ከማድረግ ይልቅ ለገለፃና ለግላዊ ተሳትፎ የላቀ ድርሻ በመስጠታቸው ከአዎንታዊ ምጋቤ-ምላሽ ጎን

ለጎን አሉታዊ ምጋቤ-ምላሾችን መቀበላቸው፣ የቤት ሥራ ባለመስጠታቸውም ተማሪዎች የማነቃቂያ ተግባራቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፤አገምሳ በልአ እና ቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ መልኩ የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ አለማበረታታት ፤የሽልማት ምጋቤ-ምላሾችን አለመስጠት፣ በመቅረፀ ድምፅ አማካይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አለመጠቀማቸው ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የተረጋገጠው የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚመለከት ነው፡፡የመጠይቆቹና የምልከታው ውጤቶች እንደሚያመለክቱት የተማሪዎች ተነሳሶት በተስተምህሮቱ ወቅት በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተና በሚያደርጉት ጥረት የሚገለጥ ነው፡፡በዚህ መሠረት በአገምሳ በልአና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በፈቃደኝነት ሲሳተፉ ታይተዋል፡፡ምንም እንኳን በሦስቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት እንዳላቸው በመጠይቁ ምላሽ የገለፁ ቢሆንም ከምልከታውና ከመምህራኑ መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፈቃደኝነት የሚሳተፍ፣ ማስታወሻ የሚይዙ፣ትምህርቱንያለ ሹክሹክታ በፀጥታ የሚከታተሉ የጓደኞቻቸው መልስ በጥንቃቄ የሚያዳምጡ ጥቂቶች መሆናቸው ሊታወቅ ችሏል፡፡

ከቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኙ የመጠይቅ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ፈቃደኝነት ላለማሳየታቸው እንደ ምክንያት የተወሰደው፤ ተማሪዎቹ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና በክፍል ተሳትፎ ወቅት የቃላት እጥረት ስለሚያጋጥማቸው ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ተረጋግቶ ጥያቄ ያለመጠየቅ፣ በክፍል ተሳትፎ ወቅት ስህተት ሲፈጠሩ መደናገጥ ፣በራስ ያለመተማመን ችግር እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊ ምጋቤ- ምላሾችን በመጠቀማቸው የተማሪዎቹ ተነሳሶት ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአንፃሩም በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ተሳትፎ ወቅት ፈቃደኝነት ያላቸው፤ መረጋጋት የሚታይባቸው፤ በራስ መተማመን

ያላቸው መሆናቸው ከመጠይቆቹና ከምልከታው ውጤት ማረጋገጥ ታችሏል፡፡በዚህ መሠረት የተሻለ ተነሳሶት እንዳላቸው ታረጋግጧል፡፡ በሌላው በኩል በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በጓደኞቻቸው የሚቀበሉትን ማበረታቻ፣ወላጆቻቸውና ማህበረሰቡ ለቋንቋ ያላቸው አመለካከት ለትምህርቱ የሚያደርጉላቸው እገዛ አነስተኛ መሆን ተመሳሳይ እንደሚታይበት የተገኘ ውጤት ያሳያል፡፡

በመሆኑም መምህራን በክፍል ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩትን ስልቶች የተሻለ ሁኔታ በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መተግበራቸው በዚህ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሃሳብ

የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶችን በመፍትሔነት አቀርቧል፡፡

- በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ስፋት ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝ አለመሆን መምህሩ የእያንዳንዱን ፍላጎትና ተነሳሶት ተከታትሎ ለማነቃቃትና ከፍ ለማድረግ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር በመሆኑ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ስፋት ጋር የተመጣጠነ ቢሆን ፤በሦስቱም ትምህርት ቤቶች በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ብዛት የሚቀንስበት ሁኔታ የተመቻቸ ቢሆን፣
- በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቂ የሆኑ መቀመጫዎች መኖርና የክፍሉ ንፅሕና መጠበቅ ተማሪዎችን ለማነቃቃት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ፤ስለዚህ የመማሪያ ክፍሉ ምቹ እንዲሆን ትምህርት ቤቱ መቀመጫዎችን ቢያሟላና ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍላቸውን ንጽህና እንዲጠብቁ መምህራን ቁጥጥር ቢያደርጉ፣
- መምህራን በተሻለ ሁኔታ በክፍ ልወስጥ የተነሳሶት ስልቶችን እንዲተገብሩ ለማድረግ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ አጫጭር ሥልጠናዎች ለመምህራን ቢሰጡ፣
- በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣በአገምሳ በልአ እና በቡኬ አካቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን መካከል የልምድ ልውውጥ ቢደረግ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ወስጥ አስፈላጊ የትምህርት መርጃመሳሪያዎችን በመጠቀም የትምህርቱን ይዘት አዝናኝና አስደሳች በማድረግ በቡድንና በግል

በማደራጀት ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታታትና ተገቢውን ምጋቤ-ምላሽ በመስጠት ተማሪዎቹ ተነሳሶት እንዲኖራቸውና በቋንቋ ትምህርቱ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ቢጥሩ፣

በተለይም በቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን እነዚህ የማነሳሻ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ቢጥሩ፣

የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለማነቃቃትና የማነሳሻ ስልቶችን ለመተግበር በቅድሚያ ቋንቋውን ለማስተማር ሙሉ ፍላጎትና ተነሳሶት ያላቸው ሊሆን ይገባል፡፡ለሚያሳዩትም ተነሳሶት ትምህርት ቤቱ የማበረታቻ ምስክር ወረቀቶችን ፣ሽልማቶችን አንዳንድጥቅማጥቅሞችን ለመምህራኑ ቢያበረክቱ መልካም ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ሰለሞን ተሰማ (1995) ፡፡ ሁለተኛ ቋነቋ በመማር ማስተማር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች መፍትሂዎቻቸዉ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማሪያ የተዘጋጁትን መረሓ ትምህርቶች ለመሻሻል ለተከሄደዉ አዉደ ጥናት ማነሻ የቀረበ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (የልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)፡፡ ስነ-ልሳን ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ (ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (1986)፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፖልስ አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፤ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

ያለው እንዳወቅ ሙሉ (1998.4)፡፡ የምርምር መስረታዊ መሪዎችንና አተገባባር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

Alaties,j (1981). The second language class room. Directions for the 1980's Cambridge: Cambridge University press.

Alisone,j (1993). Not brother motivating reluctant language learners in key stage 4. London center for information on language teaching and Research (SILT).

Bayush Tibebu, (2007). "A study of the motivation techniques employed by EFL teachers: In the case of two school two primary school in bure wereda West Gojjam"(Unpublished M.A Thesis) Addis Ababa University.

Benson, (2000). Teaching and researching autonomy in language learning. London; Longman.

Bill,H (2001). Educational Psychology interactive. New York; Oxford University Press.

Brophy, J.E (1998). Motivating students to learn. Boston;mc Grow Hiw

Brown,H.D (1987). Principle of language learning and teaching. (2nd Ed.) New Jersey:Premiero

Chamber,G.N (1999). Motivation Language learners, Cleve;Multi

Covingtion,M. (1999), Caring about learning . The nature and Nituring of subject-matter Appreciation "educational psychologist.V34, PP 127-36

Cunning Worth,A (1984). Evaluating and Selecting EFL Teaching materials. Oxford: A division of Hein emann Educational books ltd.

Deci (1971). Effect of externally mediated rewards on intrinsic motivation journal Of personality and social psychology.

Dorneyei,(1998). "Motivation in second and foreign Language learning "language learnig. V31 PP-117-135.

Dorneyei,(2001). Teaching and researching motivation. London Education Limited.

Elliot, j.G.etal. (2005). Motivation engagement and Educational Performance. International Perspectives on the contexts for learning, New York; York; pellagra,

Ellis, R. (1994).The study of second language Acquisition. Oxfords University

press.

Gardner,R.C. (1985) social Psychology and second language learning Attitudes and The role of Attiude and motivation London Aronold,

Gardn,R.C. and macin trye ,P.(1993). Special feature on Affective Variables in second language learning The international Abstractin Journal for Laanguages Teachers and Applied Linguists London Ontrio University

Gardn,R.C and Lambert,W.E. (1972). Attitude and Motivation in second Language Learning. Rowley mass New Burn House Publisher.

Harmer (1991).The Practice of English Language Teaching .

London Longman (2001) The Practice of English Language Teaching Edinburgh Gate Person in Education

Ltd. Student haris (1991) “some ideas for Motivating students “TESL Journal vol. my No.2November 2002.HttP://WWWvirtual selt com.

Haywood,H.C. (1971). “Individual Difference in Motivational orientation :Atrait Approach “in Day.H.I Berlin D.E.Intrinsic Motivation A new Direction in Education. Toronto Holt Rinhart and Wiston of Canda.PP 75-85.

Hedge,T. (2000). Teaching and Learning in language class room. Oxford: oxford University press.

Hutchinson,T. (1988). ”Making materials work in Especial class room. Brumfit(ed) Especial in class room . Practiced and Evaluation ELT

Document: P128

Janet, (1997)." Motivating learners at South Korea ''English Teaching forum, Vol.35 No, 1:10

Keller,J.M.(1983)," Motivational design of instruction. ''C.M Re,gertuth (ed)structionalDesign of theories and models: an overview of their current status .Hills doe,Nj LawrenceErlbaum, PP383-434.

Kost,S. (2006). " Motivation and Foreign language Teaching strategies for Motivation. ''http;//itesu org.Artichs/suslu Teacher Motivational Htmi.

LittleWood,W. (1981). Communicative language teaching. Cambridge: Cambbridge university press.

Mulugeta Teka. (1997). motivation in listening classes of college English at Addis Ababa University ,''(un Pulished MA.Thesis ). Addis Ababa University .

Naunan,D. (1989). Designing Tasks for the communicative class room. Cambridge; Cambridge University press.

Oxford,R.L and yong,D.J. (1993). Language learning strategies what every Teacher should Know .Cambridge; Cambridge University press.

Parrott (1993). Tasks for language Teachers: Resource Book for Training and Development.Cambridge: Cambridge University press.

Peety,G.M. (2004).Teaching Today. (3 ed.) London: Nelsan themas Ltd printrich

.and pintrich.

Pintrich,R. and schunk.H.(2002). motivation inEducation Theory.Research and Applications New York;mirill prentice Hall.

Raymond,W. (1986). Enhancing Aduit motivation to learn in Dornyei. (2001) . Motivational Strategies in the language class room Cambridge: Cambridge University press.

Rodgers,C.(1991).On becoming . a person .Boston ;Houghton Miffin .

Rosenshine,B and stevens, R.(1986) "Teaching Functions"inM.C.wittrock. (Eg) Hand book of Research on Teaching (3rd ed) pp376-39) New York; Macmillan.

Rosser,R.A and Nicholson, G.C. (1984). Educational Psychology principles in Practice. Boston: Little Brown Company.

Scheldeker,D.F William (1999). The Best Bringing out in students. How cegendry Teachers motivate kids Thousand.CA: crowing press.

Seblewangl yonas (2007). An Assessment of Teachers" Motivational strategies in ELT classroom .Tow Government universities &Two colleges in Oromia Region in focus. Unpublished M.A. Thesis in teaching English as foreign language: Addis Ababa Universty

Stern,H.H (1983). Fundamental concepts of language teaching .Oxford: Oxford University Press.

Ur.P. (1996). course in language teaching. Cambridge, Cambridge University.

Ushioda,E. (1997). '' The role of motivational Thinking in Autonongus language Learnig. In D.Little and BL voss (Eds) language centers Planning for the New millennium .Plymouth:

Vanlier,E. (1988).The classroom and the language learner. Landon: Longman Group UK Limited.

William, M. and, Burden,B. (1997). Psychology for language Teachers. Asocial Constructivist Approach. Cambridge: Cambridge university press.

Wittrack,M.C. ( 1986). '' Studentsmthaught processor in M CW itt rack (Ed) Hand book of Research on teaching (3rded) PP.297.314) New York.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ሶሻል ሳይንስና ሕዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዩጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ መቆጣጠሪያ ቅፅ (Check list)

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የማነሳሻ ስልት አተገባበር በክፍል ምልከታው ለመከታተል የተዘጋጀ መረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ (Check list)

የክፍል ምልከታው ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ተማሪዎችን ለማነሳሳት ተግበራዊ የሚያደርጓቸውን ስልቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተገኝቶ መመልከትና መረጃ መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1. የትምህርት ቤት ስም-------------------------------------

2. የክፍል ምልከታው የተደረገበት ክፍል እና ምድብ /Section/

    ክፍል ጊዜ--------------------------------------
    ቀን---------------------------------------------
    ሰዓት-------------------------------------------

የመምህሩ መለያ ኮድ

*መመሪያ፡-* ከዚህ በታች አራት የክፍል መመልከታ«ሊስት» ቀርበዋል፡፡ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተስማሚ ነው የሚትሉት አማራጭ መልሶች የ"   " ምልክት በማድረግ ያመልክቱ፡፡

## ክፍል ሁለት

| ተ.ቁ | የመማሪያ ክፍል ሁኔታ እና አደረጃጀት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍሉ ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በቂ ስፋት አለው? | | |
| 2 | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙት መቀመጫዎች ለተማሪዎች በቂ ናቸው? | | |
| 3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅሕና የተጠበቀ ነው? | | |
| 4 | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ንፅሕ አየር በመስኮት ይገባል? | | |
| 5 | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ሰሌዳው ለሁሉም ተማሪዎች በሚታይበት ቦታ ላይ ተቀምጧል? | | |

## ክፍል ሶስት

የመምህር ተማሪ ግንኙነት የሚመለከት

| ተ.ቁ | የመምህር ተማሪ ግንኙነት የሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ በሰዓት ወደ መማሪያ ክፍሉ ገብተዋል ? | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ የደንብ ልብሳቸውን ለብሰዋል? | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ትህትና ያሳያሉ? | | |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ያሳያሉ? | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ የቁጡነት ባህሪ ይታይባቸዋል? | | |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩበመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን ይከታተላሉ? | | |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ በትምህርቱ ጣልቃ አዝናኝ ቀልዶችን ያቀርባሉ ? | | |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቻቸውን ጥያቄዎችን ሲጠይቋቸው ለመመለስ ፍቃደኛ ናቸው? | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ የማበረታቻ ቃላትን ይጠቀማሉ? | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቻቸው ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ የምስጋና ቃላት ይጠቀማሉ ? | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ? የተሳሳተ መልስ ተማሪዎቹ ስመልሱ የነቀፌታ ቃላትን ይጠቀማሉ ? | | |
| 12 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ጥያቄ ጠይቀው ከተማሪዎቻቸው መልስ ሲያጡ የነቀፌታ ቃላትን ይጠቀማሉ ? | | |

## ክፍል አራት

| ተ.ቁ | የመምህሩ የተነሳሶት ስልት አተገባበር የሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች በቡድን እንዲደራጁ አደርጓል ; | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎችን በጥንድ እንዲደራጅ አደርጓል; | | |
| 3 | በቡድን ሥራ ወቅት የቡድን መር ነበር; | | |
| 4 | በቡድን ሥራ ውስጥ በአብዘኛው የሚሳተፉ ተማሪዎች ጥቅቶች ብቻ ነበሩ; | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ የውይይት መንፈስ እንዲኖር አደርጓል; | | |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ እንዲኖር አደርጓል; | | |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ከመማሪያ መጽሐፍ ሌላ የማስተማሪያ መረጃ መሳሪያ ተጠቅመዋል; | | |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ መቅረፀ ድምፅ ተጠቅመው አስተምሯል; | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ሌሎች ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ በመረጃነት ተጠቅሟል; | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ አደርጓል; | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲሳተፉ እድል ሰጥቷል; | | |
| 12 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ የክፍሉን ስነሥርዓት እንደ አስፈላጊነቱ ተቆጣጥሯል; | | |
| 13 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ መምህር መር ስልትን ተጠቅመው አስተምረዋል; | | |
| 14 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪ ተኮር ዘዴ ተጠቅመው አስተምሯል; | | |

## ክፍል አምስት

| ተ.ቁ | የተማሪዎችን ተነሳሽነት  በሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ በሰዓት ተገኝተዋል; | | |
| 2 | ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ሲያስተምሩ በፀጥታ ያዳምጣሉ; | | |
| 3 | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ወቅት እርስ በርስ በሹክሹክታ ይነጋገራሉ; | | |
| 4 | ተማሪዎች መምህራቸው ሲያስተምሩ የግል ሥራቸውን የሚሰሩ አሉ; | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ሲያስተምሩ ማስታወሻ የሚይዙ ብዙ ተማሪዎች አሉ; | | |
| 6 | በፍቃደኝነት እጃቸውን በማውጣት መልስ የሚመልሱ ተማሪዎች አሉ; | | |
| 7 | በፍቃደኝነት የሚመልሱ ተማሪዎች ጥቅቶች ናቸው; | | |
| 8 | ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች አሉ; | | |
| 9 | ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ፍርሃት ይታይባቸዋል; | | |
| 10 | ተማሪዎች ጥያቄዎችን በሚመልሱበት ወቅት ስህተት ሲፈፅሙ የመደናገጥ ስሜት ይታይባቸዋል; | | |
| 11 | ጥያቄ ሲጠይቁ የመረጋጋት ስሜት የሚታይባቸው አሉ; | | |
| 12 | ተማሪዎች በቡድን ለመሳተፍ ፍቃደኝነት ይታይባቸዋል; | | |
| 13 | የክፍል ጓደኞቻቸው መልስ ሲመልሱ በጥንቃቄ ይከታተላሉ; | | |
| 14 | የክፍል ጓደኞቻቸው የተሳሳተ መልስ ሲሰነዘሩ ይስቃሉ; | | |
| 15 | በቡድን ሥራ ወቅት ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሳይፈሩ ሲወያዩ ታይተዋል; | | |
| 16 | የቤት ሥራቸውን ሰርተው የመጡት ሁሉም ተማሪዎች ናቸው; | | |
| 17 | የቤት ሥራቸውን ሰርተው የመጡ ጥቂት ተማሪዎች ናቸው; | | |

# ክፍል ስድስት

**አስተያየትና ሀሳብ መስጠት**

1. በመቆጣጠሪያ ቅፁ ላይ ያልሰፈሩ፣ ነገር ግን በክፍል ውስጥ የተመለከቷቸው ወይም ያዳመጧቸው ነገሮች ካሉ በጹሑፍ ያስፍሩ

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

2. በመቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ ሰፍረው አዎ ወይም አይደለም ለማለት አሻሚ የሚሆኑ ሀሳቦች ካሉ በጹሑፍ ያስፈሩ

3. ስለ ክፍል ምልከታው አጠቃላይ የሆነ የግል አስተያየቶችዎን በጽሑፍ ያስፈሩ

## አባሪ ለ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሕዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጹሑፍ አማርኛ ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የፁሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ አላማ

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የማነሳሻ /የማነቃቂያ/ ስልት አተገባበር ለማወቅ መረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡ በመሆኑም፡- ውድ ተማሪ ይህንን የጽሑፍ መጠይቅ ስትሞላ/ይ/ ትክክለኛውና እውነተኛ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር ለእያንዳንዱ ጥያቄ በተሰጠው ሳጥን ላይ መልስህን /መልስሽህን/ በማክበብ እንዲታመልክት /እንዲታመልክቺ/ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ተማሪ ለምታደርግልኝ /ለምታደርጊልኝ/ ቀና ትብብር ከወዲሁ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- በፅሑፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም፡፡

**ክፍል አንድ**፡- ግላዊ መረጃ

ሀ. ፆታ---------------------------------

ለ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ---------------------------

ሐ. ዕድሜ-----------------------------------------

መ. የትምህርት ቤትህ/ሽ/ ስም-------------------

**ክፍል ሁለት**፡- የተማሪዎች የግል ስሜት ለመረዳት የቀረበ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | እስማ ማለሁ | መወሰን ያስቸግረ ኛል | አልስ ማማም | ምንም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱፍላጎት አለኝ; | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ይቀለኛል | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ሲያስተምሩ ይገበኛል | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ጥያቄ ለመጠየቅ አልፈራም. | | | | | |
| 5 | በራስ መተማመን አለኝ | | | | | |
| 6 | አማርኛ ቋንቋን ለመናገር አልጨነቅም | | | | | |
| 7 | ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኃላ እርካታን አገኛለሁ. | | | | | |

**ክፍል ሦስት፡-** የመምህራን የክፍል ውስጥ ተግባራት እና የመማሪያ መፃሕፍት በሚመለከት የቀረበ የፅሑፍ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም እስማማ ለሁ | እስማ ማለሁ | መወሰን ያስቸግ ረኛል | አልስ ማማም | ምንም አልስማ ማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በቡድን ሥራ እንዲንሳተፍ ያደርጉኛል | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የጥንድ ሥራ እንዲሳተፍያደርጉኛል | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በግል እንዲሳተፍ ያደርጉኛል | | | | | |
| 4 | የቡድን አባሎቼ የቡድን መሪ ያደርጉኛል | | | | | |
| 5 | የቡድን አባሎቼ የቡድን ፀሐፍ ያደርጉኛል | | | | | |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ አዝናኝ ቀልዶችን በመጠቀም ትምህርቱን አስደሳች ያደርጉልኛል | | | | | |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በስሜ ጠርተው መልስ እንዲመልስ ያደርጉኛል | | | | | |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በፈገግታ ጥያቄዎችን ይመልሱልኛል | | | | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እያንዳንዱ የትምህርት ክንውን ዓላማ ያሳውቀኛል | | | | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንዴ አስፈላጊነቱ መቅረፀ ድምፅ /ቴፕ/ ተጠቅመው ያስተምራሉ | | | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደ አስፈላጊነቱ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ የሆኑ በፅሑፍ የቀረቡ መረጃዎችን ይጠቀማሉ | | | | | |
| 12 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት የቀረቡ ይዘቶች በሕይወት ልምዴ ከማውቃቸው ጋር ዝምድና አላቸው | | | | | |
| 13 | በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ላይ ያሉት ምንባቦች ያስደስቱኛል | | | | | |
| 14 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የክፍሉን ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ ይቆጣጠራሉ | | | | | |
| 15 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የተሳሳተ መልስ ስሰጥ በትህትና እርማት ይሰጡኛል | | | | | |
| 16 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ትክክለኛ መልስ ስሰጥ ያስጨበጭቡልኛል | | | | | |
| 17 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በሚሰጠው | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሙከራዎች ጥሩ ውጤት ሳመጣ እንደ አስፈላጊነቱ ይሸልሙኛል | | | | | |
| 18 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ እንዲሳተፍ ከክፍል ጓደኞቼ እኩል እድል ይሰጡኛል | | | | | |
| 19 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የራሴን ፈጠራ እንዲጠቀም ያበረታቱኛል | | | | | |

**ክፍል አራት፡-** የክፍል ጓደኞቼን፣ ወላጆች እና የአከባቢ ማህበረሰብ በሚመለከት የቀረቡ መጠይቆች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለ ሁ | መወሰን ያስቸግረኛ ል | አልስማማ ም | በጣም አልስማማ ም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍል ጓደኞቼ ጥያቄዎች እንዲ መልስ ያበረታቱኛል | | | | | |
| 2 | የክፍል ጓደኞቼ በቋንቋ ትምህርት ወቅት በሚፈጠረው ስህተት አይስቁብኝም | | | | | |
| 3 | ወላጆቼ ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | | | | | |
| 4 | ወላጆቼ አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን እንዲያጠና ያበረታቱኛል | | | | | |
| 5 | በአከባቢዬ ያሉ ሰዎች ስለአማርና ቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | | | | | |

**ክፍል አምስት፡-** የተማሪዎች አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች

ውድ ተማሪ ቀጥሎ ለቀረቡልህ/ሽ/ ጥያቄዎች አዎ ወይም አይደለም የሚል መልስ በመስጠት

በተተውት ክፍት ቦታዎች ላይ ምክንያቶቻቸውን ፃፍ/ፊ/

1. የአማርኛን ቋንቋ የሚማረው የመማር ፍላጎት ስለለኝ;

አዎ ☐ አይደለም ☐

ምክንያቱም-----------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ ትምህርቱን የሚያስተምሩበት ስልት ይስማማኛል/ሻል/

አዎ ☐ አይደለም ☐

ምክንያቱም---------------------------------------------------------------------------------------------

---

## አባሪ ሐ

## ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንሰና ሕዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዩጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃል መጠይቅ

የቃል መጠይቅ ዓላማ

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ለቋንቋ ትምህርቱ ማነሳሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ምን ያህል እንደሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

ውድ መምህር፡- የቃለ መጠይቁ ከዚህ ሌላ የተለየ ዓላማ እንደሌለው በመገንዘብ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ለሚያደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

አጥኚው

**ክፍል አንድ**

ግላዊ መረጃ

1.1 ፆታ ____________________

1.2 እድሜ ____________________

1.3 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ____________________

1.4 የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡- ዓብይ__________________ ንዑስ___________________

1.5 የትምህርት ደረጃ___________________________________________

1.6 የአገልግሎት ዘመን_________________________________________

**ክፍል ሁለት**

የመምህሩን ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች

2.1 በሳምንት ምን ያህል ክፍለ ጊዜ ያስተምራሉ?

2.2 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላ በተጨማሪነት የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት አለ?_________________________

ለምን?______________________________

2.3 በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት?

2.4 የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ?________________ ካለ ምን ዓይነት________________ ለስንት ጊዜ____________

ከሌለ ምን ይመስልዎታል____________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

2.5 የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው? ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ፣

2.6 በሙያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ?______________________________________________

**ክፍል ሶስት**

የክፍል ውስጥ ክንውን የሚመለከት ጥያቄዎች

3.1 በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው?

ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ

3.2 የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን ዓይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ?

3.3 በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ?

በቡድን፣ በጥንድ፣ በነጠላ

3.4 የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ የመምህር ተማሪ ተረክቦ ንቁ እና ሳቢ እንዲሆን ምን ዓይነት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ?

3.5 በመማር ማስተማር ሂደት ከተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ሌላ ምን ዓይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ?

3.6 በመማር ማስተማሩ ሂደት የክፍል ተማሪዎች በራስ መተማመንና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን ዓይነት ስልት ይጠቀማሉ?

3.7 በመማር- ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ሥራ ይከታተላሉ? ለምን

3.8 የክፍል ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? አዎ ካሉ ምን፣ ምን ቃላትን ይጠቀማሉ?

የለም ካሉ ለምን?

3.9 የክፍል ተማሪዎቹም መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን ዓይነት ቃላትና ሐረጋትን በመጠቀም ከስህተታቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ?

3.10 የክፍል ተማሪዎቹም ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምን ምን ናቸው?

3.11 ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎችዎ ሽልመው ያውቃሉ?

3.12 በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥፋት የፈፀሙት ተማሪዎች አጋጥመዎት ያውቃሉ? ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን ነበር? ለምን?

## ክፍል አራት

### አስተያየት

4.1 ስለ ክፍል ተማሪዎችዎ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4.2 ስለ ቋንቋ ትምህርቱ አቀራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ?

4.3 ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁሟቸው አስተያየቶች

# አባሪ መ

ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ናሙና

**ክፍል አንድ**

***መምህር ሀ***

*ግላዊ መረጃ*

1.1. *ፆታ*<u>ወንድ</u>

1.2. እድሜ <u>48</u>

1.3. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት <u>ቂልጡ ካራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት</u>

1.4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት

አብይ <u>አማርኛ</u> ንዑስ <u>ኦሮምኛ</u>

1.5. የትምህርት ደረጃ <u>B.A ዲግሪ</u>

1.6. የአገልግሎት ዘመን <u>28</u>

**ክፍለ ሁለት**የመምህሩ ሁኔታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች

2.1. በሳምንት ምን ያህል ጊዜያት ያስተምራሉ; ሃያ አራት

2.2. ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላ በተጨማሪነት የሚያስተምሩ የትምህርት ዓይነት አለ?

የለም

2.3.በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት? <u>የለም</u>

2.4.የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ?<u>አላውቅም</u>

ካለ ምን አይነት ______________ ለስንት ጊዜ _________ ከሌለ ምን ይመስሎታል_____

2.5.የአማርኛን ቋንቋ ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው <u>ከፍተኛ</u>

2.6.በሙያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ?

አላገኘም

**ክፍል ሦስት**

የመምህራንን የተነሳሶት ስልት በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች

3.1. በመማር- ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው?

ዝቅተኛ

3.2. የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን ዓይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ?

ተማሪዎችን በቡድን እያደራጁ እንዲወያዩ ማድረግ

3.3. በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ?

በአብዛኛው በነጠላ እንዲሳተፉ ሲደረግ አልፎ አልፎ ግን በጥንድ በማድረግ እንዲሳተፉ አደርጋቸዋለሁ፡፡

3.4. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ የመምህር ተማሪ- ተራክቦን ንቁና ሳቢ እንዲሆን ምን ዓይነት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ?

ተማሪዎች ጥያቄዎች እንዲመልሱ እድል እሰጣለሁ፡፡ ምሳሌዎችን በማቅረብ በቀላል መንገድ እንዲረዱ አደርጋለሁ፡፡

3.5. በመማር- ማስተማሩ ሂደት ከተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ሌላ ምን ዓይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ?

ለሰዋስው ትምህርት የሚያግዙ መፅሐፍት ስለ ድርሰትና ስለ አንቀጽ ማብራሪያ የሚሰጡ መጽሐፍት እጠቀማለሁ፡፡

3.6. በመማር- ማስተማሩ ሂደት የክፍል ተማሪዎች በራስ መተማመንና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን ዓይነት ስልት ይጠቀማሉ?

ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ "አይዟችሁ፣ በርቱ፣ ትክክል ናችሁ " በማለት በማበረታታት ድፍረት እንዲያገኙ አደርጋለሁ፡፡

3.7. በመማር- ማስተማሩ ሂደት ክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ስራ ይከታተላሉ?

<u>አዎ፡፡ ምክንያቱም የክፍሉ ፀጥታ እንዳይታወክ ተማሪዎች ስራቸውን በጥንቃቄ እንዲሰሩ ለማድረግ እከታተላለሁ፡፡</u>

3.8. የክፍል ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? አዎ ካሉ ምን ምን ዓይነት ቃላትን ይጠቀማሉ?

<u>አዎ</u> ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ "በጣም ጥሩ፣ ጥሩ ነው፣ ጎበዝ፣ በዚሁ ቀጥል(ይ) " በማለት አበረታታለሁ፡፡

3.9. የክፍል ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን ብለው በመናገር ከስህተታቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ?

<u>"መሳሳት ምንም አይደለም" በማለት ስህተታቸውን በመግለጽ እንዲታረሙ አደርጋለሁ</u>

3.10. የክፍል ተማሪዎችዎ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምን ምን ናቸው?

<u>ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ፣ አመሰግናለሁ የሚል ቃላትን እጠቀማለሁ፡፡</u>

3.11. ጥሩ ውጤት ላመጡት ተማሪዎች ሽልመው ያውቃሉ;

ምንም ሽልመው አላውቅም

3.12. በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥፋት የፈፀመ ተማሪዎች አጋጥሞዎት ያውቃሉ;ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን ዓይነት ነበረ;

<u>አዎ ተማሪዎች ከጥፋታቸው እንዲታረሙና ሌሎች ተማሪዎችን እንዳይረብሹ ከክፍል አስወጥቼአቸው ከጥፋት እንዲመለሱ ተግሳጽ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡</u>

## ክፍል አራት

## አስተያየት

4.1. ስለ ክፍል ተማሪዎችም የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡-

- *የክፍል ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው ፡፡ምክንያቱም አብዘኛው ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ለመመለስ ፍቃደኛ አይደለም፡፡ የሚመልሱ ተማሪዎችም ቢኖሩም እንኳን ቋንቋን ለመናገር ቃላት ስለሚያጥራቸው መልሶችን ለመመለስ ይቸገራሉ፡፡ አንዳንድ ቃላትን እያቀላቀሉ ሲነገሩ የሚያዳምጡ ተማሪዎች ስለሚያሽኳሽኩባቸው በነፃነት ከመናገር ይቆጠባሉ፡፡አንዳንዶች ተማሪዎች ደግሞ በትምህርት ወቅት በጥንቃቄ ከመከታተል ይልቅ እርስ በርስ ስያወሩና የግል ሥራቸውን ሲሰሩ በማየት ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንደሆነ መገመት ችያለሁ፡፡*

4.2. ስለቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡

- *የቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎች በከባድ ቃላት የቀረበ ስለሆኑ ተማሪዎች ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ ተማሪዎች ክሂሎትን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ትዕዛዛትና መልመጃዎች ቢኖሩም የመጽሐፍ ይዘት ስፋት ስላለው ሁሉንም መተግብር አይቻልም*፡፡

4.3. ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁሟቸው አስተያየቶች ካሉ፡-

- *የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ በቀላል ቋንቋ ቢዘጋጅ ተማሪዎች ሁሉንም ክሂሎች በነቃ ተሳትፎ እንዲተገብሯቸው ፡ በመጽሐፍ የቀረበ ይዘቶች መጠናቸው ቢቀነስ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት ያላቸው በመሆናቸው እንደ አስፈላጊነቱ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን መፍጠር አይቻልም፡፡ ስለዚህ ሌሎች የመማሪያ ክፍሎች ተገንብቶው በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር ወደ ሃምሳ ዝቅ ቢል ጥሩ ነው እላለሁ፡፡*

**መምህር ለ**

**ክፍል አንድ**

*ግላዊ መረጃ*

1.1. *ፆታ*<u>ወንድ</u>

1.2. እድሜ <u>38</u>

1.3. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት <u>አገምሰ በልአ ሁለተኛ ደረጃ</u> ትምህርት ቤት

1.4. የሰለጠኑበት ትምህርት ዓይነት

አብይ <u>አማርኛ</u> ንዑስ <u>እንግሊዘኛ</u>

1.5. የአገለግሎት ዘመን <u>20(ሂያ)</u>

## ክፍል ሁለት

*የመምህሩ ሁኔታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች*

2.1. በሳምንት ምን ያህል ጊዜያት ያስተምራሉ; <u>ሂያ አራት</u>

2.2. ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላ በተጨማሪነት የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት አለ;<u>የለም</u>

2.3. በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት; <u>¾KU</u>

2.4. የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ; <u>አላውቅም</u>

2.5. የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው; <u>ከፍተኛ</u>

2.6. በሙያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ; <u>አላገኝም</u>

## ክፍል ሦስት

የክፍል ውስጥ ክንውን የሚያመለክቱ ጥያቄዎች

3.1. በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው; <u>መካከለኛ</u>

3.2. የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን ዓይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ;

- ተማሪዎች ስለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከፍ እንዲል ከዚህ በፊት ዘጠነኛ ክፍልን ተምረው ያለፉ ተማሪዎች የተሰሩ አንዳንድ መልመጃዎችን በምሳሌነት አሳያቸዋለሁ፡፡
- ትምህርቱን ከመጀመሬ በፊት አዝናኝ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወደ ትምህርቱ በአስደሳች ሁኔታ እንዲገቡ አደርጋለሁ፡፡
- በክፍል ውስጥ የውድድር መንፈስ እንዲኖር ለየቡድኑ ነጥብ በመያዝ እንዲከራከሩ አደርጋለሁ፡፡

3.3. በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ;

- በጥንድ እና በቡድን

3.4. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ንቁ እና ሳቢ እንዲሆን ምን ዓይነት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ;

- አዝናኝ ቀልዶችን በመጠቀም ከተማሪዎች ጋር መልካም የሆነ ግኑኝነት በመፍጠር አስደሳች እንዲሆን አደርጋለሁ፡፡

3.5. በመማር- ማስተማር ሂደት ከተማሪ መፅሐፍ ሌላ ምን አይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ;

- እንደ ቅኔ፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ፈሊጣዊ አነጋገር ያሉትን በመሰብሰብ ከማስታወሻ ፅሑፎች ላይ አስተምራለሁ፡፡ የስዋሰው መፅሐፍትና የቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍትን፤ የሰዋስውና የድርሰት መልመጃዎችን ለማስተማሪያነት እጠቀማለሁ፡፡ አልፎ አልፎ ከጋዜጣ እና ከመፅሔት ላይ የሚገኙ ምንባቦችንና ስዕሎችን በመርጃ መሳሪያነት እጠቀማለሁ፡፡

3.6. በመማር- ማስተማር ሂደት የክፍል ተማሪዎች በራስ መተማመን እና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን ዓይነት ስልት ይጠቀማሉ;

- ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ፊት ለፊት መጥተው ጭውውት እንዲያደርጉ አደፋፍራለሁ፡፡ ቃለ- ምልልሶችን ከእኔ ጋር እንዲያደርጉ እጋብዛቸዋለሁ፡፡ ለሚሰሩት ስራአድናቆትን እሰጣቸዋለሁ፡፡

3.7. በመማር- ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ስራ ይከታተላሉ;

- አዎ ምክንያቱም ተማሪዎች የሚሰሩት የክፍል ስህተት ከሆነ እንዳርማቸውና ያጋጠማቸውን ችግር አጠገባቸው ሂጄ እንዲፈታላቸው እንዲሁም በትጋት እንዲሰሩ ለማድረግ እከታተላቸዋለሁ፡፡

3.8. የክፍል ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ; አዎ ካሉ ምን ዓይነት ቃላት ይጠቀማሉ; የለም ካሉ ለምን;

- <u>አዎ፡፡ የምጠቀማቸው ቃላት "በጣም ጥሩ ነው፣ ለሁላችሁም የሚጠቅም ጥያቄ ነው፣ ጎበዝ ልጅ" በማለት አበረታታቸዋለሁ፡፡</u>

3.9. የክፍል ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን ብለው በመናገር ከስህተታቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ;

- <u>በጣም ጥሩ ሙከራ ነው፣ ሌላ ይህንን መልስ የሚቃወም ካለ በማለት የተማሪውን መልስ ቀየር በማድረግ "እንዲህ ለማለት ፈልገህ(ሽ) ነው" በማለት ወደ ትክክለኛው መልስ እንዲመጣ(ጭ) እና ስህተቱን እንዲያርሙ አደርጋለሁ፡፡</u>

3.10. የክፍል ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምን ምን ናቸው;

- <u>"በጣም ጥሩ ፣ ጎበዝ፣ አንበሳ አግኝተሃል" በማለት አበረታታችዋለሁ፡፡</u>

3.11. ጥሩ ውጤት ላመጡት ተማሪዎች ሽልመው ያውቃሉ;

- <u>ምንም ሽልሜ አላውቅም</u>

3.12. በመማር- ማስተማር ሂደት ጥፋት የፈፀሙ ተማሪዎች አጋጥመዎት ያውቃሉ; ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን ዓይነት ነበር; ለምን;

- <u>አዎ፡፡ የወሰድኩት እርምጃ በቅድሚያ ተማሪው ጥፋቱን ሲፈፅም ሌላውን ተማሪ በማይረብሽ መልኩ በአይኔ ገርመም አድርጌው አልፋለሁ፡፡ ከዚያ በኃላ ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ ጠርቼ ለምን ጥፋቱን እንፈፀመ በመጠየቅ ምክር እሰጠዋለሁ፡፡</u>

## ክፍል አራት

## አስተያየት

4.1. ስለ ክፍል ተማሪዎችዎ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ

- <u>የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ ተሳትፎ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ጥያቄ ለመጠየቅና ለመመለስ በፈቃደኝነት ይሳተፋሉ፡፡ ያልገባቸው ጥያቄ ካለ ከመማሪያ ክፍል ውጪም ቢሆን ሲያገኙኝ ይጠይቁኛል፡፡ ተማሪዎቹ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እርስ በርሳቸው ሲረዳዱና ሲተጋገዙ ይታያሉ፡፡ ስህተትም ቢሰሩ እርስ በርሳቸው ይሳሳቃሉ፡፡ የሚማሩትን ትምህርት በማጥናት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ፡፡</u>

4.2. ስለ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡-

- <u>የቋንቋ ትምህርቱ ስፋት ያለው ሲሆን ሁሉንም መልመጃዎች በተረጋጋ መልኩ ለማስተማር ጊዜ ያንሳል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ዐረፍተ ነገር ሥሩ፣ ቃላት መስርቱ</u>

*__የሚሉ ትዕዛዝ ሲያጋጥሟቸው ቀላል መስሎ ስለሚታያቸው ችላ ብለው ያልፉታል፡፡ አንዳንዶቹ ምንባቦቹ ስለማይስቧቸው ሌላ ምንባብ እንዲነበብላቸው ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎች አከባቢ ጋር የሚስማሙ ምንባቦች ቢዘጋጅላቸው ጥሩ ነው፡፡__*

4.3. **ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁሟቸው አስተያየቶች አሉ፡-**

- *__የመማሪያ መፅሐፍ ይዘት መጠኑ ቢቀነስ፤ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ስለሆነ ተማሪዎች አንዳንድ የሚከብዱ ቃላትና ሀረጋት ቀለል ባለ መልኩ ቢቀርብላቸው ጥሩ ነው እላለሁ፡፡__*